ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ

ገብሩ አሥራት

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

ታተመ በአሜሪካ
2006 ዓ.ም.

© የጸሐፊው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው:: ይህን መጽሐፍ ካለ ጸሐፊው ፈቃድ ማሳተም፣ ለውጠ፣ ገልብጠ፣ አዛውሮ መጻፍና ወደ ሌላ ቋንቋ መተርጎም፣ በሕግ የተከለከለ ነው::

ISBN: 978-0-578-14650-8

ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ
የመጀመሪያ ኅትም 2006 ዓ.ም.

በመጽሐፉ ሽፋን ላይ የሚታየው ካርታ ከኢንተርኔት የተወሰደ ነው::

ፖ.ሳ.ቁ. 31366
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ኢሜይል፣ 2002dima02@gmail.com

Printed in the USA
Signature Book Printing
www.sbpbooks.com



መታሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ዴሞክራሲን ለማስፈንና የአገር
ሉዓላዊነትን ለማስከበር ሕይወታቸውን ላጡት፣
በአካልም ይሁን በሞራል ለተጎዱት፣ ለታሰሩት፣
ለተሰቃዩትና ለተሰደዱት ኢትዮጵያውያን
በሙሉ መታሰቢያ ይሁንልኝ::

ማውጫ

ምስጋና xi

ማብራሪያ xii

የአማርኛና የትግርኛ ምሕጻረ ቃላት ትርጉም xiii

መግቢያ 1

ምዕራፍ አንድ፤ የታሪክ መንደርደሪያ

1. ቀይ ባሕር በአክሱም የግዛት ዘመን 7
2. የቱርኮችና የፖርቱጋሎች ሽኩቻ 10
3. ከዘመነ መሳፍንት እስከ አጼ ምኒልክ፣ የኤርትራ መፈጠር 14
4. የኢጣልያ ወረራና የኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋራ መዋሐድ 20
5. የአጼ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ፈተናዎች 28
6. የአጼው ሥርዓት መጨረሻ ቀናት 34
   - 6.1 አዲስ የትግል አቅጣጫ 34
   - 6.2 የፖለቲካ ድርጅቶች መመሥረት 35
   - 6.3 የዘውዳዊው ሥርዓት መገርሰስ 37

ምዕራፍ ሁለት፤ ህወሓት፣ ኢሕአዴግና የትጥቅ ትግሉ ዘመን

1. የተሓህት ምሥረታ 40
2. በሰሜን ኢትዮጵያ የነበሩ ተቃዋሚ ድርጅቶች 46
   - 2.1 ተጋድሎ ሓርነት ኤርትራ /ጀብሃ/ እና ህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ /ሻዕብያ/ 46
   - 2.2 ግምባር ገድሊ ሓርነት ትግራይ /ግግሓት/ 47
   - 2.3 ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ /ተሓህት/ 49
   - 2.4 የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ /ኢሕአፓ/ 52
   - 2.5 ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ /ጠራናፊት ኮሚቴ/- የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ጎብረት /ኢዴጎ/ 54
3. የኤርትራ ድርጅቶች ተጽዕኖ 56
4. ተሓህት/ህወሓት እና ሽኩቻዎቹ 62
   - 4.1 የተሓህትና የግንሓት ግጭት 63
   - 4.2 የተሓህትና የጠራናፊት ኮሚቴ/ኢዴጎ ግጭት 67
   - 4.3 የተሓህትና የኢሕአፓ ግጭት 73
5. ተሓህትን ያናወጠው ቀውስ 80
   - 5.1 የመጀመሪያው ቀውስ 80
   - 5.2 የ1969 ዓ.ም. ቀውስ 81
6. የደርግ ቀውጢ ቀኖች 91
7. የተሓህት የመጀመሪያ ጉባኤ 96

8. የህወሓትና የኤርትራ ድርጅቶች ግንኙነት 102
8.1 ሽካራው የህወሓትና የጀብሃ ግንኙነት 102
8.2 የሻዕብያና የህወሓት ጫጉላና ንትርክ 105
9. ህወሓትና የምሽግ ሶሻሊዝም *(Barrack Socialism)* 109
10. ከሻዕብያ ጋራ ዳግም አለመግባባት 115
11. የ1977 ዓ.ም. ድርቅና ሻዕብያዎች የተውት ጥቁር ነጥብ 121
12. የህወሓት ከኤርትራውያን በላይ ለኤርትራ መቆርቆር 123
13. የማሌሊት ምሥረታና እንድምታዎቹ 127
13.1 ማሌሊትን መመሥረትና የአመራር ሹም ሽር 127
13.2 የማሌሊት ዓለም ዐቀፋዊ ዓላማ፤ ክልላዊ አደረጃጀት 130
13.3 ማሌሊትና የህወሓት የአስር ዓመት ጉዞ 131
14. የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ኢሕዴን/ እና ህወሓት 136
15. የማሌሊት መፈጠርና የጦር ሜዳ ድሎች ሲገጣጠሙ 138
16. በግራ እጁ አልባንያ በቀኙ አሜሪካን የጨበጠው የህወሓት ዲፕሎማሲ 143
17. ሦስተኛው የህወሓት ድርጅታዊ ጉባኤና ከሻዕብያጋ ዳግም ጫጉላ 149
18. ከወታደርነት ወደ «ዴሞክራሲያዊ ድርጅት» መሥረታ 151
18.1 የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት /ኦሕዴድ/ 151
18.2 የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ /ኢዴመአን/ 153
19. የማሌሊት መክሰምና የመጀመሪያው የኢሕአዴግ ጉባኤ 154
20. የሕዝብ ድጋፍና ተሳትፎ በትጥቅ ትግሉ ሂደት 156
20.1 የከተማው ሕዝብ እንቅስቃሴ 156
20.2 የገጠሩ ሕዝብ እንቅስቃሴ 163
20.3 የውጭ አገሩ እንቅስቃሴ 170
21. የህወሓት የሰላም ጥሪና የደርግ ምላሽ 171
22. የኢሕአዴግ አዲስ አበባን መቆጣጠር 174

ምዕራፍ ሦስት፤ ከመንግሥት ምሥረታ እስከ ኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ዋዜማ /1983-1990 ዓ.ም./

1. ሽግግር መንግሥት በኢትዮጵያ፣ ጊዜያዊ መንግሥት በኤርትራ 177
2. የሕዝቡን ጥያቄ በአግባቡ ያልመለሰ የመንግሥት ሽግግር 184
3. የኤርትራ መገንጠልና የኢትዮጵያ ጥቅም መነካት 188
4. የሻዕብያ ኢትዮጵያን የመቆጣጠር ውጥን 192
5. የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች በኢትዮጵያ 194
6. የርዕዮተ ዓለም ውዥንብር በህወሓት/ኢሕአዴግ 196
7. የትእምት ባለቤትነት ጥያቄ 199
8. የ1985 ዓ.ም. የህወሓት ግምገማና ውዝግቦቹ 202
9. የሽግግሩን መንግሥት ያቋቋሙት ድርጅቶች መበታተን 206
10. የሻዕብያ ዝርፊያና ግድያ 210
11. የተሠው ታጋዮች ቤተሰቦች ቅሬታ 215

12. የሻዕብያ በሠራዊት ግንባታ መጠመድ 217
13. የኢሕአዴግ ሠራዊት መዳከም 219
14. የሻዕብያና የእነ መለስ ሜራ በትግራይ መስተዳድር ላይ 222
15. የቻይና ጉዟችንና የኤርትራን ተቃዋሚዎች ለማባረር መሞከሩ 228
16. የኢትዮ-ኤርትራ የጋራ ኮሚሽን መፍረስን ተከትሎ 232
16.1 የኮሚቴው የመጀመሪያ ግንኙነት /ግንቦት 19፣ 1987 ዓ.ም./ 232
16.2 በድንበር አካባቢ የተፈጠረው ውጥረት 233
16.3 የኮሚቴ ስብሰባዎችና ቀጣይ አለመግባባት 235
16.4 ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋ ውይይት 237
16.5 የሻዕብያ ቅሬታዎች፣ በሼኽ አላሙዲና በታምራት ላይኔ ላይ 240
16.6 የሻዕብያና የኢትዮጵያ ግንኙነት ይበልጥ መሻከር 244
17. የኢትዮጵያና የኤርትራ ግንኙነት በጦርነቱ ዋዜማ 246
17.1 የህወሓት/ኢሕአዴግ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መዳከም 246
17.2 ሻዕብያ ናቅፋ የተባለ ገንዘብ ስለማተሙ 252
17.3 የተካረረው የሁለቱ ፓርቲዎች ኮሚቴ ስብሰባ 255
17.4 በአሥመራ ቆይታችን የተገነዘብነው 256
17.5 ወደ አዲስ አበባ መልስና ከመለስ ዜናዊ ጋራ ክርክር 257
17.6 ሰሚ ያጣው የዐምስተኛው የህወሓት ጉባኤ ጩኸት 258
17.7 ጅማ የተኪያሄደው ቀዝቃዛው 3ኛው የኢሕአዴግ ጉባኤ 261
17.8 የሻዕብያዎች በድንገት በመቀሌው የካቲት ክብረ በዓል መገኘት 262
17.9 ወደ ትግራይ የጦር ኃይል እንዳይላክ ስለመከልከሉ 263
17.10 የሻዕብያ ግልጽ እንቅስቃሴና የኢሕአዴግ መጃጃል 266

ምዕራፍ አራት፤ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትና በህወሓት/ኢሕዴግ ውዝግብ

1. የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት አጀማመር 268
2. የመለስ ሻዕብያዎችን አንንካቸው ክርክር 270
3. የትግራይ መስተዳድር የክተት ጥሪ ያስነሣው ቁጣ 271
4. የአሜሪካና የሩዋንዳ የዕርቅ ሙከራ መክሸፉ 273
5. የሻዕብያ ግሥጋሜና የኢትዮጵያ ሠራዊት ያሳየው ጀግንነት 274
6. የሠራዊቱ፣ ሚሊሻው፣ የምልሱና የሕዝቡ ጽንዐት 277
7. የኤርትራውያን ከኢትዮጵያ መባረር 279
8. የአሜሪካኖች ሁለተኛው የማስታረቅ ሙከራ 281
9. የሻዕብያን ወረራ ለመቀልበስ የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ዝግጅት 283
10. የኢትዮጵያ የመጀመሪያው መጠነ ሰፊ ጥቃት 285
10.1 አሥመራ ድረስ ለመዝለቅ ስለመወሰኑ 285
10.2 ወታደራዊ ዝግጅቱና የውግያው ሂደት 286
10.3 ቀጣይ ጉልበት *(momentum)* ያጣው ጥቃት 289
11. የኢትዮጵያ ሠራዊት ለሁለተኛው ፍልሚያ መዘጋጀት 292

12. ለቀድሞ ጦር አባላት የተደረገው አገራዊ ጥሪ 295
13. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አ.አ.ድ የዕርቅ ሐሳብ 296
13.1 በአሜሪካና በአ.አ.ድ አስማሚዎች የጸደቀው ሰነድ 296
13.2 በቴክኒካል ቅንጅቱ ሰነድ የተደረገው ውይይት 298
13.3 በጠባብ መድረክ የተደረገው ውይይት 299
13.4 የድርጅቶቹ ውይይት 302
13.5 የኢሕአዴግ ምክር ቤት ውይይትና የዮሴፍ ረታ ጥያቄ 305
14. የመጨረሻው የማጥቃት ዕቅድና የዲፕሎማሲው ውስብስቦች 307
15. የማጥቃት ዕቅዱ የጫረው ውዝግብና እንድምታዎቹ 308
16. በሻዕብያ ላይ ጥቃት እንዳይኪያሄድ የሼክ አላሙዲ መማጸን 311
17. አንጸባራቂው ወታደራዊ ድልና የቀኝ ጓላ ዙሩ ትእዛዝ 312
17.1 በሻዕብያ ሠራዊት ላይ የተሰነዘረው ጥቃት 312
17.2 መለስ ቀኝ ጓላ ዙር ስለማወጁ 313
17.3 በሻዕብያ ላይ የተከፈተው ጥቃት የቆመበት ምክንያት 317
18. ሻዕብያ በጦር ሜዳ እጁን፣ ኢሕአዴግ መሬቱን፣ ሲሰጥ 318
19. በጦርነቱ ጊዜ ስለተኪያሄደው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ 322
19.1 ባለኸበት ይርጋውን መለስና ደጋፊዎቹ እንደተጠቀሙበት 322
19.2 በረቂቅ መርሐ ግብሩ ላይ የተከሰተው ልዩነት 324
20. ባለመግባባት የተቋጨው የህወሓት ፖሊትቢሮ ስብሰባ 330
20.1 የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባና ያሳለፈው ውሳኔ 330
20.2 ለውይይት የተቀረጹ አጀንዳዎችና ግምገማዎች 330
20.2.1 ፖሊትቢሮው የቀረጻቸው አጀንዳዎች 330
20.2.2 ከሻዕብያጋ የነበረን ግንኙነት ግምገማ 331
20.2.3 ወረራውን ስላለመተንበይና ዝግጅት ስላለማድረግ 333
20.2.4 በውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን ዙሪያ ውይይቶች 334
20.2.5 የጋራ አመራር እየተናደ የግለሰብ ወሳኝነት ስለመጠናከሩ 334
21. የመለስ የየካቲት በዓል ንግግርና የፖሊትቢሮው ስብሰባ መቋረጥ 335

ምዕራፍ ዐምስት፤ የህወሓት/ኢሕአዴግ ግምገማዎችና ክፍፍሉ

1. መለስ አዲሰ አጀንዳ ቀረጾ ስለመቅረቡ 337
2. የብአዴን አመራር በህወሓት ስብሰባ ለመሳተፍ ስለመጠየቁ 340
2.1 የብአዴን አመራር የአቋም ለውጥ 340
2.2 የብአዴን አመራር በህወሓት ስብሰባ ካልተሳተፍኩ 343
3. የነመለስ ሜራ ከወሳኙ የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ በፊት 349
4. ስብሰባው ሊጀመር ሲል የተከሰቱ ችግሮች 352
4.1 የተወልደ ወልደ ማርያም መታመም 352
4.2 የክንፈና የሙሉጌታ ከስብሰባው መውጣት፣ በውይይቱ አኪያሄድ አለመግባባት 353
5. የውይይቱ አጠቃላይ ሂደትና ውጤቱ 354

5.1 በመለሰና በተቃዋሚዎቹ የቀረቡ ጽሑፎች 354
5.2 የአንድ ወሩ ክርክር ውጤት 356
5.2.1 ቦናፓርቲዝም ላይ የተደረገው ውይይት 361
5.2.2 ተከራካሪዎችን የማዋከብና የመስበክ ዘመቻ 361
5.2.3 በሙስናና በፀረ-ዴሞክራሲያዊነት ዙሪያ አጭር ውይይት 362
5.2.4 የየካቲት በዓልን ለማክበር የስብሰባው መቋረጥ 363
6. ከመቀሌ መልስ የስብሰባው መቀጠልና የተላለፈው ውሳኔ 366
7. ጉባኤ እንዲጠራ ያቀረብነው አቤቱታ 368
8. የማዕከላዊ ኮሚቴው ስብሰባ መቋረጥና የማባረሩ እርምጃ 369
9. የክንፈና የሙሉጌታ የታገዱትን ማውገዝ 370
10. ለህወሓት ቁጥጥር ኮሚሽን የጻፍነው ደብዳቤ 372
11. የመቀሌው የካድሬዎች ስብሰባ 373
12. የመቀሌው የካድሬ ስብሰባ *«የለውጥ ሐዋርያት»* 381
13. የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶችን ትጥቅ የማስፈታት እንቅስቃሴ 382
13.1 የብአዴን አመራር ሚና 382
13.2 የኢሕአዴግ ምክር ቤት አስቸካይ ስብሰባና የመለስ የበላይነት መረጋገጥ 384
14. የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶችን ለመቆጣጠር ተጨማሪ ዘመቻ 393
15. ሠራዊቱን የማጥመቁና የማጥራቱ ዘመቻ 395
16. *«ኦፊንጋሮችን»* ከመንግሥት መዋቅሮች ማባረር 399
17. በውጭ አገር የትግራይ ተወላጆችን የመቆጣጠሩ ዘመቻ 402

ምዕራፍ ሰድስት፤ ተሃድሶውና ሳንካዎቹ

1. በተቀናቃኞች ላይ የተኪያሄደው የእስር ዘመቻ 405
2. ባልታሰሩት *«ኦፊንጋሮች»* ላይ የተፈጸሙ በደሎች 410
3. ህወሓት/ኢሕአዴግ በተሃድሶው ወቅት ለትግራይ ሕዝብ የገባው ቃል 413
4. ህወሓት/ኢሕአዴግና የሄጉ የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ 421
5. ታሪካዊው የ1997 ዓ.ም ምርጫና መዘዙ 428
5.1 የፖለቲካ ምኅዳሩ በመጠኑ ገርበብ ማለት 428
5.2 የመስቀል አደባባይ ሰልፎች 432
5.3 በምረጫ ሂደቱ አላስፈላጊ ቅስቀሳዎች 434
5.3.1 የገዢው ፓርቲ ኢንተርሃምዌ መጣብህ ቅስቀሳ 434
5.3.2 የተቃዋሚዎች ፓርቲንና ሕዝብን ያልለየ ቅስቀሳ 435
5.4 የተቃዋሚዎች ጎብረትና ኢሕአዴግ ያልጠበቀው የምርጫ ውጤት 437
5.4.1 የተቃዋሚዎች ጎብረት 437
5.4.2 ኢሕአዴግ ያልጠበቀው የምርጫ ውጤት 439
6. የኢሕአዴግ መልሶ ማጥቃት 441
6.1 የተቃወሚ መሪዎች ወህኒ መወርወር 441
6.2 ፓርላማው እንዳይናገር መሸበቡ 443

6.3 የሲቪል ማኅበረሰብ ነጻነት መነፈግ 444
6.4 የግል ፕሬሱ በቁጥጥር ሥር መዋል 445
6.5 አሸባሪው የፀረ-ሽብር አዋጅ 446
7. የደነገጠው ጭንቅላት ተጨማሪ እርምጃዎች 448
7.1 ብሔሮችን ማፋጠጥ 448
7.2 ኢሕአዴግ የአፈጻጸም ችግሮቼን አስወግዳለሁ ማለቱ 450
8. የ2002 ምርጫና የኢሕአዴግ ፍጹም የአንድ ፓርቲ አገዛዝ 451
8.1 ቅድመ ምርጫ ሁኔታዎች 451
8.2 የምርጫው ሂደት ክስተቶች 457
8.3 የ2002 ድኅረ ምርጫ የፖለቲካ ሁኔታ 462
9. የድኅረ ምርጫ 2002 የተቃዋሚዎች ሁኔታ 467
10. ተሃድሶውና ሳንካዎቹ በአጠቃላይ 470

ማጠቃለያ

1. በቀይ ባሕርና በአፍሪካ ቀንድ የኢትዮጵያ ቦታ የጎላ እንዲሆን መሥራት 473
2. በኢትዮጵያና በኤርትራ የተፈጠረውን ችግር ለዘለቄታው መፍታት 476
3. ኢትዮጵያዊነትና የብሔር ብሔረሰብ መብቶች እንደማይነጣጠሉ መግንዘብ 478
4. እውነተኛ ፌዴራሊዝምን ተግባራዊ ማድረግ 481
5. የዴሞክራሲና የመቻቻል እሴቶች ማስፈን 483
6. ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ፍትሕ የተረጋገጠባት አገር መገንባት 486

ዋቢ የተደረጉ ጽሑፎች

የአማርኛና የትግርኛ መጻሕፍት 492
የአማርኛና የትግርኛ ሰነዶች፣ ደብዳቤዎች፣ መጽሔቶችና ጋዜጦች 494
References 498

አባሪዎች፤

አባሪ አንድ፤ የገብሩ አሥራት ንግግር፣ አዲስ አበባ መስቀል አደባባይ፣ 1997 ዓ.ም. 501

አባሪ ሁለት፤ በክፍፍሉ ወቅት የኦሕዴድ አመራር ለኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚ አባላት የጻፈው ደብዳቤ 507

አባሪ ሦስት፤ ከብአዴን ፖሊትቢሮ ለኢሕአዴግ አመራር አባላት የተጻፈ ደብዳቤ 510

አባሪ አራት፤ የህወሓት ቁጥጥር ኮሚሽን ክፍፍሉን አስመልክቶ ያሳለፈው ውሳኔ 511

ምስጋና

ይህን መጽሓፍ ጀምሬ እስክጨርስ፤ በምክር፣ በሞራል፣ መረጃ በመስጠትና በተለያዩ ሌሎች መንገዶች፤ የረዱኝን በኢትዮጵያም ከኢትዮጵያም ውጪ ያሉትን ሁሉ ከልብ ላመሰግናቸው እወዳለሁ:: በተለይ የመጀመሪያውን ረቂቅ አንብቦ አመርቂ አስተያየቶችና ማብራሪያዎች የሰጠኝን አውዓሎም ወልዱን፤ ረቂቁን ደግማ አንብባ ጠቃሚ ግብአቶች ያደረገችልኝን አረጋሽ አዳነን፤ ጽሑፉን በማንበብ፣ በማረምና በማስተካከል ሳትታክት ሙሉ ጊዜዋን የሰጠችኝን ሠናይት ሥዩምን፤ እንዲሁም ጽሑፉን በተደጋጋሚ በማንበብ፣ ጠቃሚ አስተያየቶችን በመስጠት፣ የትግል ዘመን ትውስታዎቿን በማካፈልና የእጅ ጽሑፉን በኮምፕዩተር በማስፈር እገዛዋ ያልተለየኝን ባለቤቴን የውብማር አስፋውን እጅግ አመሰግናቸዋለሁ:: በመጽሐፉ ለሚኖረው ስሕተትና ግድፈት ግን ተጠያቂው እኔው ብቻ ነኝ::

ማብራሪያ

ይህ መጽሐፍ በበርካታ የታሪክ መረጃዎችና በግል ተሞክሬዬ ላይ የተመረኮዘ ነው። የተጠቀምኩባቸውን ጽሑፎች ምንጭና ማብራሪያዎች በየምዕራፉ በሚገኙ ከአንድ የሚጀምሩ ተከታታይ የእግርጌ ማስታወሻዎች እና መጽሐፉ መጨረሻ ላይ በሚገኙ የአማርኛ፣ የትግርኛና የእንግሊዝኛ ዋቢ የተደረጉ ጽሑፎች ጠቅሻቼዋለሁ።

ከመጽሐፉ መግቢያ ቀድሞ የሚገኘው የአማርኛና የትግርኛ ምሕጻር ቃላት ትርጉም፣ እንዲሁም ዋቢ የተደረጉ የአማርኛና የትግርኛ ጽሑፎች፣ የተቀመጡት በአበገደ ተራ ሲሆን፣ ዋቢ የተደረጉ የእንግሊዝኛ ጽሑፎች ደግሞ በኤቢሲዲ ተራ ተቀምጠዋል።

በመጽሐፉ በየቦታው ባልገለጸውም፣ ከእንግሊዘኛና ከትግርኛ መጻሕፍትና ጽሑፎች የወሰድኳቸውን ጥቅሶች ወደ አማርኛ የመለስኳቸው እኔው ራሴ ነኝ። ግልጽ ለማድረግ ይረዳ ይሆናል ብዬም ከአንዳንድ የአማርኛ ቃላት ጎን በቅንፍ የእንግሊዝኛ ትርጉማቸውን ጽፌያለሁ። ከዓመተ ምሕረት በፊት እ.አ.አ /*እንደ አውጸውያን አቆጣጠር*/ የሚል ከሌለ የተጠቀምኩት በአገራችን የዘመን አቆጣጠር ነው ማለት ነው።

በወል ተባዕቱንም /*ወንዱንም*/፣ አንስቷንም /*ሴቷንም*/ መጥቀስ ሲገባኝ በተባዕቱ የተጠቀምኩት፣ ለምሳሌ ታጋዩም ታጋይዋም ለማለት ፈልጌ በጥቅል ታጋዩ ያልኩት፣ በተለምዶ እንጂ በአድልዎ እንዳይደለ ይታወቅልኝ።

በመጨረሻም መጽሐፉ በባለሙያ አርታኢ ባለመታየቱ፣ የሆሄያት፣ የሰዋስው፣ የአገላለጽና የአቀራረብ፣ ግድፈቶች አሉትና የሥነ ጽሑፍ አግባቡን ባለመከተሌ አንባቢያንን ይቅርታ እየጠየቅኩኝ፣ ከመጽሐፉ ቅርጽ ይልቅ፣ ይዘቱና መልእክቱ ላይ እንዲያተኩሩልኝ እጠይቃለኹ።

የአማርኛና የትግርኛ ምሕጻረ ቃላት ትርጉም

አአድ	የአፍሪካ አንድነት ድርጅት
አብዴፓ	የአፋር ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ
አደፍ	አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ
አነግ	አፋር ነጻ አውጪ ግንባር
ኢአርአርፒ/ERRP	Ethiopian Rehabilitation and Recovery Program
ኢብዴድ	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት
ኢዴኃቅ	የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት
ኢዴኅ	የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት
ኢዴሊ	የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሊግ
ኢዴመአን	የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ
ኢዴቅ	የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ቅንጅት
ኢዴፓ	የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ
ኢሕአዴግ	የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር
ኢሕአድ	የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ድርጅት
ኢሕአን/EPRM	የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ንቅናቄ
ኢሕአሠ	የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ሠራዊት
ኢሕአፓ	የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ
ኢሕዴን	የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ
ኢላአድ	የኢትዮጵያ ላብ አደሮች አንድነት ድርጅት
ኢማሌድኅ	የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ኅብረት
አሠፓ	የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ
ኢሠፓአኮ	የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን
ኢሶዴፓ	የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራሲ ፓርቲ
ኢፌዴአመ/መድረክ	የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ መድረክ
ኤአግ/ELF	ኤርትራ አርነት ግንባር
አእነግ	የኦሮሞ እስላማዊ ነጻ አውጪ ግንባር
አብኮ	ኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግሬስ
አሕዴግ	የኦሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር
አሕዴድ	የኦሮሞ የሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት
አሕዴግ	የኦሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር
አሕኮ	የኦሮሞ ሕዝቦች ኮንግሬስ
አሕነኮ	የኦሞ ሕዝቦች ነጻ አውጪ ኮንግሬስ
አነግ	የኦሮሞ ነጻነት ግንባር
አፌዴን	የኦሮሞ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ
ቤሕነን	ቤኒሻንጉል ሕዝቦች ነጻ አውጪ ንቅናቄ
ብአዴን	ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ
ጋሕነን	ጋምቤላ ሕዝቦች ነጻነት ንቅናቄ
ግገሓት	ግምባር ገድሊ ሓርነት ትግራይ

ደአከ	ደቂ አንስትዮ ኮሚቴ
ደኢሕዴግ	የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ግንባር
ዴምህት	ዴሞክራሲያዊ ምንቅስቃስ ህዝቢ ትግራይ
ዴምሓኤ	ዴሞክራሲያዊ ምንቅስቃስ ሓርነት ኤርትራ
ህግዴፍ/ሻዕብያ	ህዝባዊ ግምባር ንዴሞክራሲን ፍትሕን
ህግሓአ/ሻዕብያ	ህዝባዊ ግምባር ሓርነት ኤርትራ
ህወሓት	ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ
ህሓሓ	ህዝባዊ ሓይልታት ሓርነት
ወሕዴግ	የወላይታ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር
ከሕኮ	የከምባታ ሕዝብ ኮንግሬስ
መኢአድ	መላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
መኢብዴፓ	መላው ኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ
መአሕድ	የመላው አማራ ሕዝብ አንድነት ድርጅት
መኢሶን	መላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ
ማገብት	ማሕበር ገስገስቲ ብሄረ ትግራይ
ማደት	ማሕበር ደቂ አንስትዮ ትግራይ
ማሌሊት	ማርኪሲስት ሌኒኒስት ሊግ ትግራይ
ማልት	ማሕበር ልምዓት ትግራይ
ማረት	ማሕበረ ረድኤት ትግራይ
ማተኣ	ማሕበር ተጋሩ አውሮፓ
ማተደአት	ማሕበር ተጋደልቲ ደቂ አንስትዮ ትግራይ
ማተሰአ	ማሕበር ተጋሩ ሰሜን አሜሪካ
ምሶነግ	ምዕራብ ሶማልያ ነጻ አውጪ ግንባር
ዓትሉዴ/ዓረና	ዓረና ትግራይ ንሉዓላዊነትን ዴሞክራሲን
ተሓኤ	ተጋድሎ ሓርነት ኤርትራ
ተሓህት	ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ
ተሓህት-ጠኮ	ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ ጠራናፊት ኮሚቴ
ትእምት	ትካል እግሪ ምትካል ትግራይ
ትሕነአድ	የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት
ትልማ	ትግራይ ልማት ድርጅት
ሲአን	የሲዳማ አርነት ንቅናቄ
ሳርት (SAERT)	Sustainable Agricultural and Environmental Rehabilitation of Tigray

መግቢያ

በ1993 ዓ.ም. የህወሓት አመራር ለሁለት ከተሰነጠቀ በኋላ በአገራችን በርካታ ፖለቲካዊ ክስተቶች የተስተዋሉ ሲሆን ከነዚህ አንዱም ተሃድሶ በሚል መፈክር ስም ሥልጣኑን ለማጠናከር የሞከረው የእነ መለስ ቡድን ለጊዜውም ቢሆን በአገራችን ልሂቃን፣ በሕዝቡና በምዕራባውያን ዘንድ ዴሞክራሲያዊ መስሎ ለመታየት ያደረገው ሙከራ ነው።ይህን ስልቱን ለማሳካትም መጀመሪያ ላይ የፖለቲካ ምኅዳሩን አሰፋዋለሁ ብሎ ለሕዝቡ ተስፋ ሰጥቶ ነበር። በወቅቱ በተለይ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምሁራንጋ በአራት ኪሎ ቤተ መንግሥት ረጅም ጊዜ የወሰደ ውይይት አኪያሂዶ ኢሕአዴግ በኢትዮጵያ መሠረታዊ ተሃድሶ ለማድረግና እውነተኛ የዴሞክራሲ ለውጥ ለማምጣት እንደሚጥር ቃል ገብቶ ነበር። ይህ የኢሕአዴግ የተሃድሶና የዴሞክራሲ ተስፋ ተግባራዊ ይሆናል የሚልግምት አድሮባቸውም ይሁን ክፍተቱን እንጠቀም ብለው በርካታ የአገራችን ምሁራን አዳዲስ የፖለቲካ ፓርቲዎችን አደራጅተው ለመንቀሳቀስ ሞክረው ነበር። ኢሕአዴግም እነዚህ በፓርቲ የተደራጁ ምሁራን ሥልጣኔን ከመሠረቱ ሊያናጉ አይችሉም ከሚል ግምት የቀየሰውን ሕዝቡን የማታለል ስልት ተግባራዊ ለማድረግ የመጫወቻ ሜዳውን በተወሰነ ደረጃ ከፈት አድርጎ የ1997 ዓ.ም. ምርጫ ተኪያሂደ። ምርጫው ተኪያሂዶ ውጤቱ ኢሕአዴግን ከቤተ መንግሥት የሚያስወጣው ሆኖ ሲገኝ ግን ኢሕአዴግ እጅግ ተደናግጦ «በካራ ጨዋታ የለም» እንዲሉ በአፋጣኝ ምኅዳሩን መዝጋት ጀመረ። በአጭር ጊዜም ቀደም ሲል ከነበረው የባሰ ዐፈና አኪያሂዶ በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ለእስር ሲዳርግ የፖለቲካ ፓርቲዎችን አቋቁመው በምርጫ የተሳተፉ በርካታ ምሁራንንም ዘር በማጥፋት፣ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል በመናድና በአገር ክሕደት ወንጀል ተከሰው ወህኒ ሲወርዱ ከ190 በላይ የሚሆኑ ዜጎች በአደባባይ ተገደሉ።

በወቅቱ ኢሕአዴግ በአንድ በኩል የአገራችንን ሕዝብና ልሂቃን በማታለል ሥልጣኑን ቅቡል *(legitimate)* ለማድረግ ሰፊ እንቅስቃሴ ሲያኪያሂድ በሌላ በኩል ደግሞ ከድርጅቱ አፈንግጠዋል ባለን ባላንጣዎቹ ላይ ብርቱ የማጥቃት ዘመቻ ከፈተ። እኛን ከጎበረተሰቡ ለማግለል ያልተጻፈና ያልተለፈፈ የማጥላላት መፈክር አልነበረም፤ የተሰነዘረው የስድብ ውርጅብኝም የሚያባራ አይመስልም ነበር። ፀረ-ዴሞክራቶች፣ ሙሰኞች፣ የበሰበሱ፣ ጎጠኞች፣ ጎሰኞች፣ ጠባቦች፣ ትምክሕተኞች፣ ወዘተ... የሚሉ ስያሜዎች በመለስና በጋሻ ጃግሬዎቹ ለወራት ያለማቋረጥ ተንጎድጉደውብናል። ከዚህ ዐልፎም የሻዕብያን ወረራ በመቀልበስ ረገድ ወሳኙን ሚና የተጫወተው «ጓድ መለስ እንጂ አፈንጋጮች አይደሉም» የሚለውን ተረት ለማስረገጥ የመንግሥትና የፓርቲ ሚድያዎች በከፍተኛ ደረጃ ጥረት አድርገዋል። ይህም አልበቃ ብሏቸው መለስን አጥብቀው ይቃወሙ ከነበሩት መኻል የተወሰኑትን የኢሕአዴግ አመራር አባላት ሙስና ፈጽመዋል በሚል ሽፋን ለእስር ዳርገዋቸዋል። ይህን ሁሉ ወንጀል ሲፈጽሙም ዴሞክራሲንና የሕግ የበላይነትን ተግባራዊ እያደረግን ነው፤ ተሃድሶውን ሥራ ላይ እያዋልን ነው እያሉ ነበር።

እነ መለስ የአገሪቱን ፖለቲካዊ ምኅዳር ለማፈንና ሕዝቡን አንበርክከው ለመግዛት ብዙ ሚልዮን ብር ወጪ እያደረጉ በመንግሥት ሚድያ አማካይነት በሚያሰራጩት ፕሮፓጋንዳና በሚያኪያሂዷቸው ሴሚናሮችና ስብሰባዎች ተቀባይነታቸውን ማረጋገጥ ስላልቻሉ በድጎማ *(Sponsorship)* ገንዘብ እየከፈሏቸው የሚያወድሷቸውን መጻሕፍት የሚጽፉ በርካታ እበላባዮችን ተጠቅመዋል። በተለይ በኢሕአዴግ «የልማት ድርጅቶች» ድጎማ የተጻፉ በወቅቱ በህወሓት/ኢሕአዴግ አመራር ላይ የነበሩትን ግለሰቦች ዝና የሚያወድሱ፣

ገድላቸውን እያነሱ የአገራችንን ታሪክ የሚበርዙ መጻሕፍት በብዛት ታትመዋል። «ታሪክ የሚጻፈው በገዢዎች ነው» እንዲሉ የኢሕአዴግ መሪዎችም ሥልጣንን ተቆጣጥረው ታሪክ በሚፈልጉት አቅጣጫ እንዲጻፍ ብርቱ ጥረት አድርገዋል። ይህን መጽሐፍ እንድጽፍ ካነሣሱኝ ምክንያቶች አንዱም ይህን በሕይወት እያለን የምናውቀውን ታሪክ የህወሓት/ኢሕአዴግ አመራር እያዛባውና እየከለሰው ለአገዛዙ እንደሚመች የሚያቀርበውን ታሪክ በማስተካከል ረገድ የበኩሌን አስተዋፅኦ ለማድረግ ነው።

ማንኛውም ገዢ ፓርቲ የሕዝብን ገንዘብ ተጠቅሞ ሥልጣኑን ለማስጠበቅ የተቻለውን ስለሚያደርግ ኢሕአዴግም በሚልዮኖች የሚገመት ገንዘብ እያፈሰሰ ይህንኑ ቢያደርግ አያስገርምም። እኔን በእጅጉ የሚያሳስበኝ ታሪክን በመበረዝ እየተጻፉ ያሉት መጻሕፍት በተለይ ወጣቱን ትውልድ አሳስተው ወዳልሆነ አቅጣጫ እንዳይመሩት ነው። ወጣቱ ከጊዜ በኋላ ራሱ ነጻ ሆኖ መርምሮና ተመራምሮ እውነታውን ይደርስበታል የሚል እምነት ቢኖረኝም ኢሕአዴግ እያሰራጨ ባለው መርዘኛ የውሸት ታሪክ የሚደናገሩ እንደማይጠፉ እገምታለሁ። ይህን መጽሐፍ ስጽፍ ሌላው ግንዛቤ ውስጥ ያስገባሁት ነገርም ቢያንስ እውነትን ፍለጋ ለሚሯሯጡት ይህን ዓይነት መጽሐፍ ማዘጋጀቱ እንደመነሻና እንደአማራጭ ሊጠቅማቸው ይችላል የሚለውን ነው።

በዚህ መጽሐፍ ለአንባቢው መነሻ ይሆናሉ በማለት በርካታ ጉዳዮችን ብዳስስም ዋናው ትኩረቴ ግን የህወሓት/ኢሕአዴግ አመራር በአገር ሉዓላዊነትና በዴሞክራሲ ዙሪያ ያራመዳቸውና አሁንም የሚያራምዳቸው አቋሞችና የፖለቲካ አቅጣጫዎች ላይ ነው። በእኔ ዕይታ የህወሓት/ኢሕአዴግ አመራር ሕዝቡን መርቶና አስተባብሮ የደርግን ሥርዓት በመጣሉ አምንታዊ ሚና ቢጫወትም ሥልጣን ከያዘ በኋላ ግን በሉዓላዊነትና በዴሞክራሲ ዙሪያ በርካታ መሠረታዊ ስሕተቶችን የፈጸመና አሁንም እየፈጸመ ያለ ድርጅት ነው። ባለንበት ዘመን ዴሞክራሲና የአገር ሉዓላዊነት በአንድ አገር ፖለቲካ ከፍተኛ ቦታ ስለሚይዙ ዜጎች በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው መወያየቱና መመካከሩ ጠቃሚ ነው የሚል እምነት አለኝ።

ስለአገር ሉዓላዊነትና ስለዴሞክራ ለመጻፍ ስሞክር የራሴን የቆየ የተሳሳተ ግንዛቤም ግምት ውስጥ አስገብቼ ነው። ቀደም ሲል በነዚህ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የጠራ አቋም አልነበረኝም። በመጽሐፉ ውስጥ እንደምገልጸውም የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ተኪያሂዶ የኢሕአዴግ አመራር ሲከፋፈል እንኳን የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በተመለከት የተሟላ አቋም አልነበረኝም። አፈንጋጮች የተባልነው ከነመለስ ቡድንጋ ሉዓላዊነትን በተመለከተ ስንከራከርም በጉዳዩ እምብርት ላይ አትኩረን ሳይሆን ጅራቱን ይዘን ነበር። ይኸውም የሉዓላዊነታችንን መከበር ጉዳይ ስናነሣ በሻዕብያ የተነጠቁትን ባድመን፣ ዓዲ ኢሮብን፣ ቡሬንና ሌሎች አካባቢዎች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛቶች እንደሆኑና ለኢትዮጵያ መመለስ እንዳለባቸው በማውሳት እንጂ ከሕግ፣ ከታሪክና ከፖለቲካ አንጻር የባለቤትነት መብት የሚያሰጠንን የሳብን የባሕር በር ጉዳይ ባካተተ መልኩ አልነበረም። እኔና አንዳንድ ጓደኞቼ የአሁኑን አቋማችንን የያዝነው ከክፍፍሉ በኋላ የአልጄርሱን ስምምነት መነሻ አድርገን የአገር ሉዓላዊነትን ትርጉም በሰፊው ከተወያየንበት በኋላ ነው። ከዚህ ውይይታችን በኋላ አፈንጋጮች ተብለን በክፍፍሉ ጊዜ ከህወሓት የወጣነውና የዓረና ፓርቲ መሥራቾችና አባላት የሆንነው የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መከበር የኢትዮጵያን የባሕር በር የማግኘት መብትንም እንደሚያካትት ስምምነት ላይ ደርሰናል። ይህ ስምምነታችን የኤርትራን ጥያቄ በተመለከተ ለረጅም ጊዜ ሳራምደው የነበረውን አቋም መለስ ብዬ እንዳጤነውና እንድመረምረው ምክንያት ከመሆኑም ባሻገር መሠረታዊ የአቋም ለውጥ እድርጌ ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ አብቅቶኛል።

በክፍፍሉ ወቅት በድርጅታችን የነበሩትን የዴሞክራሲ ችግሮች ያነሣናቸውም በወቅቱ ስንከተል የነበረውን ርዕዮተ ዓለምና የፖለቲካ አቅጣጫ ከመሠረቱ ፈትሸን አልነበረም። እንዲያውም፣ መጀመሪያው ላይ አፈንጋጮች የተባልነው አብዮታዊ ዴሞክራሲን ጠበቅ አድርገን ይዘን ስንከራከር መለስ ወደ ሊበራሉ ርዕዮተ ዓለም አዘንብሎ ነበር። ኋላ ላይ ግን ካድሬውንና አመራሩን ለመቆጣጠርና የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም የአብዮታዊ ዴሞክራሲን አቅጣጫ አራምዳለሁ ብሎ በመርሕ ደረጃ ተጻሮት የነበረውን አቋም እንደገና አንግቦታል። በመሆኑም የሁለታችንም ክርክር ያተኮረው በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ማዕቀፍ ሥር ዴሞክራሲን ተግባራዊ ለማድረግ ባሉት ችግሮች ላይ ነበር።

አፈንጋጮች የተባልነው ህወሓትን ለቀን ከወጣን በኋላ ለሦስት ዓመታት ያህል ባኪያሄድነው ያለፈው ጉዟችን ግምገማ ዴሞክራሲንና ሌሎች የፖለቲካ ችግሮቻችንን ለማየት የሞከርነው ዱሮ ስንከተለው ከነበረው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ አንጻር ነበር። ግምገማውና ክርክሩ እየተጠናከረ ሄዶም አብዮታዊ ዴሞክራሲ ምን ማለት ነው? ወደ ሶሻሊዝም የማያሻግር አብዮታዊ ዴሞክራሲ አለ ወይ? ከነአካቴው፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባል የፖለቲካ ሥርዓት አለ ወይ? የሚሉና ሌሎች በርካታ ጥያቄዎችን አነሣን። ጉዳዩ እጅግ መሠረታዊ በመሆኑም ሁላችንም ልንስማማ ባለመቻላችን አፈንጋጮች የተባልነው ዳግም ተከፋፈልን። በበኩሌ የዴሞክራሲን ጥያቄ በጥልቀት መመርመር የጀመርኩት ከዚህኛው «የአፈንጋጮች» ክፍፍል በኋላ ነው። በአለንበት ዘመን ፍትሐዊና ተራማጅ ሥርዓት እውን ለማድረግ ከተፈለገ ዱሮ በሄድንበትና በአንድ ፓርቲ አምባገነንነት የሚያምነውን አብዮታዊ ዴሞክራሲን መሠረት በማድረግ ነው ወይስ በሌላ አቅጣጫ? የሚለውን ጥያቄም አንሥቼ ነበር። አብዮታዊ ዴሞክራሲ ቀደም ሲል ኮምዩኒስቶች ከከፈል ፈውዳልና ከፊል ከበርቴ ሥርዓት ወደ ሶሻሊስት ሥርዓት ለመሸጋገር የተጠቀሙበት የፖለቲካ አስተሳሰብ እንደሆነና አሁን ደግሞ አምባገነኖች የዜጎችን ነጻነት በመገደብ የሥልጣን ዕድሜያቸውን ለማራዘም ምቹ ሁኖ ያገኙት የፖለቲካ አስተሳሰብ እንደሆነም ተገነዘብኩ። አስተሳሰቡ እውነተኛ ዴሞክራሲን ለማስፈን የሚበጅ እንዳልሆነና በኢትዮጵያ የለየለት የኢሕአዴግ አምባገነን ሥርዓት የነገሠው ይህን አስተሳሰብ መሠረት አድርጎ እንደሆነም ለመገንዘብ ቻልኩኝ።

ከአገር ሉዓላዊነትና ከዴሞክራሲ አንጻር ሥር ነቀል በሆነ መንገድ ከኢሕአዴግ አመራርጋ የተለያየሁት ከክፍፍሉ በኋላ ነው ስል በክፍፍሉ ሂደት ያነሣናቸው የክርክር ነጥቦች ፋይዳ አልነበራቸውም ለማለት አይደለም። የአስተሳሰብ ለውጥ ከጅምሩ በተሟላ መልኩ አይከሰትም። በቀውሱ ወቅት መጀመሪያ የተገነዘብኩት ነገር ቢኖር በኢሕአዴግ በምትመራው ኢትዮጵያ የአገር ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲን የማረጋገጡ አቅጣጫ በከባድ ችግሮች የተተበተበ መሆኑን ነው። ያኔ ሰባ ሚልዮን ሕዝብ የነበራት አገራችን አነስተኛ ሕዝብ ባላት ኤርትራ ስትወረርና መሪያችን ወረራውን ለመቀልበስ ወኔ አጥቶ ሲዋልል ወዴት እየተጓዝን ነው? የሚለውን ጥያቄለማንሣት ተገደድኩ። የሻዕብያን ወረራ ተከትሎ የተነሣው አቧራ ባይከሰት ኖሮ ኋላ ላይ የተነሡት በርካታ የፖለቲካ ጥያቄዎች በድርጅቱ ውስጥ ባልተነሡ ነበር፤ ለጥያቄዎቹም መልስ ለመስጠት ያደረግናቸውም ጥረቶች ቶሎ ባልተከሰቱ ነበር። በጦርነቱ ወቅትና ከዚያም በኋላ የተነሡት ውዝግቦች በግለሰብ ደረጃ ካስከተሉብኝ የአስተሳሰብ ለውጦች ባሻገር ለአገሪቱም ፈይደዋልእላለሁ። ሌላው ቀርቶ ለረጅም ጊዜ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ተጠምቀን ለግለሰብ ነጻነት እምብዛም ደንታ ያልነበረን ወገኖች ኢትዮጵያ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ የተለየ የፖለቲካ አቅጣጫ ካልተከተለች ዘላቂ ልማት ሊረጋገጥ እንደማይችል ለመገንዘብ ችለናል።

ይህን መጽሐፍ ስጽፍ ለዓመታት የቆየኹበትን ድርጅት ታሪክ በትረካ መልክ ለማቅረብ አይደለም። ታሪክን እንደ ትረካ ማቅረቡን አሁን በሥልጣን ላሉት የህወሓት/ኢሕአዴግ አመራር አባላትና ለተከታዮቻቸው እተወዋለሁ። የኢሕአዴግ መሪዎች በሚልዮኖች የሚገመት ገንዘብ እያፈሰሱ ሕዝቡ ትግላቸውን እንደ ገድለ ሰማዕታት እንዲቀበለው አድርገው በሥልጣን ለመቆየትና ከሞቱም በኋላ ዘልዓለማዊ ክብርና ዝና ለማግኘት መሞከሩን ተያይዘውታል። በሚጽፏቸውና በሚያጽፏቸው መጻሕፍት፣ በሚሰጧቸው መግለጫዎች፣ በሚያኪያሂዷቸው ሥልጠናዎችና ስብሰባዎች ሁሉ ህወሓት/ኢሕአዴግ የተጓዘበትን ታሪክ አውስተው በግላቸው የነበራቸውን ሚና ሊያጎሉ ይጥራሉ። በመጨረሻም ይህን የሕዝብና የሰማዕታት የተጋድሎ ታሪክ ጠቅልለው ለአንድ ሰው ለማሸከም ይሞክራሉ። ሰውየው ከሰውነት ዐልፎ እንዲመለክ ለማድረግም ይሞክራሉ። ይህን ሁሉ የሚያደርጉትም በአሁኑና በወደፊቱ ተግባሮቻቸው ከመኖር ይልቅ በዐለፈው ታሪክ መኖሩ ለሥልጣናቸው ህልውና ጠቃሚ ሆኖ ስላገኙት ነው።

በዚህ መጽሐፍ የማቀርበው የድርጅትና የአመራር ታሪክ ከላይ ከተጠቀሰው የተለየ ሲሆን ከረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ በመንደርደር ህወሓት/ኢሕአዴግ የተጓዘበትን ሂደት የሚተች ነው። ይህ አኪያሄዴ፤ ዐውቀው በሚያጠፉና ነገሩ ሳይገባቸው የተነገራቸውን ሁሉ እንደወረደ በሚቀበሉ ዘንድ ብዙ አሿራ ማንሣቱ አይቀርም። እንደ ጣዖት ሲመለክ የነበረን ድርጅትና አመራር ከመሠረቱ መተቸቴም ብዙዎችን እንደሚያስቆጣ አያጠራጥረኝም። ትቸቴ ይህን ዓይነት አቀባበል ይኖረዋል ብዬ ብገምትም የመረጥኩት ግን የነበረውንና ያለውን ኩነት *(Status quo)* ማወደስ ሳይሆን መጠየቅ ነው። እንኳንና አቋሜን በመጽሐፍ መልክ አቅርቤ፣ በ1997 ዓ.ም. መስቀል አደባባይ ላይ አጭር መግለጫ በማቅረቤ ገዥው ፓርቲና ተከታዮቹ እስካለሁን ድረስ ከጎብረተሰቡ ሊያገሉኝ ከንቱ ቅስቀሳ እያደረጉብኝ ነው። ሆኖም አመራሩን ያስቀይማል ወይም ያስቆጣል ብዬ እውነቱን ከማዳፈን በይፋ ማውጣቱን መርጫለሁ። ሐቅና ነጻነት የማምንባቸው ውድ የሰው ልጅ እሴቶች ናቸውና ለዚህ ድርጊቴ የሚያስፈልገውን ዋጋ ለመክፈል ተዘጋጅቻለሁ።

ይህ መጽሐፍ ሊነበብ ሌላ ሊነሣ የሚችል ጥያቄ አለ። ይኸውም ያለፈው ጉዞኽን ይህን ያህል ከተቸህ ጉዞኽ በሙሉ ከንቱ ነበር ወይ? ባደረከውስ ትጸጸታለህ ወይ? የሚለው ነው። ከዚህ ዐልፎም፣ እነዚያ ለመብትና ለነጻነት ሲሉ በህወሓት/ኢሕአዴግ ሥር ተደራጅተው የተፋለሙት፣ አካላቸውንና ሕይወታቸውን ያጡትን ወገኖች አስተዋፅኦ መና እያስቀረኽው አይደለም ወይ? የሚል ጥያቄም ሊነሣ ይችላል። በእኔ እምነት በህወሓት/ኢሕአዴግ የተሰለፍነውም እንሁን በሌሎች ድርጅቶች ተሰልፈው ደርግን የተፋለሙትን ታጋዮች ሁሉ ታሪክ በአዎንታ መዝግቧቸዋል። እዚህ ላይ መታየት ያለበት እነዚህ ታጋዮች ያስገኙት ውጤት ሳይሆን ያነገቡት አምባገነንነትን ገርስሶ ፍትሐዊ ሥርዓት የማስፈን ዓላማቸው ነው። ለዚህ ዓላማ ማንኛውንም ዓይነት መሥዋዕትነት የከፈለ ዜጋ ክቡር እንደመሆኑም በአገራችን ታሪክ ለዘልዓለም ሊዘከር ይገባዋል። ይህን ማለት ግን በዚህ የትግል ጉዞ የነበረውን የፖለቲካ አኪያሄድ ቢያንስ ከዴሞክራሲና ከአገር ጥቅም አንጻር የነበረበትን መሠረታዊ ጉድለት መመርመር የለበትም ማለት አይደለም። የእውነተኛ የፖለቲካ መጽሐፍ ፋይዳም የአሁኑንም ይሁን ያለፈውን ታሪክ ያለምንም ፍርሀትና ወገናዊነት በነጻነት እንዲታወቅ ማድረግ ነው። ጎብረተሰቡ ወደ ፊት መራመድ የሚችለውም የዚህ ዓይነቱ ድባብ ሲሰፍን ነው። ስለሆነም በዚህ መጽሐፍ ለጎሊናዬ ትክክል የመሰለኝን ሁሉ ለማስፈር መሞከሬም ሰማዕታቱ የተሠውለትን ዓላማ ለማክበር ሞክሪያለሁ።

በጽሑፌ የአንዳንዶችን ድርጅቶች ታሪክ ከህወሓትጋ ከነበራቸው ግንኙነት አንጻር አውስቼዋለሁ። ይህን ያደረኩት የራሴን ድርጅት ስተች እንዳደረኩት ሁሉ ከሌሎች ድርጅቶችምጋ የነበረንን ግንኙነት በማጤን እንድንማማር እንጂ ዳግም ወደ እርስበርስ ሽኩቻና መጠፋፋት እንድንገባ ወይም የሌሎችን ድርጅቶች ታሪክ ለማንኳሰስ አይደለም። ስለሌሎች ድርጅቶች ያለኝ መረጃ የህወሓት/ኢሕአዴግን ያህል አጥጋቢ ባለመሆኑ ባገኘሁት ውሱን መረጃና በራሴ በተወሰነ የግንኙነት አድማስ ላይ ብቻ ተንተርሼ አስተያየቴን አቅርቢያለሁ። የተነሣሁበትን ዓላማና ያጋጠመኝን የመረጃ ውስንነት በመገንዘብ ያልተሟላ አቀራረቤ በጠቀስኳቸው ድርጅቶች ዘንድ ቅሬታ እንደማይፈጥር ተስፋ አለኝ። በአቀራረቤ ሊፈጠር የሚችለውን ክፍተት ለማሟላትም ሆነ ለማስተካከል ተጨማሪ መረጃዎችን፣ ገንቢ አስተያየቶችንና ሂሶችንም ለመቀበል ዝግጁ ነኝ።

ይህ መጽሐፍ ከመግቢያውና ከማጠቃለያው ውጪ በስድስት ዋና ምዕራፎችና በበርካታ ርእሶች የተከፋፈለ ነው። አቀራረቡ በተለያየ የጊዜ ሰሌዳ የተከሰቱ አጋጣሚዎችን የሚከተል እንደመሆኑም ምዕራፎቹ በርዝማኔያቸውም ሆነ በዝርዝራቸው ተመጣጣኝ አይደሉም።

ምዕራፍ አንድ፣ የታሪክ መንደርደሪያ ሲሆን፣ ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እስከ ትጥቅ ትግሉ ዘመን ያሉትን አንኳር የአገራችንን ታሪክ ፍጻሜዎች፣ በተለይ ከሉዓላዊነትና ከዴሞክራሲጋ አያይዞ ይዳስሳል። ምዕራፉ በትጥቅ ትግሉ ወቅት የትግላችን መነሻ እንዲሆን የጻፍነውን ቁንጽል የኢትዮጵያ ታሪክ ለማስተካከል ይሞክራል።

ምዕራፍ ሁለት፣ የትጥቅ ትግሉን ዘመን የሚሸፍን ሲሆን፣ ይህም ቢሆን የ17 ዓመቱን ውስብስብ የትግል ሂደት በዝርዝር የሚተነትን ሳይሆን አንኳር ኩነቶችና ፍጻሜዎች ላይ የሚያተኩር ነው። ምዕራፉ አጭር ቢሆንም በርካታ አገራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በማንሣት ሂደቱን ለመፈተሽ ይሞክራል። በዚህ ምዕራፍ ህወሓት ውስጥ የተነሡ ቀውሶች፣ ከተለያዩ ድርጅቶችጋ የነበረው ግንኙነት፣ የተለያዩ የጎብረተሰብ ክፍሎች ሚናና የደርግ አወዳደቅ ይወሳሉ።

ምዕራፍ ሦስት፣ ህወሓት/ኢሕአዴግ የመንግሥት ሥልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ ከኤርትራጋ እስከተኪያሄደው ጦርነት ዋዜማ ድረስ ያለውን ሂደት የሚዳስስ ሲሆን፣ በተለይ የኤርትራን ነጻ መውጣትና ከሻዕብያጋ የነበረውን ግንኙነት በስፋት ለመዳሰስ ይሞክራል። የኢሕአዴግን የውስጥ ዴሞክራሲና ዲፕሎማሲም ይመለከታል።

ምዕራፍ አራት፣ የኢትዮ-ኤርትራን ጦርነት ሂደትና ጦርነቱን በድል ለመወጣት ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች ይዳስሳል። ይህ ምዕራፍ በተለይ መለስ ዜናዊና ተከታዮቹ ወረራው እንዳይቀለበስና ወራሪው ለፈጸመው ጥፋት በተመጣጣኝ መንገድ እንዳይቀጣ የፈጠሩትን ዘርፈ ብዙ ዕንቅፋት ከተመለከተ በኋላ ጦርነቱ ለሁለት በተከፈለው አመራር ተመርቶ እንዴት ግቡን ሳያሳካ ተሰናክሎ እንደቀረ ያሳያል።

ምዕራፍ ዐምስት፣ በድኅረ ኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ህወሓት ውስጥ የተፈጠረውን ቀውስና መሰንጠቅ የሚመለከት ሲሆን፣ በዚህ ዳሰሳም መለስና ተከታዮቹ እንዴት የበላይነት እንደተቀዳጁ ለማሳየት እሞክራለኹ። ቀውሱ የመንግሥት የጸጥታና የመከላከያ ተቋማትንና የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶችን ምን ያህል እንዳናጋና ኢሕአዴግ ውስጥ አዲስ የኃይል አሰላለፍ እንዳስከተለም እመለከታለኹ።

ምዕራፍ ስድስት፤ ከቀውሱ በኋላ የኢትዮጵያን የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች አያያዝ የሚዳስስ ሲሆን፣ የመለስ መንግሥት መጀመሪያ ፖለቲካዊ ምኅዳሩን ከፈት አድርጎ ሲያበቃ ከምርጫ 97 ሽንፈት በኋላ ግን፣ ዱሮ ከነበረበት በባሰ ሁኔታ ምኅዳሩን እንዳጠበበውና ይህን ለማሳካት የወሰዳቸው ፖለቲካዊ እርምጃዎችን ይዳስሳል። በተለይ የዜጎች ነጻነት ምን ያህል እንደታፈነና በተለያዩ አደረጃጀቶች እንደተሸበበም ያሳያል።

የመጽሐፉ ማጠቃለያ፤ ስድስቱን ምዕራፎች በመቀመር አገራችን ወዴት ማምራት እንዳለባት የግል አስተያየቶቼን ያመለክታል። መጽሓፉን ለመጻፍ ስነሣ አንዱ ዋና ምክንያቴም በዚህ የማጠቃለያ ምዕራፍ ያሰፈርኳቸው ሐሳቦች ለወደፊት ለውይይት ቀርበው ልንወያይባቸው እንችል ይሆናል የሚለው ተስፋዬ ነው።

ይህን መጽሐፍ ለማሳተም ያሰብኩት ከመለስ ዜናዊ ዕልፈት በፊት ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ይህ ሳይሳካልኝ ቀርቷል። ጽሑፉ መለስ ሲመራው የነበረውን ህወሓት/ኢሕአዴግን በስፋት የሚተች በመሆኑ እርሱ በሕይወት ኖሮ መልስ ቢሰጥበት ደስ ባለኝ ነበር። ይህ ባለመሆኑ ቅሬታ ቢሰማኝም፣ ሂደቶችንና ስሕተቶችን የምገመግመውና በሕይወት የሌለውን መለስንና በሕይወት ያሉትንም የማነጻጸሩ፣ ሥርዓቱን ለመተቸት እንጂ ከግል ቂም በቀል ተነሥቼ እንዳልሆነ አንባቢያን እንዲገነዘቡልኝ እፈልጋለሁ።

ምዕራፍ አንድ፤
የታሪክ መንደርደሪያ

1. ቀይ ባሕር በአክሱም የግዛት ዘመን

ኢትዮጵያ በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ ጥንታዊ ሥልጣኔ ካሏቸው አገሮች አንዷ እንደመሆኗ በተለያዩ አካባቢዎቿ ረጅም ዘመን ያስቆጠሩ የሥልጣኔ ማዕከላት ከማካበቷ ሌላ የአክሱምን ሥልጣኔ አፍርታለች። የአክሱም መንግሥት በደቡብ ቀይ ባሕር ዳርቻ የምትገኘውን የአዱሊስን ወደብ በመጠቀም በወቅቱ ኃያላን ተብለው ይታወቁ ከነበሩ መንግሥታትጋ የንግድ ግንኙነት እንደነበረው በርካታ የታሪክ መዛግብት ያመለክታሉ። የአዱሊስንና ሌሎች በደቡብ ቀይ ባሕር ዳርቻ የሚገኙ ወደቦችን ሁኔታ የዘገበው ስሙ የማይታወቀው ግሪካዊ በአንደኛው ምዕተ ዓመት በጻፈው «The Periplus of the Erythrean Sea»[1] አካባቢውን ገልጸታል። ከዚህ ቀድመውም ግብጻውያን እስከዚህ ደቡባዊ የቀይ ባሕር ዳርቻ እየመጡ እስከ ሠላሳ ዐምስት ያኽል ምርቶችን ይሸምቱ እንደነበር ተባባሪ ፕሮፌሰር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ በእንግሊዝኛ በጻፉት «Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270» መጽሐፋቸው አውስተውታል።[2] ፖል ሄንዚ የተባለው የታሪክ ጸሐፊም «ከአሁኗ የምጽዋ ወደብ በስተ ደቡብ በኩል የምትገኘው የአዱሊስ ወደብ የሞቀች የንግድ ማዕከል በመሆን የግብጽና የደቡብ ዓረብያ መርከቦች የሚያርፉባት ነበረች። ወርቅ፣ የዝሆን ጥርስ፣ ዕጣንና ሌሎች የትሮፒክ አካባቢ ምርቶች በገፍ ወደ ሜዲትራንያኑ ዓለም ይጎርፉ ነበር። በዚያን ጊዜ አዱሊስ የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ መንግሥት የነበረው የአክሱም ግዛት ዋና ወደብ ነበረች።»[3] ሲል ይተርካል። በሦስተኛው ክፍለ ዘመን የነበረው ማኒ የተባለው ፋርሳዊ ነቢይም «በዓለም ላይ አራት ትላልቅ ንግሥናዎች አሉ። የመጀመሪያው የባቢሎንና የፋርስ ንግሥና ነው፤ ሁለተኛው የሮም ንግሥና ነው፤ ሦስተኛው የአክሱማውያን ንግሥና ሲሆን አራተኛው ደግሞ የቻይናውያን ነው»[4] ይላል።

ከሦስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የነበረው የአክሱም ሥልጣኔ ባበበበት ወርቃማ ዘመን ከግብጽና ከሮማ ጋራም የዲፕሎማሲ ግንኙነት ጠንክሮ ነበር። በዚህ ዘመን የአክሱም ግዛት በጣም ሰፊ እንደነበር በአራተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አጋማሽ ላይ ነግሦ የነበረው ኤዛና የተወው የድንጋይ ላይ ጽሑፍ ያመለክታል። በጽሑፉ[5] ከተጠቀሱት ግዛቶች መኻል ሂምያር፣ ራይዳን፣ ሳብና ሐለን በደቡብ ዓረብያ የሚገኙ ሲሆኑ ጸያሞ ጋምቤላ እንደሆነ ቤጋ የሚለው ደግሞ ቤኻ እንደሆነና ጠቅላላው ግዛቱ ምዕራባዊ ኤርትራን አካቶ እስከ ምሥራቅ ሱዳን ይደርስ እንደነበር ይናገራል። ኤዛና የኑብያንና የፑንትን ግዛቶች ጭምር ይቆጣጠር እንደነበርም የታሪክ መዛግብት ይመሰክራሉ። ኑብያ ከአትበራ ወንዝ በስተምሥራቅ ያለውን የሱዳን ሰሜን ምሥራቅ ክፍል ሲያካትት የፑንት ግዛት እስከ አሁን ድረስ የትኛውን ክፍል እንደሚያመለክት በውል ባይታወቅም ከቀይ ባሕር በስተ ደቡብ ያለውን ግዛት እንደሚያካትት ግን የተለያዩ የታሪክ ሰነዶች ያመለክታሉ።

---

[1] Henze, P.B. 2011. *The Origins of Eritrea*, http://www:africans.com /articles/2011/01/01/, p.1

[2] Sergew Hable Selassie. 1972. *Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270.* Haile Selassie University, Addis Ababa, p. 23.

[3] Henze, op.cit., pp. 1-2.

[4] Henze, P.B. 2000. *Layers of Time: A History of Ethiopia.* New York: St Martin's Press, p. 22.

[5] Sergew Hable Selassie, op.cit., p.93.

በጊዜው በነበሩት የዓለም ኃያላን መንግሥታት ግንኙነት የንግድ ብቻ ሳይሆን ልክ እንደአሁኑ ገኖ ለመውጣትና ልዕለ ኃያልነትን ለማረጋገጥ ብርቱ ፉክክርም ነበር። በተለይ ከአራተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በባይዘንታይንና በፋርስ መካል ዓለምን ለመቆጣጠር ብርቱ ፉክክር ስለነበር ባይዘንታይን ደቡብ ዓረብንና ቀይ ባሕርን በማቋረጥ ከህንድ፣ ከቻይናና ከሌሎች የሩቅ ምሥራቅ አገሮች ጋራ የምታደርገው የንግድ ግንኙነት በፋርሳውያን እንዲቋረጥባት አትፈልግም ነበር። ፋርሳውያንም እንዲሁ ደቡብ ዓረብንና ቀይ ባሕርን ተቆጣጥረው በሜዲቴራንያን በኩል ወደ ምዕራብ ያደርጉት የነበረውን የግዛት መስፋፋትና የንግድ ግንኙነት ዋነኛ ተቀናቃኛቸው አድርገው ይቆጥሯት በነበረችው በባይዘንታይን እንዲገታባቸው አይፈልጉም ነበር። በአጠቃላይ ሁለቱም ተቃናቃኞች ቀይ ባሕርን በንግድ መሥመር አማራጭነት የመጠቀም ፍላጎት ነበራቸው[6]።

ባይዘንታይን ቀይ ባሕርን ለመጠቀም ከግብጽ እስከ ህንድ ውቅያኖስ ያለውን የባሕር ጠረፍ መቆጣጠር የግድ ይላት ነበር። በመሆኑም ከአካባቢው ኃይሎች በተለይ ደግሞ ከአክሱም መንግሥትጋ ግንኙነቷን ለማዳበር ስልቶችን ቀይሳ ነበር። ከስልቶቿ አንዱም አክሱምን በክርስትና እምነት አጥምቆ ጠንከራ ስትራቴጂያዊ ወዳጅ በማድረግ ቀይ ባሕርን መቆጠ ቀጠርና የባይዘንታይንን ጥቅም ማስጠበቅ ነበር። በአራተኛው ክፍለ ዘመን ንጉሥ ኤዛናን በክርስትና ያጠመቁት የመጀመሪያው ጳጳስ ፍሬምናጦስና ወንድማቸው ኤዴሽስ ወደ አክሱም የመጡት ከባይዘንታይን ግዛት ነበር። እንዲሁም ከ460 ዓ.ም. እስከ 470 ዓ.ም. በነበረው የንጉሥ አል ዓሜዳ ዘመን ወደ አክሱም ግዛት የፈለሱት ተስዓቱ ቅዱሳን የሚባሉ የወንጌል ሰባኪዎች መነሻቸው ባይዘንታይን ነበር።[7] የአክሱሙ ንጉሥ ኤዛና ክርስትናን መቀበልም ክርስትና በኢትዮጵያ ታሪክ የመንግሥት ሃይማኖትና ርዕዮተ ዓለም እንዲሆንና ለዘመናት በፖለቲካው፣ በባህሉ፣ በኪነ-ጥበቡ፣ በማኅበራዊ ኑሮው በኢኮኖሚውና ከሁሉም በላይ ግን በዲፕሎማስያዊ ግንኙነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዲያሳድር ፈር ከፍቷል።

በስድስተኛው ክፍለ ዘመን እጅግ ገናና የነበረው ንጉሥ ካሌብ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ የአይሁድ እምነት ይከተል የነበረውን የደቡብ ዓረብን ንግሥና እ.አ.አ በ525 ዓ.ም. በቁጥጥሩ ሥር አውሎ አካባቢውን ለተወሰነ ጊዜ በክርስትና ሃይማኖት ሥር አቆይቶታል።[8] የአክሱም የንግድ ግንኙነትና ቀይ ባሕርን ተሻግሮ ግዛት የመመሥረቱ ክስተት የወዳጅነት ትስስር ፈጥረው ለነበሩት ለባይዘንታይንና ለአክሱም መንግሥታት ወሳኝ ስትራቴጂ ነበር። በወቅቱ አዱሊስ የአክሱም የወጪና የገቢ ንግድ ማዕከል ሆና የአክሱም ነገሥታት በተለይ አጼ ካሌብ የመሠረቱት ግዙፍ የባሕር ኃይል የሚርመሰመስባት ወደብ ነበረች። በዚህ ዘመን አክሱም ላሳየችው እድገትና ሥልጣኔ መሠረት ከሆኑት ምክንያቶች አንዱም ምዕራባዊና ምሥራቃዊ የቀይ ባሕር ዳርቻዎችን መቆጣጠሯ ነበር። ነገር ግን የአጼ ካሌብ የደቡብ ዓረብ ቆይታ እንዲሁ ልሙጥ አልነበረም። አካባቢውን ለመቆጣጠር የሚሹ የተለያዩ ተቀናቃኝ ኃይሎች በተለይ ደግሞ ፋርሳውያን የአክሱምን ነገሥታት ወኪሎች በተደጋጋሚ ወግተዋል። የአካባቢው ሕዝብም ቀስ በቀስ በአክሱም ግዛት ላይ ተቃውሞውን አጠናክሮ በመጨረሻ ለፋርሳውያን የድረሱልን ጥሪ አድርጎ እ.አ.አ በ570 ዓ.ም. መልስ አግኝቶ በደቡብ ዓረብ የነበረው የአክሱም ግዛት ተንኮታኩቷል።[9] የአክሱም መንግሥት ምሥራቃዊ የቀይ ባሕር ዳርቻ ቁጥጥርም እንዲሁ አከተመ።

---

[6] Lewis, B. 2001. *The Middle East : 2000 Years of History from the Rise of Christianity to the Present Day*. Phoenix Press, p.45.

[7] ሀብተ ማርያም አሰፋ /ዶክተር/ ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባህሎች*፣ ገጽ 267.

[8] Armstrong, K. 1993. *Muhammed: a Biography of the Prophet*. Red Sea Press, p.56.

[9] ibid., p.56.

የአክሱም ግዛት በደቡብ ዓረብ የነበረው ቁጥጥር ባበቃበት ዓመተ ምሕረት ነብዩ መሐመድ ተወልደው ቀስ በቀስ የእስልምና ሃይማኖት ተስፋፍቶ በመጠናከሩ በአካባቢው አዲስ ተቀናቃኝ ኃይል ተፈጠረ። በመሆኑም በዋነኛነት በባይዘንታይንና በአክሱም እንዲሁም በፋርሳውያን ቁጥጥር ሥር የነበረው ቀይ ባሕር በእስልምና ሃይማኖትና ርዕዮት በሚመራው አዲስ ኃይል ቁጥጥር ሥር ዋለ። የዚህ ኃይል እንቅስቃሴ መነሻ ደቡብ ዓረብ ቢሆንም በፍጥነት ወደ ሌሎች የዓለም አካባቢዎች ተስፋፍቶ የአክሱምን መንግሥትም በተጽዕኖው ሥር ማሳደሩ አልቀረም። መጀመሪያው ላይ እስልምና መስፋፋት ሲጀምር ከሐበሻ መንግሥት ጋር መልካም ግንኙነት እንደነበረውና የነብዩ መሐመድ ተከታዮች ስሐባዎችም ወደ ሐበሻ ምድር ተሰደው ሲመጡ መልካም አቀባበል እንደተደረገላቸው በቅዱስ ቁርአን ተገልጿል። እንዲያውም የሐበሻ ምድር የጻድቃን ተብሎ ነብዩ መሐመድ «*ሐበሾች ካልነኳችሁ አትንኳቸው በማለት በእሷ /በሐበሻ/ ላይ ወታደር እንዳይዘምት*»[10] ብለው አዘዋል ይባላል።

በዚሁ ሁኔታ በአክሱም ግዛትና በዓረቡ ዓለም የነበረው ግንኙነት ለተወሰነ ጊዜ ሰላማዊ መስሎ ቆይቶ ውሎ አድሮ ግን የጥቅም ሽኩቻ ተከሰተ። በስምንተኛው ክፍለ ዘመን የእስልምና ሃይማኖት በመስፋፋት ላይ እያለ በርካታ የካሊፎች ማዕከላት ተቋቁመው ከምድረ ሐበሻ ጋር የሚደረገው የጥቅም ግጭት እጅጉን አየለ። የተለያዩ የታሪክ ማስረጃዎች እንደሚያመላክቱት በሶርያ የተቋቋመው የኡመሰይድ ካሊፌትና በኢራቅ የተቋቋመው የአቡሰይድ ካሊፌት በወቅቱ ኃያላን ወደ ነበሩት የባይዘንታይን፣ የፋርስና የአክሱም ግዛቶች ዘልቀው ገብተው ነበር። ይህን የእስልምናን መስፋፋት ለመግታትም የአክሱም መንግሥት በቀይ ባሕር ምሥራቃዊ ዳርቻ የሚገኙትን የሂጃዝንና የጅዳን ከተሞች ለመቆጣጠር ሙከራ ሲያደርግ ዓረቦች ሥጋት ላይ በመውደቃቸው ሱሌማን ኢብን ዓብደል ማሊክ የተባለው ካሊፍ ከደማስቆ ገሥግሦ መጥቶ እነዚህን ስትራቴጂያዊ ስፍራዎች አስለቅቆ ተቆጣጠረ። በመቀጠልም እ.አ.አ. በ702 ዓ.ም. ከአዱሊስ ወደብ በቅርብ ርቀት የሚገኙትን የዳህላክ ደሴቶችን በመቆጣጠር አክሱም ከውጪ ዓለም ጋራ የምታደርገው ግንኙነት እንዲቋረጥ አደረገ።[11] ዶክተር ሀብተ ማርያም አሰፋ በጻፉት መጽሐፍም «*የዓረብና የእስልምና ተከታዮች ኃይል በዚያን ጊዜ የነበሩትን ታላላቅ የክርስትያን መንግሥታት ባስጨነቁበት ጊዜ ኢትዮጵያም የጭንቁ ተካፋይ ሆነች። ስለሆነም በቀይ ባሕር የነበራትን የባሕር ኃይሏን፣ የባሕር ንግዷን፣ ወደቦቿን፣ ደሴቶቿን፣ በ7ኛውና በ8ኛው ክፍለ ዘመን ዓረቦች ድል መትተዋት ነጠቋት። ይህ ሁኔታ ለአክሱም ሥልጣኔ ውድቀት ተደራራቢና ተጨማሪ ምክንያት ሆነ።*»[12] ይላሉ።

ለአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ መዳከምና መውደቅ ሌላው ተጨማሪ ምክንያት በአክሱም ግዛቶች የተነሣው ከፍተኛ የሕዝብ ተቃውሞና ዓመፅ ነበር። በግዛቱ ይጣል የነበረው ከባድ ግብርና ሕዝቡ የክርስትና ሃይማኖትን በግዴታ እንዲቀበል መደረጉ ለዓመፅ እንደገፋፋ ይነገራል። በተለይ ቤጃዎችና አገዎች /ፈላሾች/ በተለያዩ ጊዜያት እንዳመፁና ለአክሱም ግዛት መዳከም አስተዋፅኦ እንዳደረጉ ታሪክ ይዘግባል[13]። ከሁሉም ይበልጥ ከአክሱም ግዛት በስተ ደቡብ ይኖሩ የነበሩት አገዎች ወይም ፈላሾች እጅግ ጠንካራ ተቃውሞ በማንሣት

---

[10] ብርሃኑ ተሾመ ከግል፣ ኢማም አሕመድ ኢብራሂም /አሕመድ ግራኝ/፣ ሚያዝያ 2000፣ አዲስ አበባ፣ ገጽ 32፤ Haggai, E. 1994. *Ethiopia and the Middle East*. Lynne Rienner Publishers Inc., p. 9.

[11] ibid., Haggai, p. 11.

[12] ዝኒ ከማሁ፣ ሀብተ ማርያም አሰፋ /ዶክተር/፣ ገጽ 270

[13] መስፍን ዘርአብሩክ፣ ካብ ኤርትራ ክሳብ ኢትዮጵያ ዛንታን ወለዶን /በአማርኛ ሲተረጎም፤ ከኤርትራ እስከ ኢትዮጵያ ታሪክና የዘር ሐረግ፣ ገጽ 27

የአክሱምን ሥልጣኔን ለውድቀት ዳርገውታል[14]። ይህ ሁሉ ተጨማምሮ የአክሱምን መንግሥት ሲፈርስ አቢሲንያ /ኢትዮጵያ/ ለዘመናት በጨለማ ውስጥ እንድትዳክር ምክንያት ሆነ።

2. የቱርኮችና የፖርቱጋሎች ሽኩቻ

ከአክሱም መንግሥት ውድቀት በኋላ የኢትዮጵያ የሥልጣን ማዕከል በመሆን የቀጠለው በቡግና አካባቢ የተመሠረተው የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ነበር። የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት በተወሰኑ መስኮች በሥነ ሕንጻና በሥነ ጽሑፍ ከፍተኛ እድገት አስመዝግቦ በዓለም ድንቅ የሚባሉትን የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስትያናት አፍርቷል። እነዚህ አስደናቂ ሥራዎች በጊዜው የነበረውን የዛጉዌዎች የመጠቀ ቴክኖሎጂ ሲያመለክቱ ረቂቅነታቸው አንዳንዶችን የመላእክት እንጂ የሰው ሥራ አይደሉም አሰኝቷቸዋል። ይህ ይሁን እንጂ የዛጉዌ ነገሥታት በውጭ ንግድና ግንኙነት ረገድ እንደ ቀዳሚው የአክሱም ሥርወ መንግሥት አይታወቁም።

«የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት እ.አ.አ. በ1270 ዓ.ም. አማርኛ ተናጋሪ በሆኑት አጼ ይኩኑ አምላክ ከተተካ በኋላ ንጉሠ የዘር ሐረጋቸውን ከንግሥት ሳባና ከንጉሥ ሰለሞንጋ አቆራኝተው ጥንታዊውን የአክሱም ንግሥና ዳግም እንዲያንሰራራ አደረጉ። አዲሶቹ ነገሥታት ግዛታቸውን ኢትዮጵያ በማለት ከሰየሙ በኋላ ባሕሩን ጭምር ያካተተውን የአክሱም የጥንት ግዛት ግዛታቸው እንደሆነ አውጀዋል። የኢትዮጵያ ነገሥታት ጠንክረው በወጡበት ወቅት ከሥራቸው ባሕረ ነጋሽ /የባሕር አስተዳዳሪ/ የተባሉ ወኪሎች በመሾም ሚናዊውን ክፍልና የባሕር ጠረፉን እንዲያስተዳድሩ የምጽዋን ወደብ በፍጹም ለሌላ ወገን አሳልፈው አልሰጡም ነበር።»[15]

የዓረቦችንና የባይዘንታይንን መዳከም ተከትሎ በአሥራ አራተኛው ክፍለ ዘመን ጠንክሮ የወጣውና እስልምናን መመሪያው ያደረገው የምዕራቡ ዓለም ተቀናቃኝ ኃይል ቱርክን ማዕከሉ ያደረገው የኦቶማን ኢምፓየር ነበር። የኦቶማን ነገሥታት በመካከለኛው ምሥራቅና በቀይ ባሕር የነበራቸውን ቁጥጥር በአብዛኛው ያራምዱ የነበረው በሰየሚቸው የግብጽ ፓሻዎችና ማምሉኮች አማካይነት ነበር። እነዚህ አስተዳዳሪዎች ከቀይ ባሕር በተጨማሪ የዓባይን ምንጭና ተፋሰስ ለመቆጣጠር ፍላጎት ስለነበራቸው ኢትዮጵያን ወደሚከተሉት የእስልምና ሃይማኖት ለመለወጥ ጥረት ያደርጉ ነበር። ይህን የረጅም ጊዜ ስትራቴጂያቸውንም ቀስ በቀስ በነጋዴዎች አማካይነት በመተግበር ከቀይ ባሕር በስተ ምዕራብ ያሉትን ዳርቻዎች አልፈው ወደ ሐረርና ይፋት በመዝለቅ ተጽዕኖቸውን አሳድረዋል።

ኢትዮጵያን ወደ እስልምና የመለወጡ ስትራቴጂያቸው ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር የነበራትን ቁጥጥር ከመግታት ባሻገር በጊዜው ይኪያሄድ ከነበረው የአውሮፓውያንና የዓረቦች የመስቀል ጦርነት ጋራም ሊያያይዙት ሞክረዋል። ኢትዮጵያ የክርስትናን ሃይማኖት ከተቀበለች ከአራተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ከባይዘንታይንጋ በአሌክሳንድርያ በኩል ግንኙነት እንደነበራት አውሮፓውያንም ይሁኑ ዓረቦች ያውቁ ነበር። በመሆኑም ከዓረቦች ጋራ በመስቀል ጦርነት የተጠመዱት አውሮፓውያን *Prester John* /ፕሬስተር ጆን/ ብለው ከሰየሙት የአፍሪካ ገናና የክርስትያን ንጉሥ ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ይሞክሩ ነበር።

---

[14] ዝኒ ከማሁ፣ ሀብተ ማሪያም አሰፋ /ዶክተር/፣ ገጽ 271-273

[15] Henze, *The Origins of Eritrea*, op. cit., p.5.

ከባይዘንታይን ኢምፓየር ውድቀት በኋላ እስልምናን የተቀበሉት አቶማን ቱርኮች ቀይ ባሕርን ተቆጣጥረው ስለነበር በአውሮፓ ጠንክረው የወጡት መንግሥታት ከሩቅ ምሥራቅ ጋራ የሚደረገውን የንግድ ግንኙነት ለመቀጠል ሲያስቡ በወቅቱ የንግድና የሃይማኖት ግንኙነቷን ለማስፋፋት ቆርጣ የተነሣችውም ፖርቱጋል ከፐሬስተር ጆን ጋራ ግንኙነት ለመፍጠር እ.አ.አ. በ1490ዎቹ በፋዘር ፍራንሲስኮ አልቫሬዝ የሚመራ ቡድን ልካ ነበር።[16] ይህ ወቅት አቶማን ቱርኮች ቀይ ባሕርን አጥብቀው የተቆጣጠሩበት ስለነበር ፖርቱጋል ከሩቅ ምሥራቅ ጋ በቀጥታ የሚያገናኛትን አማራጭ መሥመር ለመክፈትም በደቡብ አፍሪካ በኩል እነ ቫስኮ ዳጋማን አሰማርታ ነበር።

አውሮፓውያን የዓረቦችን የመስፋፋት እንቅስቃሴ መክተው የውስጥ እድገት ካስመዘገቡ በኋላ ከምሥራቁ ዓለም በተለይ ከህንድ ጋራ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር ሲሞክሩ ከኢትዮጵያ ነገሥታትጋ መልካም ግንኙነት ፈጥረው አገሪቱን በካቶሊክ ሃይማኖት ለማጥመቅ ይመኙ ነበር። በአጠቃላይ የአውሮፓውያንና የቱርኮች ፍጥጫ የኢትዮጵያን ሰላም፣ መረጋጋትና እድገት በእጅጉ ሲፈታተን ቆይቶ በመጨረሻ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን የተኪያሄደው የእርስበርስ ጦርነት አገራችንን እጅግ አዳክሟታል[17]።

እስልምና ወደ ኢትዮጵያና ወደ አጎራባቾቿ ከመስፋፋቱ በፊት የነበሩት አብዛኛዎቹ የውስጥ የሥልጣን ሽኩቻዎች ሃይማኖት ነክ አልነበሩም። ንግሥና ይገባኛል የሚልና ዘሩን ከሰለሞን ወይም ከዛጉዌ ሥርወ መንግሥት መዞ ለማውጣት የሚሞክር ሁሉ ሥልጣን ለመንጠቅ ሲጥር ቤተ ክርስትያን አንዱን ወይም ሌላውን ትደግፍ ነበር። በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን የተከሰተው ጦርነት ግን ክርስትናንና እስልምናን በሚከተሉ ኢትዮጵያውያን መኻል የተኪያሄደ ሲሆን ከወትሮው በተለየ ሁኔታ በጅሃድ መልክ ማዕከላዊ መንግሥቱን ለመቆጣጠር የተደረገ ሙከራ ነበር።

ከአጼ ልብነ ድንግል በፊት የነበሩ ነገሥታት በምሥራቅ ኢትዮጵያ ከነበሩት የሙስሊም ኤሚሬቶችጋ ተደጋጋሚ ውግያዎች ቢያኪያሂዱም በአጼ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት የተካሄደው ጦርነት ግን ለየት ያለ ነበር። ዘመኑ በዓለም ኃያልነቱን አረጋግጦ የነበረው የኦቶማን ግዛት ከግብጽ፣ ከሌሎች የዓረብ አካባቢዎችና ከቀይ ባሕር አልፎ በሐረርና በአዳል ኤሚሬቶች ላይ ተጽዕኖውን ያሳደረበትና አስፈላጊውን ወታደራዊና ቁሳቁሳዊ ድጋፍ ካሰባሰቡ በኋላ በአጼ ልብነ ድንግል መንግሥት ላይ ጦርነት የከፈቱበት ነበር። በዚህ በቱርኮች በከፍተኛ ደረጃ በተደገፈውና በታወቀው የጦር አበጋዝ አሕመድ ግራኝ /ኢማም አሕመድ ኢብራሂም/ መሪነት በተሰነዘረው የጀሃድ ጦርነት ከሸዋ ጀምሮ እስከአሁኗ ኤርትራ /የሐማሴን አካባቢ ድርስ ያለው/ ግዛት በቁጥጥር ሊውል ችሏል[18]።

በአብዛኛው የደጋ ሕዝብ አሕመድ ግራኝ ተብሎ የሚጠራው ኢማም አሕመድ ኢብራሒም በሸምብራ ኩሬና በሌሎች አካባቢዎች ወሳኝ ወታደራዊ ድሎችን ከተቀዳጀ በኋላ የያኔዋን ኢትዮጵያ ለአሥራ ዐምስት ዓመታት ያህል ገዝቷል። አሕመድ ግራኝን ለመደገፍ ከተለያዩ አገሮች በወዶ ዘማችነት የተሰለፉት ዓረቦችና በመድፈኝነትና በተኳሽነታቸው የሚታወቁት ቱርኮች በሠራዊቱ ውስጥ ከመሳተፋቸው ባሻገር የእስልምና ሃይማኖትን ለማስፋፋት ሞክረዋል። ሆኖም የአሕመድ ግራኝ አሥራ ዐምስት ዓመታት የግዛት ዘመን የሰላም ጊዜያት አልነበሩም። ከኤዛና ጀምሮ በክርስትና የቆዩት መሳፍንትና ሕዝቡ መጀመሪያ

---

[16] ibid., p.5.

[17] ይልማ ደሬሳ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ፣ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን፣ የመጀመሪያው ጎትም* 1959 ዓ.ም.፣ ሁለተኛው ጎትም 1999 ዓ.ም./ ዝኒ ከማሁ፣ *ኢማም አሕመድ ኢብራሂም*፣ ibid., *The Origins of Eritrea*, pp. 5-6.

[18] ibid., Henze. *The Origins of Eritrea*, p. 5.

በአጼ ልብነ ድንግል ከዚያም በእቴጌ ሰብለ ወንጌልና በልጃቸው በአጼ ገላውዲዎስ መሪነት በተለያዩ አካባቢዎች ግራኝን በመቃወም ብርቱ ውጊያዎች አኪያሂደዋል። የደጋው አቢሲንያ ሕዝብ የአሕመድ ግራኝን አገዛዝ እየተቃወመ በነበረበት ሁኔታ ቀይ ባሕርንና የሩቅ ምሥራቅን ለመቆጣጠርና የቱርክ ተቀናቃኞቿን ለመተካት ፍላጎት የነበራት ከዘመኑ የአውሮፓ ኃያላን አንዷ የነበረችው ፖርቱጋል ጦሯን ወደ ኢትዮጵያ አዘመተች።

ፖርቱጋሎች የቫስኮ ደጋማ ልጅ በነበረው በወጣቱ ክሪስቶፎሮ ደጋማ የሚመራ አንድ ሻለቃ ጦር ወደ ኢትዮጵያ የላኩበት ሁኔታ እጅግ አስገራሚ ነበር። አጼ ልብነ ድንግል በኢማም አሕመድ ኢብራሂም ከተሸነፉ በኋላ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች እየተዘዋወሩ ውግያዎችን ሲያካሂዱ ዓቅማቸው እየተዳከመ መሆኑን በመገንዘባቸው የውጭ ድጋፍ ለመሻት ወስነው ቀደም ሲል ከኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ከመሠረተችውና በአካባቢው ጂኦ ፖለቲካዊ ተጽዕኖ ለመፍጠር ትንቀሳቀስ ወደነበረችው ፖርቱጋል መልእክተኛ ሊልኩ ተዘጋጁ። ለዚህም በቤተ መንግሥታቸው የቅርብ አማካሪ የነበረውን ዶን ጃን በርሙዴዝ የተባለውን ፖርቱጋላዊ በ1527 ዓ.ም. ወደ ሮምና ወደ ሊዝበን ላኩት። ዶን በርሙዴዝ ሊዝበን ደርሶ ከንጉሡጋ ከተገናኘ በኋላ በ1531 ዓ.ም. በህንድ የፖርቱጋል እንደራሴ ለነበረው ዶን ጋርችያ ዳኖሮንሐ ንጉሡ ለኢትዮጵያ ረዳት ጦር እንዲልክ የሚያዘውን ደብዳቤ ይዞ ገባ። ሆኖም ደብዳቤው የተላከለት እንደራሴ ሞቶ ዶን ኤስቴቫኦ በተባለ እንደራሴ ተተክቶ ቆየው። አዲሱ እንደራሴም ሠራዊቱን ከፍሎ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ፈቃደኛ ባለመሆኑ የአጼ ልብነ ድንግል እርዳታ የመሻት ሙከራ ከንቱ ሆኖ ቀረ። ኑሮ ኑሮ ዶን ኤስቴቫኦ ከህንድ ተነሥቶ በቀይ ባሕር የነበረውን የቱርክ ጦር አጥቅቶ ምጽዋ አጠገብ የምትገኘውን ህርጊጎ የተባለችውን ወደብ ተቆጣጠረ። ጥቃቱን በመቀጠልም አሁን ስዌዝ ካናል ተብሎ እስከሚታወቀው አካባቢ ድረስ ተጉዞ ወደ ህርጊጎ ሲመለስ በቦታው ወታደሮቹ በአጼ ልብነ ድንግል መልእክተኛ ዶን በርሙዴዝ ተመርተው ኢትዮጵያን እንርዳ ብለው ወደሙበት። በዚህ ጊዜ አጼ ልብነ ድንግል ሞተው የነበር ቢሆንም ባለቤታቸው ንግሥት ሰብለ ወንጌል ባሕረ ነጋሽ ይስሐቅን እርዳታ እንዲጠይቅላቸው ወደ ዶን ኤስቴቫኦ ልከውት ነበር። የፖርቱጋል ወታደሮች ኢትዮጵያን ለመርዳት ከፍተኛ ፍላጎት ስለነበራቸውም ዶን ኤስቴቫኦ 400 ነፍጠኞችና 130 አሽከሮችን ወደ ኢትዮጵያ ላከ[19]።

ከፖርቱጋል የተላከው ጦር በቀይ ባሕር ከምትገኘው የምጽዋ ወደብ ተነሥቶ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ከተጓዘ በኋላ ከኢትዮጵያውያንጋ በመሆን በግራኝ ጦር ላይ ብርቱ ጥቃቶችን አኪያሂደ። ትግራይ ውስጥ በእምባ ሰነይቲ፣ በሠሓርቲና በእንደርታ አካባቢ በተኪያሂዱት ከባድ ውግያዎችም የግራኝ ጦር በእጅጉ ሊመናመን ቻለ። ግራኝ ሠራዊቱ እንደተዳከመ ተገንዝቦ ለማገገምና ከቱርኮች ተጨማሪ ድጋፍ ለማግኘት ሰሜን ወሎ ወደሚገኘው ዞብል አካባቢ ሄዶ ለወራት ከተቀመጠ በኋላ ተጨማሪ 2 ሺሕ ቱርኮችና ዓረቦች ተልከውለት[20] እንደገና የንግሥት ሰብለ ወንጌልንና የፖርቱጋሎችን ጦር ወፍላ ላይ መስከረም 2 ቀን 1535 ዓ.ም. ገጠመ። በዚህ ውግያ የፖርቱጋሎች መሪ የነበረውን ክሪስቶፎሬ ዳጋማን ማርኮ አንገቱን ሲቆርጠው የተቀረውን የንግሥቲቱን ጦር በታተነው[21]። የግራኝ ጦር ድል ቢቀዳጅም ሠራዊቱ እጅግ ተመናምኖ አካባቢውን ለቆ ጣና ዳር ወደሚገኘው ምሽጉ ተጓዘ።

የኢትዮጵያ ጦር ወፍላ ላይ ቢሸነፍም በፖርቱጋሎች ድጋፍ ከግራኝ ሠራዊት ቀድሞ ለማገገም በመቻሉ ግራኝን ተከታትሎ በጣና ዳርቻ እንፍራዝ አካባቢ በምትገኘው ዛንታር

[19] ዝኒ ከማሁ፣ ይልማ ደሬሳ፣ ገጽ 147-148
[20] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 187
[21] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 199

በር ላይ የካቲት 28 ቀን 1535 ዓ.ም. የመጨረሻውን ፍልሚያ አኪያሂዶ ሲገድለው ተከታዮቹ ተበታተኑ።[22] የግራኝ ባለቤት ድል ወንበራም በጦርነቱ የተዘረፈውን ሀብት ይዛ ወደ ሐረር አፈገፈገች። እንዲሀም ቱርኮችና በጦርነቱ በተዋጊነትና በሃይማኖት ሰባኪነት የተሳተፉት ዓረቦች በኢትዮጵያ ላይ ሊያሳድሩት የፈለጉት ተጽዕኖ መከነባቸው። ከአሕመድ ግራኝ ሽንፈት በኋላም አውሮፓውያንም ሆኑ ዓረቦች ስትራቴጂያዊውን የቀይ ባሕር ዳርቻና ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር መከጀላቸው አልቀረም። ፖርቱጋሎችና ሌሎች አውሮፓውያን ኢትዮጵያን በካቶሊክ ሃይማኖት ለማጥመቅ ሲሞክሩ፣ ቱርኮችና ሌሎች የዓረብ አገሮችም ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር መጣራቸው ቀጠሉ።

ኢትዮጵያ ከግራኝ ወረራ በኋላ እጅግ ተዳከማ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ማቋቋም ተስኗት ነበር። ያከማቸው ሀብት የተዘረፈበትና ሠራዊቱ የተበታተነበት የሐበሻው መንግሥት እንኳንስ የውጭ ወራሪን ከውስጥ ሊነሣ የሚችለውን ተቃውሞም ለመመከት ዓቅም ዐጣ። ይህን የአቢሲኒያ ነገሥታትን መዳከም ቱርኮችና የአዳል ሱልጣኔቶች ተገንዝበው ግራኝን በመተካት የተመረጠውን ኑር ኢብን አልዋዝርን እያገዙ ዳግም አጼ ገላውዲዎስን ገጥሞ ፈጠጋር ላይ እንዲገድላቸው ረድተዋል።[23] ሆኖም በአሥራ ዐምስት ዓመቱ ጦርነት የተዳከሙት የሐበሻ ነገሥታት ብቻ ሳይሆኑ ደጋውን የሐበሻ ክፍል ለመቆጣጠር ዓቅም ያጡት ኤሚሬቶችም ነበሩ። ይህን ሁኔታ በጥሞና ይከታተሉ የነበሩት ኦሮሞዎች ይዞታቸውንና ተጽዕኗቸውን በማስፋፋት ከደቡብ የአገሪቱ ክፍል ተነሥተው በምችሌ ገዳ መሪነት በገላውዲዎስ ላይ ድል የተቀዳጀውን የአሊ ኑርን ሠራዊት በሐዚሎ ጦርነት[24] ድል አደረጉ። በአንድ በኩል የአዳል ሱልጣኔቶችና የሐበሻ ነገሥታት መዳከም በሌላ በኩል ደግሞ የኦሮሞዎች መጠናከር በአካባቢው አዲስ ክስተትን አስከተለ። በታሪክ የኦሮሞች የመስፋፋት እንቅስቃሴ በከረዩ፣ በሜጫ፣ በቱለማ፣ እንዲሁም በወሎ የሚመሩ የኦሮሞ ጎሳዎች በሰሜን እስከ ራያና ጎጃም፣ በምሥራቅ እስከ ሐረርጌ፣ በምዕራብ እስከ ከፋና ዳሞት በመዝለቅ ሰፊ ግዛትን ሊቆጣጠሩ ችለዋል። ይህ ክስተትም በአገሪቱ ሕዝቦች የአኗኗር ስብጥር፣ የአስተዳደር ዘይቤ፣ ባህልና ቋንቋ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል።

ኦሮሞዎች በሰሜን ምሥራቅ የአገሪቱ ክፍል ወሎን ጨምሮ ትግራይ ውስጥ እስከ ራያ ዓዘቦና ዋጀራት ድረስ፣ በሰሜን ምዕራብ በኩል ደግሞ ዓባይን አቋርጠው እስከ ጎጃም ድረስ በምዕራብ በኩል ጊቤን ተሻግረው ያኔ ኢናርያና የጊቤ መንግሥታት ይባል የነበረው የአሁኖቹን ጅማ፣ ኢሉባቦርና ወለጋን የሚያጠቃልለውን አካባቢ ተቆጣጥረዋል። በምሥራቅ በኩልም አሁን ምሥራቅ ሐረርጌ ተብሎ እስከሚጠራው አካባቢ ዘልቀዋል። በአጠቃላይ በሁሉም የኢትዮጵያ አቅጣጫዎች ከመንቀሳቀሳቸውና ከመስፈራቸው ባሻገር[25] ተዳክመው በነበሩት የአቢሲኒያ ነገሥታትና ከሸዋ ወደ ጎንደር ባፈገፈገው የመንግሥት ማዕከል ላይ ተጽዕኗቸውን አሳድረዋል። በተንቀሳቀሱበት ሁሉ ቋንቋቸውና ባህላቸውን በማስፋፋታቸው ዛሬም ከአሮሚያ ክልል ውጭ በርካታ አሮምኛ ተናጋሪዎች ይገኛሉ። በአማራው ክልል በወሎና በጎጃም አሮምኛ ተናጋሪዎች እንዳሉ ሁሉ ትግራይ ውስጥም በራያ ዓዘቦ አካባቢ አሮምኛ ተናጋሪዎች አይታጡም።

---

[22] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ*፣ እንደገና በ2000 ዓ.ም. የታተመ፣ አዲስ አበባ፣ ገጽ 60.

[23] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 232፣ Mohammed Hassen. 1990. *The Oromo of Ethiopia: A History 1570-1860.* Red Sea Press, p. 25.

[24] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 233

[25] የኦሮሞዎች የአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን እንቅስቃሴ «*የኢትዮጵያ ታሪክ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን*» በሚለውና '*The Oromo of Ethiopia*' በተባሉት የታሪክ መጻሕፍት በስፋት ተገልጿል።

3. ከዘመነ መሳፍንት እስከ አጼ ምኒልክ፣ የኤርትራ መፈጠር

ከአሮሞዎች መስፋፋት በኋላ በኢትዮጵያ ጎልቶ የሚታወቀው እስከ አሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ማብቅያ ድረስ ማዕከሉን ጎንደር ያደረገው የጎንደር ሥርወ መንግሥት ነበር። ከአሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ማብቅያ ጀምሮ ግን ኢትዮጵያ ውስጥ በታሪክ «ዘመነ መሳፍንት» ተብሎ የሚታወቀውና የማዕከሉ ጥንካሬ ተዳክሞ በጎጃም፣ በጎንደር፣ በወሎ፣ በትግራይና በሸዋ እጅግ ጠንካራ መሳፍንት ብቅ ያሉበት ዘመን መጣ። በዚህ ዘመን የትግራይ መሳፍንትና የየጁ አሮሞዎች በጎንደር ቤተ መንግሥት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድረው ነበር። ራስ ስሑል ሚካኤል የተባሉት የትግራይ መስፍን በጎንደር ቤተ መንግሥት «አንጋሽ» ሆነው ለዓመታት ሲቆዩ የየጁ አሮሞዎችም በዚህ ቤተ መንግሥት ንግሥናውን ተጋርተው ነበር። በዚሁ የጎንደር ሥርወ መንግሥት ላይ አሮሞዎች ከፍተኛ ተጽዕኖ ማሳደራቸውንና በስተ መጨረሻውም የወሎ፣ በተለይ የየጁ፣ አሮሞዎች ነገሥታቱን መቆጣጠራቸውን ታሪክ ይመሰክራል።[26] በዚህ ዘመን የነገሠው የእያሱ ብርሃን ሰገድ ልጅ እያአስ እናት ወይዘሮ ውቢት የየጁ አሮሞ ተወላጅ በመሆናቸው ተከትሏቸው ወደ አካባቢው የመጡት በርካታ አሮሞዎች ጎንደርን ወደ አሮምኛ ተናጋሪነት ለውጠውት ነበር ይባላል። በጎንደር ሥርወ መንግሥት ማብቅያ ገደማ ጎንደርን ይመራ የነበረው ራስ ዓሊ ጓንጉልም የአሮሞ ተወላጅ ነበር። በዚህ ዘመን ጠንካራ ማዕከል በመጥፋቱ ለውጭ ግንኙነት ያለው ትኩረት ቢቀዘቅዝም የየአካባቢው መሳፍንቱ የቀይ ባሕርን ወደቦች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚቆጣጠሩበትና የወጪና የገቢ ንግድ በማካሄድ ኃይላቸውን የሚያደልቡበት ሁኔታ ነበር።

የኢትዮጵያ ነገሥታት ተዳክመው ተቀናቃኝ መሳፍንት ክንዳቸው አፈርጥመው በእርስ በእርስ ጦርነት በተጠመዱበት ዘመን አጼ ቴዎድሮስ በርካታ መሳፍንትንና ተቃናቃኞችን አሸንፈው ደርስጌ ማርያም ላይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ዘውድ ጫኑ።[27] ሆኖም በግዛታቸው የሚነሣው ዐመፅ ማባሪያ አጥቶ በተለይም የወሎ፣ የጎጃም፣ የትግራይ፣ የሸዋ መሳፍንት ተነሥተውባቸው ላፍታ ዕረፍት አላጣቸው። የአጼ ቴዎድሮስ አንድ ሕልም ኢትዮጵያን ከውጭ ጥቃት ሊከላከል የሚችል ጠንካራ ቋሚ ጦር እንዲኖራት ማድረግ ነበር። ይህን ሕልማቸውን ለማሳካት የቆየውን የግብርና የመሬት ይዞታ መለወጥና ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ማቋቋም የግድ ይል ነበር። ሆኖም የአጼ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ዘመናዊ የማድረግና የማሠልጠኑ ራዕይ በተለይ በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ በነበራቸው በቤተመንግሥት በቤተክህነትና በአካባቢው መሳፍንት ተቀባይነት አላገኘም ነበር።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አጼ ቴዎድሮስ ከእንግሊዞች ጋራ በዲፕሎማሲያዊ እሰጥ አገባ ምክንያት ጦርነት ውስጥ ሲዘፈቁ ተቀናቃኞቻቸውም ሕዝቡም ሳይደግፋቸው ቀረ። በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ፖል ሄንዚ ሲገልጸው «የናፕዬር ጦር አስቸጋሪውን የዛታ ሸለቆ ለማለፍ ሲንደፋደፍ ሌሎች ጠላቶቻቸው ማለትም የሰሜኑ ዋግ ሹም ጎበዜ፣ የወሎ አሮሞዎችና የሸዋው ምኒልክ እየተሰባሰቡ መሆናቸውን ቴዎድሮስ ተገነዘቡ፣» ብሎ «ናፕዬር ትግራይን ሲያቋርጥ የደጃዝማች ካሳ ምርጫ ትብብርን አግኝቷል..... ጎበዜም በግዛቱ ይደረግ ለነበረው የእንግሊዞች እንቅስቃሴ ሞቅ ያለ ድጋፍ ባይሰጥም አልተቃወመውም ነበር።» ይላል።[28]

---

[26] Bahru Zewde. 2002. *A History of Modern Ethiopia: 1855-1991.* Addis Ababa University Press, Second Edition 2002, Reprinted 2005, 2007, pp.11-12.

[27] ibid., p. 30.

[28] Henze. *Layers of Time*, op.cit. p.140.

ብዙ ታሪክ ጸሐፊዎች እንደሚሉት አጼ ቴዎድሮስን ዘመናዊና ቋሚ ጦር ለመገንባት ካነሣሷቸው ምክንያቶች አንዱ የግብጽ ወታደራዊ እድገት የፈጠረባቸው ሥጋት ነበር። በወቅቱ ግብጾች በንጉሥ መሐመድ ዓሊ እየተመሩ ዘመናዊና ቋሚ ጦር መሥርተው የዛሬዎቹን ግብጽና ሱዳንን የሚያካትተውንና ኢትዮጵያን የሚዋሰነውን የአንግሎ-ኤጂፕሺያን ግዛት ለማጠናከር ይንቀሳቀሱ ነበር። ለዚህም እንቅስቃሴያቸው ዋነኛው ምክንያት የዓባይን ተፋሰስ በአስተማማኝ ሁኔታ መቆጣጠርና የቀይ ባሕር ይዞታቸውን ማጠናከር ነበር። ከዚያ ዘመን ጀምሮ የግብጽ ፖሊሲ ምሰሶዎች ዓባይንና ቀይ ባሕርን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መቆጣጠር ስለነበር በኢትዮጵያ ህልውና ላይ ሥጋት ማሳደሩ አልቀረም። አጼ ቴዎድሮስ ግብጻውያንና ቱርኮች ሥጋት ያሳደሩባቸው ገና ሽፍታ እያሉ እ.አ.አ በ1848 ዓ.ም. ደባርቅ ላይ ከነዚህ ባላንጣዎቻቸውጋ ውግያ ገጥመው ሽንፈት ከደረሰባቸው ጊዜ ጀምሮ ነበር።[29] አጼ ቴዎድሮስ ከሽንፈታቸው የወሰዱት ትልቅ ትምህርት በኢትዮጵያ በአስቸኳይ ዘመናዊ ጦር ካሳደራጁ በስተቀር እንኳንስ ሲያልሙት እንደነበረው ኢየሩሳሌምን ከቱርኮች ይዞታ ነጻ ማውጣትና በአገራቸው ሊደርስ የሚችለውን ጥቃት ለመመከት እንደማይችሉ ነበር። ሆኖም የአጼ ቴዎድሮስ ሕልም በአገሬው ብርቱ ተቃውሞ ስላጋጠመው እውን ሳይሆን ቀረ።

አጼ ቴዎድሮስ በ1860 ዓ.ም. መቅደላ ላይ ሕይወታቸው ካለፈ በኋላ የቀጠለው የሥልጣን ሽኩቻ በላስታው ዋግ ሹም ጎበዜ ወይም አጼ ተክለ ጊዎርጊስና በትግራዩ በዝብዝ ካሳ ወይም አጼ ዮሐንስ መካከል ነበር። ለጊዜው የበላይነት ተቀዳጅተው የነገሡት ዋግ ሹም ጎበዜ ቢሆኑም የሥልጣን ዘመናቸው እጅግ አጭር ሆኖ በነገሡ በሦስተኛ ዓመታቸው ሰኔ 1863 ዓ.ም. ላይ በአጼ ተክለ ጊዎርጊስና በአጼ ዮሐንስ መኻል ዓድዋ ላይ በተደረገው ጦርነት አጼ ተክለ ጊዎርጊስ ተማርከው[30] አጼ ዮሐንስ አራተኛው በትረ ሥልጣኑን ተቆጣጠሩ።

አጼ ዮሐንስ ልክ እንደ አጼ ቴዎድሮስ አንገብጋቢ የሆኑ የውስጥና የውጭ ችግሮች ተደቅነውባቸው ከውስጥ የጎጃምና የሸዋ ነገሥታት ዐመፅ ከውጭ ደግሞ የግብጾች፣ የጣልያኖችና የድርቡሾች ትንኮሳዎችና ጥቃቶች ተጠናክረውባቸው ነበር። በአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት እ.አ.አ በ1885 ዓ.ም. ኃያላኑ የአውሮፓ መንግሥታት አፍሪካን ለመቀራመት ስምምነት ያደረጉበት የበርሊን ኮንፈረንስ ተኪያሄደ። በኮንፈረንሱ ቀደም ብለው በአፍሪካ ግዛታቸውን በማስፋፋት ላይ የነበሩት እነ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ፖርቱጋል እንዲሁም አዲስ ግዛት ለመቀራመት የከጀሉት እነ ጀርመንን የመሳሰሉት አገሮች ሲሳተፉ ኢትዮጵያም ለቅኝ ግዛትነት ከታጩትና በተለይ እንግሊዞችና ጣልያኖች ዓይናቸውን ከጣሉባቸው አገሮች አንዷ ነበረች። በመሆኑም ኃያላኑ በቀይ ባሕር በኩል ይዞታቸውን ለማጠናከር በጋራ ከተንቀሳቀሱ በኋላ ጣልያኖች ፕሮጄክቱን በብቸኝነት ይዘውት የኢትዮጵያ የባሕር መውጫና መግብያ በሆኑት በምጽዋና በዓሰብ አካባቢ ይዞታቸውን ለማጠናከር ሲሞክሩ ከአጼ ዮሐንስ ጋራ በተከታታይ መጋጨታቸው አልቀረም።

በአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ሌላው የተከሰተው ችግር የግብጾች የቱርኮች ወራሽ ነን በማለት ቀይ ባሕርንና ኤርትራን ዐልፎም ኢትዮጵያንና የዓባይን ተፋሰስ በአጠቃላይ ለመቆጣጠር ቀደም ሲል መሐመድ ዓሊ የጀመረውን ፕሮጄክት በልጅ ልጁ በኢስማኤል ኬሕዲቭ በኩል መቀጠላቸው ነው። የኢስማኤል ኬሕዲቭን ዕቅድ በተመለከተ አቶ ገብረ ጻዲቅ ደገፉ «ናይል» በሚለው መጽሐፋቸው ሲናገሩ፤ «ኢስማኤል መላውን የናይል ተፋሰስ

[29] Bahru Zewde, op. cit., p.28.
[30] ibid., p.145.

በመቀላቀል ናይልን የግብጻውያን ወንዝ ለማድረግ ነበር ፍላጎቱ። በዚህም ታላቋን ግብጽ መፍጠር ማለት ነው። ይህንና ሌሎች ፖለቲካዊ ዓላማዎቹን ለማስፈጸም በርካታ የውጭ አገር ቅጥረኞችን በመጠቀም ተከታታይ ዘመቻዎችን አካሄደ»[31] ይላሉ። ኤርሊክ ሃጋይ የተባለው ጸሐፊም በተመሳሳይ «*እንደ ድዌን አገላለጽ የኢስማኤል ሕልም ናይልን የግብጽ ወንዝ ማድረግና በተፋሰሱ ያሉትን አካባቢዎች ሁሉ ወደ ግዛቱ ማቀላቀል....የግብጽን ግዛት እስከ ኤኳቶርያል ሐይቆች፣ እስከ ህንድ ውቅያኖስ ዳርቻና የጥቁሮች ንግሥና ግዛት እስከነበረችው ቻድ ድረስ ማስፋት ነበር። ሆኖም የመጀመሪያው እርምጃው የቀይ ባሕር ወደቦችን በተለይ ምጽዋን ከሱዳንጋ ማገናኘት ነበር*»[32] ይላል።

እንደተባለውም ኢስማኤል ኬሕዲቭ በነገሠ በአራተኛው ዓመት ማለትም እ.አ.አ. በ1867 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ግዛት ሥር የነበሩትን ስዋኪንና ምጽዋን ተቆጣጠረ፤[33] ወደ አገር ውስጥ ዘልቆም መንላዕንና ጊንዳዕን፣ ብዙ ሳይቆይም ደጋውን ሐማሴን ተቆጣጠረ። አጼ ዮሐንስ የኬሕዲቭን ወረራ ለማስቆም የአውሮፓ መንግሥታትን ቢማጸኑም ሰሚ ባለማግኘታቸው ግብጻውያን ወደ መኻል ገሥግሠው ከአጼ ዮሐንስ ጋራ በ1867 ዓ.ም. በመረብ ወንዝ ዳርቻ ጉንደት ላይ በ1868 ዓ.ም. ደግሞ ጉራዕ ላይ ገጥመው ተሸነፉ። በእነዚህ ጦርነቶች ግብጾች ኢትዮጵያ በቀይ ባሕርና በዓባይ ላይ ቁጥጥር እንዳይኖራት ብዛት ያለው የሠለጠነ ሠራዊትና የአሜሪካንና የስዊስ ቅጥረኛ ወታደሮችና መኮንኖች አሰማርተው ነበር[34]። ሆኖም ጦርነቶቹ በአጼ ዮሐንስ አሸናፊነት በመቋጨታቸው ግብጾች ሊከፍሉት እማይችሉት ዕዳ ውስጥ ተዘፍቀው አገራቸውንና ግዛታቸውን ለባለ ዕዳዋ ለእንግሊዝ አሳልፈው ለመስጠት ተገደዱ። እንግሊዞችም የግብጾችን ግዛት በመረከብ ላይ ሳሉ በቅኝ ግዛታቸው ሥር የነበሩት ሱዳኖች የነጻነት እንቅስቃሴያቸውን አፋፍመው ማሕዲስቶችና ድርቡሾች በገዥው የግብጽ ሠራዊት ላይ ከባድና ሰፊ ጥቃት ሰነዘሩ። በዚህ አጋጣሚ በግብጽና በሱዳን ከፍተኛ የጥጥ እርሻ በማስፋፋት ለጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪዋ አስተማማኝ አቅርቦት ለማረጋገጥ ትሻ የነበረችው እንግሊዝ በራሷ ሠራዊት ሳይሆን በኢትዮጵያ ሠራዊት ተጠቅማ በድርቡሾች የተከበበውን የግብጽ ሠራዊት ለማዳን ተንቀሳቀሰች። ይህን ዕቅዷን ለማሳካትም እ.አ.አ. በ1884 ዓ.ም በሰር ዊልያም ሔዉት የሚመራ የእንግሊዝ የልኡካን ቡድን ዓድዋ ላይ ከአጼ ዮሐንስጋ እንዲገናኝ አድርጋ ኢትዮጵያ በከሰላ የተከበቡትን የግብጽ ሠራዊት አባላት ካስለቀቀች ለውለታዋ በግብጾች ቀጥጥር ሥር የነበረውን የቦጎስና የከረንን አካባቢ እንድትወስድና የምጽዋን ወደብ ያለምንም ቀረጥና ገደብ እንድትጠቀም ስምምነት ላይ ተደረሰ[35]።

ከዚህ ተከትሎም የኢትዮጵያ ሠራዊት የመረብ ምላሽ[36] አስተዳዳሪና የአጼ ዮሐንስ ታዋቂ ጀኔራል በነበሩት በራስ አሉላ አባነጋ አዛዥነት በኩፊትና በከሰላ ተዋግቶ የግብጽን ጦር ከድርቡሾች ከበባ ነጻ አወጣ። ሆኖም እንግሊዝ የበርሊኑ የቅኝ ግዛት ስምምነት ፈራሚ ከመሆኗም ባሻገር ኢትዮጵያ የከረንን አካባቢ እንድትቆጣጠርና ወደ ቀይ ባሕር ዘልቃ የወደብ ተጠቃሚ እንድትሆን ፍላጎት ስላልነበራት ግዛቱን ለኢጣልያ አሳልፋ ሰጠች። ኢትዮጵያም በአንድ በኩል በእንግሊዞች ሸር ከድርቡሾችጋ ደም ተቃብታ በሌላ በኩል

---

31 ገብረ ጻድቅ ደገፉ. 2005. *ናይል፣ ታሪካዊ ሕጋዊና ልማታዊ ገጽታዎች፣ ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ማስጠንቀቂያ፣ በእንግሊዝኛ Nile: Historical, Legal and Developmental Perspectives* በሚል እ.አ.አ. በ2003 ዓ.ም. በቪክቶርያ ካናዳ ታትሞ በ2005 ዓ.ም. በወርቁ ሽፈራው ወደ አማርኛ የተተረጎመ፣ ገጽ 69

32 Haggai, E. 1986. *Ethiopia and the Challenge of Independence.* Lynne Rienner Publishers, p.19.

33 Henze. *Layers of Time,* op. cit., pp. 146-147.

34 ibid., p.147.

35 ibid., pp.155-156.

36 መረብ ምላሽ ማለት መረብን ወሰን በማድረግ ከትግራይ በስተሰሜን ያለውን አሁን ኤርትራ የሚባለውን አካባቢ የሚያመለክት ሲሆን የቀይ ባሕር ወደቦችንም የሚያካትት ነው።

ደግሞ ከኢጣልያ ቅኝ ገዥዎች ጋራ በማያባራ ሽኩቻ ውስጥ ተዘፍቃ ለረጅም ጊዜ የቀይ ባሕርና የመረብ ምላሽ ግዛቷን አጣች።

በዚህ መሠረት እ.አ.አ. በ1885 ዓ.ም. የካቲት ወር ላይ የኢጣልያ ሰንደቅ ዓላማ ምጽዋ ወደብ ላይ ተውለበለበ። እንግሊዞችም በስፍራው የነበረው የግብጽ ኃይል እንዲለቅ አደረጉ። ጣልያኖች ምጽዋን ማግኘታቸው ሳይበቃቸው ይዞታቸውን ወደ ቀይ ባሕር ደቡባዊ ክፍልና ከወደቡ ገባ ብለው ባሉ የኢትዮጵያ ግዛቶች አስፋፉ። ሰሃጢ በተባለው ስፍራ የመሸገው የጣልያኖች ኃይልም ከራስ አሉላ ሠራዊት ጋራ በተደጋጋሚ ተጋጭቶ በመጨረሻ ራስ አሉላ ይህን ኃይልና ሊረዳው ከምጽዋ የተንቀሳቀሰውን አንድ ሻለቃ ጦር ዶጋሊ ላይ በ1879 ዓ.ም. ደመሰሱ።[37]

ከጣልያኖችጋ ለመደራደር ሲሞክሩ የነበሩት አጼ ዮሐንስ ይህን የራስ አሉላን ድርጊት አልወደዱትም ነበር። እንግሊዞችም በአጼ ዮሐንስና በጣልያኖች መኻል ጦርነት እንዳይቀሰቀስ ሥጋት ስላደረባቸው በካይሮ የነበረውን ዲፕሎማታቸውን ጄራልድ ፖርታልን አጼ ዮሐንስ ዘንድ ልከው አሉላ ዶጋሊ ላይ ለፈጸሙት ጥቃት ጣልያኖችን ይቅርታ እንዲጠይቁና ከመረብ ምላሽ አስተዳዳሪነታቸው እንዲነሡ ጠየቁ። ሆኖም አጼ ዮሐንስ «*አሉላ ጥፋት አላጠፋም፤ ሐበሾች እንግሊዝ አገር ድረስ ሄደው ጥቃት ቢያኪያሂዱ እንደምትዋጓቸው ሁሉ፤ እሱም ግዛቱ ድረስ ዘልቀው የገቡትን ጣልያኖች ተዋግቷል፤*»[38] ብለው መለሱላቸው።

ሰር ፖርታል አጼ ዮሐንስን ትግራይ ሄዶ ለማግባባት እየሞከረ ሳለ ጣልያኖች ከኻያ ሺሕ በላይ ጦር ምጽዋ ላይ አፍሰው ሁለት ብርጌዶችን ወደ ዶጋሊ አንቀሳቀሱ። አጼ ዮሐንስና አሉላም ጣልያኖችን ለመግጠም በርካታ የኢትዮጵያ ራሶችንና ሠራዊታቸውን አሰባሰቡ። በተጨማሪም በንጉሥ ሚካኤል የሚመሩ 25 ሺሕ የኦሮሞ ፈረሰኞች ትግራይ ደረሱ። አጼ ዮሐንስ ከጣልያኖች ጋራ ጦርነት ለመግጠም በዝግጅት ላይ እያሉ ማሕዲስቶች ደምቢያ ላይ ሳር ውሃ በተባለ ስፍራ ንጉሥ ተክለሃይማኖትን ገጥመው ማሸነፋቸው ተሰማ። አጼ ዮሐንስ ይህን ዜና እንደሰሙ ጣልያኖችን ለመግጠም የነበራቸውን ዕቅድ ሠረዙ፤ አሉላም መጀመሪያ በቆላው የመረብ ምላሽ አካባቢ የነበረውን ሠራዊታቸውን አስወጡ፤ ቀጥለውም እ.አ.አ. በየካቲት 1888 ዓ.ም. አሥመራን ለቀው ወደ ዓድዋ አፈገፈጉ። እንዲህም ጣልያኖች ሳይዋጉ መረብ ምላሽን ለመቆጣጠር ቻሉ።

በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የነበረው ሁኔታ ይህ ሆኖ ሳለ፤ በመኻል አገር ደግሞ ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለሃይማኖት በአጼ ዮሐንስ አንገዛም በማለታቸው አጼ ዮሐንስ ራስ አሉላን አስከትለው ጎጃምንና ሸዋን ለመቅጣት ተንቀሳቀሱ። ሆኖም አጼ ዮሐንስ ጎጃምን ክፉኛ ቢቀጡም ንጉሥ ምኒልክ ሕዝቡን አደራጅተው መዘጋጀታቸውንና ከጣልያኖች የጦር መሣሪያ ድጋፍ ማግኘታቸውን ሲያውቁ ሸዋን ለማጥቃት የነበራቸውን ዕቅድ ሠረዙ። በሌላ በኩል ማሕዲስቶች በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ለመፈጸም መተማ ላይ ኃይላቸውን አሰባስበው ስለነበር አጼ ዮሐንስ ወደ መተማ አምርተው ከድርቡሾች ጋራ ሲዋጉ መጋቢት 1881 ዓ.ም. ላይ ሕይወታቸው ዐለፈ። ይህ እንደ ሆነም ጣልያኖች በቀይ ባሕርና በመረብ ምላሽ የነበራቸውን ይዞታ ይበልጥ አስፋፍተው ኢትዮጵያን የባሕር በር ባለቤትነት አሳጧት። እንግሊዝም የግብጽና የሱዳን ቅኝ ግዛቷን አጠናክራ የፈለገ ግዮን ወይም የዓባይ ወንዝ ዋነኛ ተጠቃሚና ወሳኝ ኃይል ለመሆን በቃች።

---

[37] በላይ ግደይ፤ ኢትዮጵያ አገሬና ትዝታዬ፣ 1990 ዓ.ም.፣ ገጽ 10

[38] Henze. *Layers of Time*, op.cit., p.158.

ከአጼ ዮሐንስ ዕልፈት በኋላ በአካባቢው የነበረው የኃይል ሚዛን ተለወጠ። የንጉሠ ነገሥቱ ዋና ተቀናቃኝ የነበሩት አጼ ምኒልክ ከድርቡሾች ጋራ ባለመዋጋታቸውና ከጣልያኖች የጦር መሣሪያ ድጋፍ በማግኘታቸው ኃይላቸውን አጠናክረው ከሁሉም በላይ በርትተው ብቅ አሉ። አጼ ምኒልክ፣ አጼ ዮሐንስ ከመሞታቸውም በፊት ቢሆን፣ በትረ ሥልጣኑን ለመጨበጥ ከፍተኛ ፍላጎት ስለነበራቸው ኃይላቸውን እያጠናከሩና ከውጭ መንግሥታት ጋራ የዲፕሎማሲ ግንኙነት እያዳበሩ ቆይተው ነበር። የውጫሌው ውል ተደራዳሪና ፈራሚ የነበረው ጣልያናዊ ካውንት ፔትሮ አንቶኔሊ እንደሚለው እ.አ.አ. በ1887 ዓ.ም. ምኒልክ 196,000 ሠራዊት፤ አጼ ዮሐንስ እንደሞቱም 130,000 የወሎ ጦር አባላት ነበሯቸው።[39] አጼ ዮሐንስ አልጋቸውን ለራስ መንገሻ ዮሐንስ ቢያወርሱም ሠራዊታቸው መተማ ጦርነት ላይ ተበታትኖ እጅግ ተዳክመው ነበር። የወሎው ንጉሥ ሚካኤልና የጎጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም የአጼ ምኒልክን ያህል ኃይል አልነበራቸውም ስለሆነም በትረ ሥልጣኑን የሚይዙት ምኒልክ እንደሚሆኑ ግልጽ ነበር።

አጼ ምኒልክ ሥልጣን ሲይዙ ከአገር ውስጥ ከባድ ጫና ባይገጥማቸውም የውጭ ኃይሎች ያሳድሩባቸው የነበረው ተጽዕኖ ግን ቀላል አልነበረም። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ጣልያኖች ከኢንግሊዞችጋ ተስማምተው ከመተማ ጦርነት በፊት እ.አ.አ. በ1882 ዓ.ም. ዓሰብን፣ ከሦስት ዓመት በኋላ ደግሞ ምጽዋን ተቆጣጥረው ነበር። ጣልያኖች ለአዲሶቹ ይዞታዎቻቸው ዕውቅና ለማግኘት ከአጼ ዮሐንስና ከአጼ ምኒልክ ጋራ በተደጋጋሚ ለመደራደር ቢሞክሩም አጼ ዮሐንስ ከእንግሊዛዊው ከሰር ሔወት ጋራ የተደረሰውን የኢትዮጵያን በቀይ ባሕር የመጠቀም መብት ከሚያስጠብቀው ውል በስተቀር ሌላ ስምምነት እንደማይቀበሉ ገልጸውላቸው ነበር። ጣልያኖች በተለይ ከአጼ ዮሐንስ ጋራ መስማማት አቅቷቸው ጦርነት እንደሚገጥሟቸው ከገመቱ በኋላ ምኒልክ ወደ ዮሐንስ ካልወገኑና ገለልተኛ ሆነው የቀረበላቸውን የሰምምነት ሰነድ ከተቀበሉ 5000 ሬሚንግተን ጠመንጃዎችን እንደሚሰጧቸው ቃል ገብተውላቸው ነበር።[40] ጣልያኖች እ.አ.አ. በመስከረም 1888 ዓ.ም. የውጫሌውን ውል ረቂቅ ሲጠነስሱም ምኒልክ ውሉን ከተቀበሉ 10,000 ጠመንጃዎችን በዓሰብ በኩል እንደሚያቀርቡላቸው ቃል ገብተውላቸው ነበር።

ከአጼ ዮሐንስ ዕልፈት በኋላ ኢትዮጵያን የተቆጣጠሩት አጼ ምኒልክ ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር በኩል ስለሚኖራት ይዞታ፣ መብትና ተጠቃሚነት እምብዛም ትኩረት እንዳልሰጡ አጼ ዮሐንስ ከሞቱ ሁለት ወራት በኋላ ከጣልያኖች ጋራ የፈረሙት የውጫሌ ስምምነት ይመሰክራል። ስምምነቱ የባሕር በሩን ብቻ ሳይሆን የተወሰነውን የኤርትራን ደጋ ክፍል ጭምር በጣልያኖች ግዛት ሥር የሚያካትት ሲሆን ስምምነቱም «*በነዚህ በፊ ነገሥታት ወሰን ጠብና ክርክር እንዳይነሣ በውቅ የተመረጡ ከፊ ወገኖች ፪ ፪ ሽማግሌዎች ልከው በማይጠፋ ምልክት የግዛቱን ድንበር ይካፈላሉ። ከድንበሩ ወዲህ የሚጨመሩት አገሮች እነዚህ ናቸው፤*

ሀ. የደጋው አፋፍ ከኢትዮጵያና ከኢጣልያ ማኸል ወሰን ይሆናል
በ. ከራፋሊ ዝምሮ ኃለይ፣ ሰገነይቲ፣ አሥመራ፣ ፫ቱ የኢጣልያ መንግሥት መንደር ይሆናሉ። ዳግመኛ በቦገስ በኩል፣
ከ. አዲ ነፋስ አዲ ዋንስ በኢጣልያ ድንበር ውስጥ ይሆናሉ።
ደ. ከአዲ ዋንስ መንደር ዝምሮ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ በቀና ይከፋፈላል[41]» ይላል።

---

[39] Rubenson, S. *Wichale XVII: The Attempt to Establish a Protectorate over Ethiopia*. Artistic Printing Press, Addis Ababa, Appendix p. 66, Article III.

[40] ibid., p.46.

[41] ibid., p.66.

ጣልያኖች በውጫሌ ውል ባገኟቸው የኢትዮጵያ ግዛቶች ሳይወሰኑ ወደ ፊት እየገፉ ሰፊ አካባቢን ተቆጣጥረው እ.አ.አ. ጥር 1 ቀን 1890 ዓ.ም. በውጫሌ ውልና ከውሉ ውጭ የተቆጣጠሯቸውን ግዛቶች አጣምረው «*የኤርትራ ቅኝ ግዛትን*»[42] መሠረቱ። ቀስ በቀስም ወደ ፊት እየገፉ ሄደው ከአራት ዓመት በኋላ የውጫሌን ውል በይፋ ሳይሠርዙ በደቡብ በኩል ወሰናቸው መረብ-በለሳ-ሙና መሆኑን አወጁ። በወቅቱ ጣልያኖች ኢትዮጵያን በተመለከተ ሁለት ተቃራኒ ፖሊሲዎችን ያራምዱ ነበር። በአንድ በኩል፣ በኢትዮጵያ የነበረውን የመከፋፈንና የመሳፍንት ቅሬታ እየቆሰቆሱ ምኒልክን አዳክመው ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር ሲሞክሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ምኒልክን በመደገፍ በውጫሌ ውል አንቀጽ 17 መሠረት የእነእርሱ አገልጋይ ለማድረግ ይሞክሩ ነበር። ይህን አቋማቸውንም ለማንጸባረቅ ከአጼ ምኒልክ ጋራ ተከታታይ ድርድሮችን እያደረጉም ግዛታቸውን ከኤርትራ ዐልፎ ወደ ትግራይም ለማስፋፋት ሳይቦዝኑ ዓዲግራትንና ዓድዋንም ተቆጣጠሩ። የጣልያኖችን መስፋፋት ያሳሰባቸው አጼ ምኒልክም ኃይላቸውን አሰባስበው ወደ ትግራይ በመንቀሳቀስ እ.አ.አ. በ1890 ዓ.ም. መቀሌ ገብተው እስከ ሐውዜን ተንቀሳቅሰው ትግራይን በሦስት ግዛቶች ከፍለው አስተዳዳሪዎች ሾመው ወደ መኻል አገር ተመለሱ። ከነዚህ ከሾሟቸው አስተዳዳሪዎች አንዱም ራስ መንገሻ ዮሐንስ ነበሩ።

ጣልያኖች አጼ ምኒልክን ለማዳከም ሲሉ በወቅቱ ከነበሩት ታዋቂ መሪዎችና መኳንንት ማለትም ከንጉሥ ተክለሃይማኖት፣ ከንጉሥ ሚካኤል፣ ከራስ መንገሻ ዮሐንስ፣ ከራስ መኮንንና ከሌሎችም ጋራ የምስጢር ግንኙነት ጀመሩ። ይህም በአጼ ምኒልክ ዘንድ ቁጣን ቀስቅሶ «*አጼ ምኒልክ እ.አ.አ. የካቲት 27 ቀን 1893 ዓ.ም. የውጫሌን ውል በይፋ ማውገዛቸውን ለኃያላኑ የአውሮፓ መንግሥታት አስታወቁ*»[43]። ይህ የአጼ ምኒልክ ውሳኔ ኢጣልያ በአንድ የፖሊሲ አማራጭ ማለትም ኢትዮጵያን በኃይል በመቆጣጠር ፖሊሲ ብቻ እንድትጸና አድርጓት ጣልያኖች ዋናውን ጦራቸውን ዓዲግራት ላይ በማስፈር ቃኚ ኃይላቸውን ደግሞ መቀሌና አላጄ አካባቢ አሰፈሩ። ይህ የጣልያኖች ተግባር በ1888 ዓ.ም. በኢትዮጵያና በኢጣልያ መኻል ዓድዋ ላይ ለተደረገው ጦርነት ምክንያት ሆነ።

ጣልያኖች ከተቆጣጠሩት ቀይ ባሕርና በአብዛኛው በረሐማ ከሆነው የኤርትራ ግዛት ከሚያገኙት ጥቅም ይልቅ ወጪያቸው በመብለጡ ለም የሆነውን ቀሪውን የኢትዮጵያ ግዛት ለመቆጣጠር ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው። ይህን ሲወጥኑም የተበታተነ የመሰላቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመሪዎቹ ጎን በአንድ ልብ ተሰልፎ ለነጻነቱና ለሉዓላዊነቱ እንደሚቀና ዓድዋ ላይ በጦርነት እስኪሸነፉ ድረስ አልገባቸውም ነበር። አጼ ምኒልክ ክተት ካወጁ በኋላ ሕዝቡ ምንም ዓይነት ክፍያ ሳይሰጠውና ዋስትና ሳያገኝ ሕይወቱን ለመገበር ቆርጦ መነሣቱ የድሉ ዋናው ምሥጢር መሆኑን ጣልያኖችም ሆኑ ሌላው ዓለም አልተገነዘቡትም ነበር። በወቅቱ በአጼ ምኒልክ የተከፋውና ቂም ያለው ሕዝብ ሳይቀር በዓድዋ ጦርነት የራሱን ስንቅ ቋጥሮ፣ የራሱን መሣሪያ ታጥቆ፣ ለወራት ተጉዞ፣ ሕይወቱን ገብሯል። አጼ ምኒልክና ሌሎች አዛዦችም ያደረጉት የማስተባበር ሥራ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፤ ታሪክም አይረሳውም።

ጣልያኖች ዓድዋ ላይ አሳፋሪ ሽንፈት ቢከናነቡም ከሽንፈታቸው በኋላ በማያሻማ ሁኔታ የኢትዮጵያ ግዛት የነበረውን የቀይ ባሕርና የኤርትራን ስትራቴጂያዊ አካባቢ ግዛታቸው ሆኖ እንዲቀጥልና ሕጋዊ ዕውቅና እንዲያገኝ እ.አ.አ. ጥቅምት 2 ቀን 1896 ዓ.ም. ከአጼ ምኒልክጋ ውል ተፈራረሙ።[44] በመቀጠልም የኢጣልያ ቅኝ ግዛት የሆነችውን የኤርትራን

[42] Berkeley, G.F.H. 1902. *The Campaign of Adowa and The Rise of Menelik*. Negro Universities Press, p.24.
[43] ibid., p. 54.
[44] Henze, P.B. *Eritrea in the First Half of the 20th Century*. Article, p.1.

ወሰን ለማረጋገጥ እ.አ.አ. በ1900 ዓ.ም.፣ በ1902 ዓ.ም. እና በ1908 ዓ.ም. ከአጼ ምኒልክ ጋር የድንበር ማካለል ውሎች፣ ስምምነቶችና መግባባቶችን ተፈራረሙ። እነዚህ የድንበር ስምምነቶች በተለይ ደግሞ የ1908 ዓ.ም.ቱ ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር አካባቢ መግቢያና መውጫ እንድታጣ አደረጋት። ጣልያኖች ከራስ ካሳር እስከ ታጁራ ያለውን ረጅም የባሕር ጠረፍ ሲቆጣጠሩ፣ ፈረንሳዮች የጅቡቲን የባሕር በር፣ እንግሊዞችም ሶማሌላንድን ሲቆጣጠሩ ኢትዮጵያ በስትራቴጂያዊው ቀይ ባሕር የነበራትን ይዞታ ፍጹም ዐጣች።

4. የኢጣልያ ወረራና የኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋራ መዋሐድ

ከአጼ ምኒልክ በኋላ ሥልጣኑን በቅደም ተከተል የተረከቡት ልጅ እያሱና ንግሥት ዘውዲቱ ቀይ ባሕርንና ዓባይን በተመለከተ የወሰዱት የጎላ እርምጃ አልነበረም። አንዳንድ የታሪክ ተመራማሪዎች ልጅ እያሱ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ከጀርመንና ከሽሪኮቿ ጋራ ጠንካራ ግንኙነት ለመፍጠር የሞከሩት በወቅቱ ቀይ ባሕርን ተቆጣጥረው የነበሩትን እንግሊዞች፣ ፈረንሳዮችና ጣልያኖችን ለመቋቋምና በአካባቢው ይዞታ ለማግኘት በማሰብ ነበር ይላሉ። ያም ሆነ ይህ በንግሥት ዘውዲቱ የመጨረሻ የሥልጣን ዘመን ማለትም እ.አ.አ. በ1929 ዓ.ም. የዓባይ ወንዝ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሥር ለነበሩት ለሱዳንና ለግብጽ ብቻ እንዲካፈል ተደረገ። ይህ ኢ-ፍትሐዊ ስምምነት እንግሊዞች በግብጽና በሱዳን ከነበራቸው ጥቅም በተለይ የዓባይም ውሃ በመጠቀም የሚመረተውን ጥጥ የሚመለከት ስለነበር በግዛታቸው ሥር የነበሩትን ሌሎች የምሥራቅ አፍሪካ አገሮችና ኢትዮጵያን ከዓባይ ተጠቃሚነት ያገለለ ነበር። ሱዳን ነጻ ከወጣች ከሦስት ዓመታት በኋላ ማለትም እ.አ.አ. በ1959 ዓ.ም. ከዓባይ ውሃ ሰባ ዐምስት ከመቶው ለግብጽ፣ ኻያ ዐምስት ከመቶው ደግሞ ለሱዳን ጥቅም፣ እንዲውል ስምምነት ላይ የተደረሰውም አብዛኛዎቹ የተፋሰሱ አገሮች ባልተሳተፉበት ነበር[45]። የመጀመሪያው ስምምነት ሱዳን በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሥር ግብጽ ደግሞ በእንግሊዞች ተጽዕኖ ሥር በነበሩበት ወቅት የተፈረመ ሲሆን ሁለተኛው በግብጽና በሱዳን መኻል የተፈረመው ውልም የቆየውን የቅኝ ገዥዎች ዱካ በመከተል ነበር።

በንግሥት ዘውዲቱ የሥልጣን ዘመን ኢጣልያን ያስተዳድር የነበረው እ.አ.አ. በ1922 ዓ.ም. ሥልጣን የተቆጣጠረው የቤኒቶ ሙሶሊኒ ፋሺስት ፓርቲ፣ ኢጣልያ በ1888 ዓ.ም. ዓድዋ ላይ ለደረሰባት ሽንፈት ለመበቀልና በምሥራቅ አፍሪካ ሰፊ ግዛት ለመመሥረት ኢትዮጵያን ዳግም ለመቆጣጠር ታጥቆ ተነሥቶ ነበር። በወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣናት አይቀሬውን የኢጣልያን ወረራ ለማክሸፍ ብርቱ ዝግጅት ከማድረግ ይልቅ በውስጥ የሥልጣን ሽኩቻና የእርስ በእርስ ግጭት ተጠምደው ነበር። አጼ ምኒልክ በጠና ታመው የዕለት ተዕለት የመንግሥት ሥራ ማከናወን ባቃታቸው ጊዜም መንግሥቱን ይመሩ የነበሩት እቴጌ ጣይቱ ተፈጥሮ በነበረው የሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት በሸዋ መኳንንት መጋቢት 12 ቀን 1902 ዓ.ም. ከሥልጣን ተገለው ለቁም እስር ተዳረጉ። ልጅ እያሱ እቴጌ ጣይቱን ተክተው ሥልጣን ቢይዙም በመኳንንቱ መኻል የነበረው ሽኩቻ ሳያባራ እንዲያውም በ1909 ዓ.ም. በልጅ እያሱ አባት በወሎው ንጉሥ ሚካኤልና በሸዋ መኳንንት መኻል ወደ ተኪያሂደው የሰገሌ ጦርነት አመራ።[46] ከዚያ በኋላም ልጅ እያሱ ከሥልጣን ተወግደው በንግሥት ዘውዲቱ ቢተኩም ንግሥት ዘውዲቱም የሥልጣን ሽኩቻው አልተለያቸውም ነበር። በ1922 ዓ.ም. በሸዋና በእቴጌ ጣይቱ የወንድም ልጅ በሆኑት በራስ

---

[45] Allan, G.A. 2000. *The Middle East Water Question: Hydropolitics and the Global Economy*, I.B. Tauris Publishers: London - New York, p.218.

[46] Bahru Zewde, *op.cit.*, p.128.

ጉግሳ ወሌ መኻል የአንቺም ጦርነት[47] በመባል የሚታወቀው ከባድ ጦርነት ተኪያሄደ። በዚሁ ዓመተ ምሕረት በማዕከላዊው መንግሥትና በራያ ሕዝብ መኻልም ግጭት ተከስቶ ነበር።

ራስ ተፈሪ መኮንን በንግሥት ዘውዲቱ የሥልጣን ዘመን ወሳኙን የአመራር ሚና እየተጫወቱም ሳለ በወግ አጥባቂው የመኳንንቱ ክፍልና ተራማጅ በሚባሉት በእነ ራስ ተፈሪ መኻል የሥልጣን ሽኩቻው ቀጥሎ ነበር። ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው በ1923 ዓ.ም. ዘውድ ከጫኑ በኋላ ግን በወግ አጥባቂዎችና በተራማጆች መኻል የነበረው የሥልጣን ሽኩቻ አከተመ። ራስ ተፈሪም ዘመናዊ ሕገ መንግሥት አርቅቀው ሥራ ላይ እንዲውል አድርገው ኢትዮጵያን ወደ ዘመናዊነት እንድትሸጋገር መንገዱን ከፈቱ። ሆኖም አጼ ኃይለ ሥላሴ በነገሡ በአራተኛ ዓመታቸው ኢጣልያ በወልወል በኩል ግጭት አንሥታ ከአንድ ዓመት በኋላም መስከረም 1928 ዓ.ም. ላይ ጣልያኖች በኢትዮጵያ ላይ ታላቁን ጦርነት ከፈቱ።[48] አጼ ምኒልክ በጠና ከታመሙበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ጣልያኖች ወረራ ባሉት 29 ዓመታት ኢትዮጵያ በእርስ በርስ ሽኩቻና ጦርነት ስትታመስ ወረራ ለመመከት የሚያስችል የመከላከያ ኃይል ሳትገነባ በድንገት በፋሺስት ኢጣልያ ተወረረች።

ኢጣልያ በ1928 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ላይ ያኪያሄደችው ወረራ ከዓድዋ ጦርነት በፊት ቀይሳው የነበረው መላ ኢትዮጵያን የሚያካትት ሰፊ የቅኝ ግዛት የማቋቋም ዕቅዷ ቅጥያ ነበር። የኢጣልያ መሪዎች የዓድዋው ሽንፈት ትልቅ ቁጭት አሳድሮባቸው ስለነበር ለዘመናት ተዘጋጅተው በ1928 ዓ.ም. ዘመኑ ባፈራቸው በርካታ የጦር አውሮፕላኖች፣ መድፎችና ታንኮችን ተጠቅመው ጦርነቱን በድል ለመወጣት ቻሉ። በአንጻሩ በኢትዮጵያ በኩል የነበረው ዝግጅት፣ የጦር መሣሪያና አደረጃጀት እንኳንስ ከጣልያኖች ሊወዳደር በዓድዋ ጦርነት ከነበረውም ፍጹም አይመጣጠንም ነበር።

ይህ ሁሉ ሆኖም ኢትዮጵያ የነበራትን ኃይል አረባርባ ለስድስት ወራት ያህል የጣልያኖችን በሚገባ የተደራጀ አስር ክፍለ ጦርና በርካታ አውሮፕላኖች በሰሜን ግንባር መክታለች። የኢትዮጵያ ጀግኖች በተምቤን፣ በአምባ አርዓዶም፣ በሽሬ እንዳባጉና፣ በመጨረሻም በማይጨው ብርቱ የመከላከል ውግያዎችን አኪያሂደዋል። ጣልያኖች በነዚህ ውጊያዎች ከባድ ኪሳራ ቢደርስባቸውም ድል ግን ተቀዳጅተዋል። በምሥራቅ ግንባርም ጀግኖቹ የኢትዮጵያ ልጆች የጣልያኖችን አንድ የተጠናከረ ሜካናይዝድ ጦርና በሺዎች የሚቆጠሩ ባንዳዎችን ተጋፍጠው ከባድ መሥዋዕትነት ከፍለዋል። በመጨረሻም ኢትዮጵያ የገጠማት የጠላት ኃይል ከዓቅሟ በላይ ሆኖ ጣልያኖች ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም. አዲስ አበባን ተቆጣጠሩ።[49]

ጣልያኖች ኢትዮጵያን ለዐምስት ዓመታት ያህል ይግዙ እንጂ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች የኢትዮጵያ አርበኞች የሽምቅ ውግያ እያኪያሄዱ ሰላም ነስተዋቸው ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳለ በ1932 ዓ.ም. ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተቀሰቀሰ ጣልያኖች ከጀርመን ጎን በመሰለፋቸው ከእንግሊዞች፣ ከፈረንሳዮችና ከአሜሪካኖች ጋራ ባላንጣ ሆኑ። ይህ ክስተት ለኢትዮጵያ መልካም አጋጣሚ ፈጠረ። እንግሊዞች ከጣልያኖች ጋራ የነበራቸውን ቃል ኪዳን አፍረሰው ጣልያንን በአፍሪካ ከተቆጣጠረቻቸው ግዛቶች ለማስወጣት ተንቀሳቅሰው

---

[47] ibid., p.136.
[48] ዝኒ ከማሁ፣ በላይ ግደይ፣ ገጽ 23፣ ገጽ 63
[49] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 135

በሊብያና በምሥራቅ አፍሪካ ፀረ-ኢጣልያ ጥቃቶችን ከፈቱ። ጣልያኖችም ይህን የእንግሊዞችና የአርበኞች ጥቃት መቋቋም አቅቷቸው ጎዳር 24 ቀን 1934 ዓ.ም በምሥራቅ አፍሪካ ግዛታቸው የመጨረሻ ምሽጋቸው ከነበረው ጎንደር ወጡ። ጣልያኖች ከምሥራቅ አፍሪካ ግዛታቸው ሙሉ በሙሉ ከመውጣታቸው በፊት በጎጃምና በአዲስ አበባ ተሸንፈው ስለነበር በ1932 ዓ.ም. በሱዳን በኩል ወደ ኢትዮጵያ መግባት ጀምረው የነበሩት አጼ ኃይለ ሥላሴ ከዐምስት ዓመታት በፊት ወደ ተውዋት አዲስ አበባ ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም. በድል ተመለሱ።[50]

የዐምስት ዓመታቱ የኢጣልያ የቅኝ ግዛት በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ቢጠናቀቅም የሙሶሊኒ ፋሺስት ጦር ያደረሰው ጉዳት ወደር አልነበረውም። በዓለም ዐቀፍ ሕግ የተከለከለውን የመርዝ ጋዝ በመጠቀም በርካታ ኢትዮጵያውያንን ጨርሰ፤ የንጹሐንን ሕይወት ቀጥፎ፤ በርካታ ንብረትን አውድሞ ነበር። የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት እንዳለቀ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ሰዎች በተደረገው አኃዛዊ ግምገማ ወይም የኢትዮጵያ መንግሥት በ1938 ዓ.ም. በፓሪስ የሰላም ጉባኤ ላይ ያቀረበው ማስታወሻ እንደሚገልጸው ሰባት መቶ ስድሳ ሺሕ ሦስት መቶ /760,300/ ኢትዮጵያውያን በልዩ ልዩ ምክንያት እንደተገደሉ፣ እንደቆሰሉ ወይም እንደተመረዙ ሲያመለክት፣ ዐምስት መቶ ኻያ ሺሕ /520,000/ ቤቶች ከነንብረታቸው እንደ ተቃጠሉ፣ ሁለት ሺሕ /2,000/ አብያተ ክርስትያናት ተቃጥለው እንደ ፈረሱና ቅርሳቸውም እንደተበዘበዘ፣ ዐምስት ሚልዮን /5,000,000/ የቀንድ ከብቶች፣ ሰባት ሚልዮን /7,000,000/ በጎችና ፍየሎች፣ አንድ ሚልዮን /1,000,000/ ፈረሶችና በቅሎች፣ ሰባት መቶ ሺሕ /700,000/ ግመሎች እንደተፈጁ፣ አንጅሎ ዴል ቦካ የተባለው ጣልያናዊ የታሪክ ጸሐፊ «*የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*» በሚለው መጽሐፉ በገጽ 275 ያመለክታል። እንዲሁም በላይ ግደይ «*በጊዜው ተምረዋል ይባሉ ከነበሩት ወጣቶች መኻል ከመቶ ሰባ አጅ ያህሉ በግፍ ተገድለዋል*»[51] ይላሉ።

አጼ ኃይለ ሥላሴ በእንግሊዞች እርዳታና በኢትዮጵያውያን አርበኞች ተጋድሎ ከስደት ሲመለሱ ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ አልተረከቡም ነበር። ጣልያኖች በ1928 ዓ.ም. ኢትዮጵያን ከተቆጣጠሩ በኋላ በምሥራቅ አፍሪካ የነበሯቸውን ግዛቶች አንድ ላይ አዋሕደው «*የኢጣልያ የምሥራቅ አፍሪካ ግዛት*» በሚል ሰይመዋቸው ነበር። በአስተዳደር ረገድም ኤርትራን፣ ትግራይንና አፋርን እንደአንድ ክፍለ ሀገር አዋቅረው አሥመራን ዋና ከተማ አድርገዋት ነበር። አማርኛ ተናጋሪዎችንም በአንድ አስተዳደር ሥር አዋቅረው ጎንደርን ዋና ከተማ አድርገዋት ነበር። አብዛኛውን የኦሮሚያና የደቡብ ክልልንም በአንድ አስተዳደር አጠቃለው ጅማን ዋና ከተማ አድርገዋት ነበር። ከፊል አጋዴንንና ምሥራቅ ኦሮሚያንም በአንድ አስተዳደር አዋቅረው ሐረርን ዋና ከተማ አድርገዋት ነበር። አብዛኛውን የአጋዴን ክፍልም ከደቡብ ሶማልያ ጋራ አዋሕደው ሞቃዲሾን ዋና ከተማ ሲያደርጉ አዲስ አበባና አካባቢዋንም አንድ ራሱን የቻለ አስተዳደር አድርገው አደራጅተውት ነበር።[52] የዚህ የጣልያኖች ሰፊ ግዛት ዋና ከተማም አዲስ አበባ ነበረች።

ጣልያኖች ትግራይንና ኤርትራን በአንድ አስተዳደር አጣምረው ይገዙ ስለነበር የተኳቸው እንግሊዞችም እስከ 1934 ዓ.ም. ድረስ ትግራይን ለንጉሠ ነገሥቱ አላስረከቡም ነበር።

---

[51] ዝኒ ከማሁ፣ በላይ ግደይ፣ ገጽ 143

[52] ተድላ ዮሐንስ፣ 2004 ዓ.ም፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ኢጣልያ በኢትዮጵያ፣ ከወልወል እስከ ጎንደር*፣ ግንቦት 1927 ጎዳር 1934 ዓ.ም.፣ ገጽ 210፣ Bahru Zewde, op. cit., p.162.

የኦጋዴንን አካባቢም ከእንግሊዝ ሶማሊላንድ ጋራ አጣምረው ለመግዛት ፍላጎት ስለነበራቸው ለንጉሡ አሳስረከቡም ነበር። እንዲያውም በጉዳዩ ለመነጋገር በአክሊሉ ሀብተ ወልድ የሚመራ የልኡክ ቡድን ለንደን በሄደበት ወቅት የእንግሊዙ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኧርነስት ቤቪን «*ኢትዮጵያ ኦጋዴንን አስተዳድራ ስለማታውቅ እንግሊዝ ይህን ግዛት አትመልስም።*»[53] የሚል የጸና አቋም ይዞ ነበር። እንግሊዞች ኦጋዴንን ለኢትዮጵያ በከፊል ያስረከቡት እ.አ.አ. በ1948 ዓ.ም. ሲሆን ሙሉ በሙሉ ያስረከቡት ደግሞ እ.አ.አ. በ1954 ዓ.ም. ነበር።[54] እንግሊዞች ኢትዮጵያ ነጻና ሉዓላዊ አገር ነች ብለው ሁለት ጊዜ የወዳጅነት ስምምነት ቢፈራረሙም ከኢትዮጵያ ጋር የነበራቸው ተጨባጭ ግንኙነት ግን ሞግዚታዊ ሆኖ በመንግሥት ጸጥታዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ጣልቃ እየገቡ ውሳኔዎችን በመስጠት የአገሪቱን ሉዓላዊነት የሚጋፉበት ነበር።

እንግሊዞች ትግራይን ለአንድ ዓመት ያህል ከተቆጣጠሩ በኋላ ለንጉሠ ነገሥቱ ሲያስረክቡ ኤርትራን ግን «*በቁጥጥር ሥር የዋለ የጠላት ግዛት*» ብለው በእንግሊዝ ሞግዚታዊ አስተዳደር ሥር አቆይዋት። እንግሊዞች ይህን ሲያደርጉ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ገና ባለማብቃቱ የቃል ኪዳን አገሮች ኤርትራን በመካከለኛውና በሩቅ ምሥራቅ ለሚያደርጓቸው ወታደራዊ ዘመቻዎች መረማመጃ አድርገዋት ስለነበር የተሻለ እድገት አሳይታ ነበር። ኤርትራ ከጣልያኖች ነጻ ከወጣች በኋላ ከቃል ኪዳን አገሮች ጋራ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተሳተፉት አሜሪካውያንም የኤርትራ ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ማርኳቸው 3,000 ወታደሮቻቸውን አስፍረውባት ነበር። ኤርትራውያንም ምጽዋ ላይ በተቋቋሙት የቃል ኪዳኑ ወታደራዊ ተቋማትና በበርካታ ፋብሪካዎች በመሥራት ጥሩ ገቢ ማግኘት ጀምረው ነበር። በተጨማሪም ኢንግሊዞች ኤርትራውያንን የሠራተኛ ማኅበራት፣ የግል ፕሬስና ሌሎች ሲቪል ማኅበራት እንዲያቋቁሙ ያበረታትዋቸው ነበር። እ.አ.አ. በ1945 ዓ.ም. ከተጀመረ ከዐምስት ዓመት በኋላ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲያበቃ የሲቪልና የፖለቲካ ነጻነቶች ቢቀጥሉም የኤርትራ ኢኮኖሚ ዳሽቆ፤ የእድገት ተስፋ ጨልሞ፣ የሕዝቡ ኑሮ ተመሰቃቅሎ፣ የዐመፅና የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ተበራከቱ።

እ.አ.አ. በ1945 ዓ.ም. ስለኢጣልያ፣ ጀርመንና ተባባሪዎቻቸው ቅኝ ግዛቶች የወደፊት ዕጣ ፈንታ ለመነጋገር የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ሄንሪ ትሩማን፣ የታላቋ ብሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዊንስተን ቸርችልና የሶቭዬት ኅብረቱ መሪ ማርሻል ጆሴፍ ስታሊን ፖትስዳም በምትባል ትንሽ የጀርመን ከተማ ተሰበሰቡ። በስብሰባውም ጉዳዩን በጥልቀት ለመመልከትና ውሳኔ ለመስጠት ፈረንሳይን ጨምሮ ሌላ ጉባኤ ለመጥራት ወሰኑ። በዚህ መሠረትም እ.አ.አ. መስከረም 1946 ዓ.ም. ለንደን ላይ እንደገና ሲሰበሰቡ ኤርትራን በተመለከተ ኢጣልያና ኢትዮጵያ የይገባኛል ጥያቄ አቀረቡ። በጉዳዩ የመወሰን ሥልጣን የነበራቸው ኃያላን መንግሥታትም በዚህ ጉዳይ የጋራ ውሳኔ ላይ ሊደርሱ ሳይችሉ አሜሪካኖችና ሶቭዬቶች ኤርትራ በሞግዚት አስተዳደር ሥር ትቆይ ሲሉ ፈረንሳይ ኤርትራ ለኢጣልያ ትመለስ እንግሊዝ ደግሞ የኢትዮጵያ ጥያቄ ቸል መባል የለበትም በማለት በጉዳዩ ለመስማማት ሌላ ጉባኤ እንዲጠራ ስምምነት ላይ ደረሱ።[55]

---

[53] አክሊሉ ሀብት ወልድ /ጸሐፊ ትእዛዝ/፣ 2003 ዓ.ም.፣ መስከረም 10 ቀን 1967 ዓ.ም. ለመርማሪ ኮሚሽን ያቀረቡት መግለጫ፣ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ፕሬስ፣ ገጽ 34

[54] Bahru Zewde, op.cit., p.181.

[55] ዘውዴ ረታ፣ *በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥት፣ የኤርትራ ጉዳይ፣ 1941-1963* እ.አ.አ.፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ ጥር 2000 ዓ.ም.፣ ገጽ 30

በስምምነቱ መሠረት እ.አ.አ. በ1946 ዓ.ም. አራቱ ኃያላን መንግሥታት የኢጣልያ ቅኝ ግዛቶችን ጉዳይ በተመለከተ አንድ ዓለም ዐቀፍ ኮንፈረንስ ፓሪስ ላይ ሲያኪያሂዱ ኢትዮጵያ በኮንፈረንሱ ተሳታፊ ሆና ኤርትራ ለእርሷ እንደምትገባ ጥያቄ ከማቅረቧም ባሻገር በኢጣልያ ሶማልያ ወይም በሞቃዲሾ ላይም የይገባኛል ጥያቄ አቅርባ ነበር[56]። ኢትዮጵያ ጥያቄዎቿን ያቀረበችው መልካም አጋጣሚውን ለመጠቀም ሳይሆን በተለይ ኤርትራ ከታሪክ፣ ከሕግና ከፖለቲካ አንጻር የኢትዮጵያ አካል እንደሆነች በማስረጃዎች አስመርኩዛ ጥያቄዋ አግባብነት እንዳለው በማመን ነበር። በእርግጥ የአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ካከተመ ከ1881 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1928 ዓ.ም. ድረስ ጣልያኖች ኤርትራን ከኢትዮጵያ ነጥቀው በቅኝ ግዛታቸው ሥር አውለዋት ነበር። ሆኖም ከ1928 ዓ.ም. ጀምሮ ጣልያኖች ኤርትራን፣ ቀሪውን ኢትዮጵያና ደቡብ ሶማልያን አዋሕደው አንድ የምሥራቅ አፍሪካ የቅኝ ግዛት ቀጠና አቋቁመው አዲስ አባባን እንደቅኝ ግዛታቸው ማዕከልና እንደእንደራሴያቸው መኖርያ እንዳደረጓት ቀደም ሲል ተጠቅሷል። ከዚህ የተነሣም የዓድዋን ጦርነት ተከትሎ ኤርትራ የጣልያኖች ቅኝ ግዛት እንድትሆን እንዲሁም የኢትዮጵያንና የጣልያን ሶማልያን ድንበሮች ለማካለል በአጼ ምኒልክና በጣልያኖች መካከል የተደረጉት ስምምነቶች ሁሉ ውድቅ ሆነውም ነበር።

በፓሪሱ ዓለም ዐቀፍ ኮንፈረንስ ግብጽና ኢጣልያ በኤርትራ ላይ የይገባኛል ጥያቄ አቅርበው ነበር። ግብጾች «*ዶሮ ማሳዋን ተቆጣጥረን ነበርና ለኛ ትገባለች።*»[57] የሚል ክርክር በማንሣት የቱርኮችን ውክልና አግኝተው ምጽዋን ለረጅም ጊዜ ማስተዳደራቸውንና ጣልያኖች ኤርትራን የተቆጣጠሩት እነእርሱን አስለቅቀው እንደነበር በማስረጃነት ያጣቅሱ ነበር። ኢጣልያም እንዲሁ ኤርትራ ቅኝ ግዛቷ እንደነበረችና ሕዝቡም የኢጣልያን አገዛዝ የመቀበል ፍላጎት እንዳለው ትገልጽ ነበር። ይህ የኤርትራ የይገባኛል ጥያቄ ለዓመታት ሲያወዛግብ መቆየቱ ሦስቱም መንግሥታት የይገባኛል ጥያቄ በማቅረባቸው ብቻ ሳይሆን አራቱ ድል አድራጊ ኃያላን መንግሥታት አገራዊ ጥቅማቸውን የማስጠበቅ ፍላጎት ስለነበራቸውም ነበር። ሶቭዬቶች ኤርትራ በጣልያኖች ሥር እንድትቆይ ወይም ነጻ እንድትወጣ ይፈልጉ የነበረው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት ከእነርሱጋ ጥብቅ ግንኙነት የነበረው የኢጣልያ ኮሙዩኒስት ፓርቲ በምርጫ ያሸንፋል የሚል ግምት ስለነበራቸው ፓርቲው ኤርትራን ቢቆጣጠር ለኮሙዩኒስቶች መጠናከር ምክንያት ይሆናል ከሚል ነበር። እንግሊዝ ደግሞ ኤርትራ ከሁለት ተከፍላ ቆላው ክፍሉ ከሱዳን ቅኝ ግዛቷ ጋራ፣ ደጋው ትግርኛ ተናጋሪ ክፍልም ከኢትዮጵያ ጋራ እንዲቀላቀል አልያም ኤርትራ ከትግራይ ጋራ ተዋሕዳ በእርሷ ተጽዕኖ ሥር የዋለ «*የትግራይ ትግርኚ*»[58] መንግሥት እንዲቋቋም ፍላጎት ነበራት። አሜሪካኖችም መጀመሪያ ላይ ግልጽ የሆነ አቋም ባይኖራቸውም ኋላ ላይ ግን ጥቅማቸው ይበልጥ የሚጠበቀው የእንግሊዝን መሰል አቋም በማራመድ መሆኑን ተቀብለው ነበር። የፈረንሳዮች አቋም መጀመሪያ ላይ ኤርትራ በኢጣልያ ሥር ትቆይ የሚል ሆኖ ኋላ ላይ ግን ከሞላ ጎደል ከአሜሪካና ከእንግሊዝ ጋራ ተመሳሳይ አቋም ያዙ። በጉባኤው ማብቂያ ላይም ኢጣልያ የቅኝ ግዛቶቿን ተነጥቃ ለወረራቻቸው አገሮች ካሳ ከፍላ ዕርቅ እንድትፈጽም በድምጽ ብልጫ ተወሰነ። ውሳኔው ለኢትዮጵያ ትልቅ ድል ቢሆንም አራቱ ኃያላን መንግሥታት የኤርትራን የወደፊት ዕጣ ፈንታ በተመለከተ አሁንም ሊስማሙ ባለመቻላቸው እ.አ.አ. በ1948 ዓ.ም. ጉዳዩ ወደ ተባበሩት መንግሥታት ተላለፈ። በዚህም መሠረት ከኖርዌ፣ ጓቴማላ፣ ፓኪስታን፣ በርማና

---

[56] ዝኒ ከማሁ፣ አክሊሉ ሀበት ወልድ /ጸሐፊ ትእዛዝ/፣ ገጽ 43

[57] ዝኒ ከማሁ፣ አክሊሉ ሀበት ወልድ /ጸሐፊ ትእዛዝ/፣ ገጽ 43

[58] ትግራይና ኤርትራ በጋራ የሚጠሩበት ስም ሲሆን በተለይ በሁለቱ አካባቢዎች የሚኖሩትን ትግርኛ ተናጋሪዎች ታሳቢ የሚያደርግ ነው።

ደቡብ አፍሪካ አንዳንድ ሰው የተወከለበት ኮሚሽን ተቋቁሞ የኤርትራን ሕዝብ ፍላጎት በማገናዘብ ኮሚሽኑ ለተባበሩት መንግሥታት የመፍትሔ ሐሳብ እንዲያቀርብ ተወሰነ።

ከላይ የተጠቀሰው ኮሚሽን ኤርትራን በተመለከተ የመፍትሔ ሐሳብ ለማቅረብ በሚንቀሳቀስበት ወቅትም ሆነ ከዚያም ቀደም ብሎ በአካባቢው ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያካሂዱ የነበሩት፤ 1ኛ/ የኢጣልያ መንግሥት፣ 2ኛ/ የእንግሊዝ መንግሥት፣ 3ኛ/ የግብጽ መንግሥት፣ 4ኛ/ የኢትዮጵያ መንግሥት፣ ነበሩ። እነዚህ መንግሥታት እንደየዓቅማቸው ኤርትራ ውስጥ የሚደግፏቸው ፓርቲዎች ነበሯቸው። እንግሊዝ ኤርትራን በተጽዕኖዋ ሥር ለማቆየት በአብዛኛው ትግርኛ ተናጋሪዎችን ለሚያካትተውና ትግራይንና ኤርትራን በማዋሐድ «ትግራይ ትግሪኚ» የሚል ነጻ አገር የመመሥረት ፍላጎት ለነበረው «የኤርትራ ሊበራል ፕሮግሬሲቭ ፓርቲ» ድጋፏን ትሰጥ ነበር። የኢጣልያ መንግሥት ደግሞ «ሠልፊ ነጻነት» ወይም የነጻነት ፓርቲ የሚባለውን አንስተኛ ፓርቲ አቋቁሞ ነበር። ግብጽም በሱዳኑ የአልማርጆኒ ፓርቲ አማካይነት «አል ራቢጣ አል ኢስላምያ» እንዲሁም «እስላማዊ ሊግ» የሚል ነጻነትን የሚሻ ፓርቲ በመደገፍ ፍላጎቷን ለመጫን ትጥር ነበር። ኢትዮጵያም «አንድነት ወይም አገር ፍቅር» የሚባለውን የውሕደት ፓርቲ ትደግፍ ነበር[59]። በአጠቃላይ በአንድ በኩል ኤርትራ ነጻ አገር ሆና እንድትቀጥል የሚፈልጉ የነጻነት ቡድን (Independence Block) በሌላ በኩል ደግሞ የአንድነት ደጋፊዎች (Unionists) ፓርቲዎች ተሰልፈው ነበር። ከፍ ብለው ከተጠቀሱት ፓርቲዎች መካከል ትልቁና የደጋውን ሕዝብ ይወክል የነበረው የአንድነት ፓርቲ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ለማዋሐድ እየተንቀሳቀሰ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኤርትራን የወደፊት ዕድል ለመወሰን ጥናት በሚያደርግበት ወቅት ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሮ ነበር።

በወቅቱ ኤርትራ ነጻነቷን እንድትቀዳጅ የሚሹትም ይሁኑ ሌሎቹ መንግሥታት የሚስማሙበት አንድ ጉዳይ ኢትዮጵያ የዓለብ ወደብ ባለቤት መሆን እንዳለባት ነበር። የኤርትራን ነጻነት ይደግፉ የነበሩት ሶቭዬቶችና ጣልያኖች ሳይቀሩ ዓለብ ለኢትዮጵያ እንደምትገባና ኢትዮጵያ የባሕር በር ባለቤት መሆን እንዳለባት ተቀብለው በዚህ ጉዳይ ዙሪያ የሚነሣ ብርቱ የተቃውሞ ክርክር አልነበረም። ሆኖም በወቅቱ የነበረው የኢትዮጵያና የአብዛኛው የኤርትራ የደጋው ሕዝብ አቋም ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል በመሆኗ ሳትሸራረፍ ከእናት አገሯ መዋሐድ አለባት የሚል ነበር።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያቋቋመው ኮሚሽን ወደ ኤርትራ ከመሰማራቱ በፊት ከሞርዌ በስተቀር ሁሉም የኮሚሽኑ አባላት ኢትዮጵያ የምታራምደውን የአንድነት አቋም የሚጻረሩ ነበሩ። ኤርትራ ሄደው የሕዝቡን ስሜት ከቃኙ በኋላ በርማና ደቡብ አፍሪካ የአቋም ለውጥ አድርገው በመጨረሻ ላይ ኖርዌ አንድነትን ስትደግፍ፣ በርማና ደቡብ አፍሪካ ፌደሬሽንን ደግፈው ፓኪስታንና ጓቴማላ ነጻነትን ደገፉ። የኮሚሽኑ አባላት የአቋም ልዩነት የጋራ ውሳኔ ለማስተላለፍ ስላስቸገረ በ1943 ዓ.ም. ጉዳዩ ወደ ተባበሩት መንግሥታት ቀርቦ ውሳኔ እንዲሰጥበት ተደረገ። ይህ 390A /ኤ/ በሚል የሚታወቀው ውሳኔ «ኤርትራ በኢትዮጵያ ዘውዳዊ ሉዓላዊነት ሥር በፌዴሬሽን እንድትቀናጅ» አድርጎ ኤርትራ ውስጥ ለሚቋቋመው 68 መቀመጫዎች ላሉት ሕገ መንግሥታዊ ጉባኤ ምርጫ ተኪያሂዶ አንድነቶች 32 መቀመጫዎችን፣ ከነጻነት ቡድን ወደ ዴሞክራሲያዊ ቡድን ስማቸውን ለውጠው ለነበሩት 18 መቀመጫዎችን፣ እስላማዊ ሊግ 15 መቀመጫዎችን፣

[59] Bahru Zewde, op. cit., p.182.

ሁለት አነስተኛ ፓርቲዎችና አንድ የግል ተወዳዳሪ 3 መቀመጫዎችን አሸነፉ::[60] ከዚህ ምርጫ በኋላ ሕገ መንግሥቱን ለማጽደቅ የተሰበሰበው ጉባኤ በረቂቅ ሕገ መንግሥቱ ላይ ስምምነት ላይ ሳይደርስ አንድነቶችና እስላማዊ ሊግ ረቂቅ ሕገ መንግሥቱን ሲቀበሉ ዴሞክራሲያዊ ቡድኑ ግን ድምጸ ተዐቅቦ አደረገ:: አስገራሚው ነገር ሕገ መንግሥታዊው ጉባኤ ሌላ ምርጫ ሳያካሂድ ራሱ ሕግ መወሰኛ ምክር ቤት እንዲሆን መወሰኑ ነበር:: ያም ሆነ ይህ መስከረም 1945 ዓ.ም. ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ፈርመውበት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋራ በፌዴሬሽን እንድትቀናጅ ተደረገ::[61] ይህ ውሳኔ በወቅቱ የአብዛኛውን ኤርትራ ሕዝብ ይሁንታ በማንጸባረቁ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ሕጋዊ ዕውቅና አግኝቶ ነበር::

በዚህ መሠረትም ኤርትራ በኢትዮጵያ መንግሥት ሥር ሆና ውስጣዊ ነጻነቷ የተጠበቀ *(autonomous)* ፌዴራል አሐድ ሆነች:: በጸደቀው ሕግ መንግሥት መሠረትም ኤርትራ ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ነጻ ፕሬስ፣ ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ የተለዩበት መንግሥታዊ ሥርዓት፣ እንዲቋቋም ተፈቀደ:: በዚህ አጋጣሚ ኤርትራ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሥር እያለች የሲቪልና የፖለቲካ ነጻነቶች ሥራ ላይ ውለው ሳለ ቀሪው የኢትዮጵያ ግዛት በንጉሠ ነገሥቱ ፍጹም ፈላጭ ቆራጭነት ሥር ስለነበር ከፌዴሬሽኑ በኋላ እነዚህን ሁለት ሥርዓቶች አስታርቆ መሄዱ ትልቅ ፈተና ሆኖ ነበር:: ንጉሡ ወይም በኤርትራ ፌዴራላዊ ግዛት የጸደቀውን ዓይነት ሕገ መንግሥት በቀሪው የኢትዮጵያ ክፍልም ማጽደቅ ወይም ደግሞ የኤርትራውን ሕገ መንግሥት አፍርሰው ፈላጭ ቆራጭነታቸውን በኢትዮጵያና በኤርትራ ተግባራዊ ማድረግ በሚሉ በአገዛዛቸው ላይ መሠረታዊ እንድምታ በሚያስከትሉ ሁለት አማራጮች ተወጥረው ነበር:: በተለይ ፌዴሬሽኑን አፍርሰው አሐዳዊ አገዛዝ ቢመሠርቱ ሊከተል ስለሚችለው መዘዝና አደጋ ከኤርትራ ወደ ኤደን የተዘዋወረው ትሬቫስኪስ የተባለው የእንግሊዝ ባለ ሥልጣን በወቅቱ በሪፖርት መልክ ያቀረበው ትንቢት «*ኢትዮጵያ ኤርትራን በቁጥጥሯ ሥር ለማዋል ያላት ጉጉት ሁሌ የሳቀ ይሆናል:: ይህን ካደረገች የኤርትራውያኑን ቅሬታ በመቀስቀስ ወደ ዐመፅ ሊያመራ ይችላል:: ዐመፁ የውጭ ድጋፍና ጎዘኔታ አግኝቶ ኤርትራንና ራሷን ኢትዮጵያን ሊያምስ ይችላል::..... ኢትዮጵያ በምትወስደው እርምጃ የፌዴሬሽኑን መጻኢ ዕድልና በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ ያሉት አዳዲስ አገሮች ሁኔታ ሊታወክ ይችላል:: ኢትዮጵያ ከፍተኛ ኃላፊነት ይጠበቅባታል*»[62] የሚል ነበር::

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የትሬቫስኪ ሥጋት እውን ሆነ:: የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ፌዴሬሽኑ ከተቋቋመ ከሳምንት በኋላ የፓርቲዎችንና የነጻ ጋዜጦችን እንቅስቃሴ አግዶ ስማዊ የነበረውን የጠቅላይ እንደራሴ ሥልጣን ገደቡን ዐልፎ እንዲጠናከር አደረገ:: የአንድነት ፓርቲ አመራር የነበሩት አቶ ተድላ ባይሩም የኤርትራ መንግሥት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆነው ቢመረጡም በማዕከላዊ መንግሥትና በእንደራሴው ከባድ ተጽዕኖ እየደረሰባቸው ሥራቸውን በሚገባ ለማከናወን ተቸግረው በ1948 ዓ.ም. ሥራውን ለቀው የስዊድን አምባሳደር ሆነው ሲሾሙ በቢትወደድ አስፍሃ ወልደ ሚካኤል ተተኩ:: በ1949 ዓ.ም. በፌዴሬሽኑ ሕገ መንግሥት መሠረት የኤርትራ የሥራ ቋንቋዎች የነበሩት ትግርኛና ዓረብኛ ተሠርዘው በአማርኛ ተተኩ:: የመማሪያ ቋንቋውም እንዲሁ አማርኛ ብቻ ሆነ:: በ1949 ዓ.ም. የኤርትራ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የነበሩት ኢድሪስ መሐመድ አደም በደረሰባቸው ተጽዕኖ ምክንያት ሥራቸውን ለቀው ወደ ካይሮ ሄደው ቀደም ሲል ከተሰደዱት ከአቶ ወልደ አብ ወልደ ማርያም ጋራ ተገናኙ:: አቶ ወልደ አብ ወልደ

---

[60] Henze, P.B., *Eritrea in the First Half of the 20th Century*, p.8.
[61] ibid., p.8.
[62] ibid., p.8.

ግሪያም በእንግሊዝ ይደገፍ የነበረው የትግርኛ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ፤ በእንግሊዞች ይደገፍ የነበረው የሊበራል ፕሮግሬሲቭ ፓርቲ ሊቀመንበርና የኤርትራ ሠራዶኞች ማኅበር መሪ ነበሩ።

ከዚህ ቀጥሎም በኤርትራ የዴሞክራሲያዊ ቡድን መሪ የነበሩት ኢብራሂም ሱልጣን ሽሽተው ካይሮ ገቡ። ሁሉም ከተሰባሰቡ በኋላ በ1950 ዓ.ም. የኤርትራ ነጻነት ንቅናቄ *(Eritrean Liberation Movement)* የሚል ድርጅት በፖርት ሱዳን ከተማ መሠረቱ። በ1950 ዓ.ም. የኤርትራ ሠራተኞች ማኅበር የጠራው አጠቃላይ የሥራ ማቆም ዐድማ በኃይል ተደመሰሰ። በ1951 ዓ.ም. ምክር ቤቱ የፌዴሬሽኑን ሰንደቅ ዓላማ ሠረዘው። በ1952 ዓ.ም. ምክር ቤቱ የኤርትራን ፌዴራል መንግሥት *«በንጉሠ ነገሥቱ አጼ ኃይለ ሥላሴ ሥር የኤርትራ አስተዳደር የሚል ሰያሜ ሰጠው»*። መስከረም 1954 ዓ.ም. በተደረገው ምርጫ ለንጉሠ ነገሥቱ ፍጹም ታዛዥ የሆነ ምክር ቤት ተቋቋመ። በ1955 ዓ.ም. ምክር ቤቱ በአጠቃላይ እንዲፈርስ ተደረጎ ኤርትራ የኢትዮጵያ አሥራ አራተኛዋ ጠቅላይ ግዛት ሆነች።

አጼ ኃይለ ሥላሴና መንግሥታቸው ፌዴሬሽኑ እስኪቋቋም ድረስ ኢትዮጵያ በአጼ ምኒልክ ዘመን ያጣችውን የኤርትራ ግዛትና የባሕር በሯን ለማስመለስ ጥበብ የተሞላበት ትግል አኪያሂደዋል። በወቅቱ አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋራ ለመዋሐድ ያደረገው ትግልም በታሪክ የማይረሳ ነው። ሆኖም አጼ ኃይለ ሥላሴ ያን ሁሉ ለፍተው በኻያኛው ክፍለ ዘመን ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጉትን የፖለቲካ ማሻሻያዎች ከማድረግ ይልቅ ወደ ኋላ የሚጎትቱ እርምጃዎችን በመውሰዳቸው ደጋፊዎቻቸው የነበሩትን ኤርትራውያን ሁሉ እያስከፉ ሄዱ። ከዚህ የተነሣም በወርሐ መስከረም 1954 ዓ.ም. *«የኤርትራ ነጻ አውጪ ግንባር-ጀብሃ ኦል ታሕሪር ኤሪትሪያ»*[63] ተመሥርቶ በግብጽ አሌክሳንደርያ ከተማ ወታደራዊ ሥልጠናውን ካጠናቀቀ በኋላ በምዕራብ ኤርትራ የትጥቅ ትግሉን ጀመረ። ይህ ክስተት ከወቅቱ ዓለማዊና አካባቢያዊ ችግርጋ ተቆራኝቶ ኢትዮጵያን ዳግም ወደ አስቸጋሪ ሽኩቻ የሚከታት ነበር። ወቅቱ ሶቭዬት ኅብረት ልዕለ ኃያልነቷን አረጋግጣ በቀይ ባሕር ተገቢ ቦታዋን ለመያዝ የምትንቀሳቀስበትና በእነ ጀማል ዓብደል ናስርና ሌሎች አክራሪ ዓረቦች የሚመራው የዓረቦች እንቅስቃሴ ኤርትራን እንደዓረቡ ዓለም አንድ አካል የሚያይበት ነበር። በሌላ በኩል የሶቭዬቶችንና የዓረቦችን የአካባቢ ተጽዕና የማይቀበሉት አሜሪካኖች ለመገናኛ ሲሉ *«የቃኘው ሰቲሽን»*ን ጦር ሰፈር በአሥመራ ያቋቋሙበት ነበር። በዚህ ሁኔታ *«ታሪክ ራሱን ይደግማል»* እንዲሉ የቀይ ባሕር አካባቢ ዳግም የዘመኑ ልዕለ ኃያላንና ዓረቦች ዓይናቸውን የጣሉበት የሽኩቻ ስፍራ ሆነ፤ ኢትዮጵያም አካባቢውን ለመቆጣጠር ሲባል የተቀጣጠለው የቋያ እሳት ሰለባ ሆነች።

አጼ ኃይለ ሥላሴ በአንደኛው የዓለም ጦርነት የጎለመሱና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በሥልጣን ላይ የነበሩ መሪ እንደመሆናቸው ከወቅቱ የዓለም ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ ብዙ ዕውቀትና ጥበብን ተምረዋል፤ ልምድም ቀስመዋል። ያገኙትን የዲፕሎማሲ ዕውቀትና ልምድም ለአገራቸው ጥቅም ለማዋል ጥረዋል። ኤርትራን ያለ ጦርነት ከኢትዮጵያ ጋራ እንድትዋሐድና ኢትዮጵያ የባሕር በር ባለቤት እንድትሆን ማድረጋቸው በዲፕሎማሲው ረገድ የተካኑ ለመሆናቸው ማረጋገጫ ቢሆንም በፖለቲካ ረገድ ግን ወቅቱን ያገናዘቡ ማሻሻያዎችን ለማድረግ ዝግጁ ባለመሆናቸው በኤርትራና በቀሪው የኢትዮጵያ ክፍል የሚያባራ ምስቅልቅልን አስከትሏል።

[63] Henze, P.B. *From Federation through War to Independence*, p.2.

አጼ ኃይለ ሥላሴ ከስደት ተመልሰው ሥልጣን ከተቆጣጠሩ በኋላ ትኩረት የሰጡት ኤርትራን ማስመለስና ለኢትዮጵያ የባሕር በር ማስገኘቱ ላይ ብቻ ሳይሆን በጦርነቱ የዳሸቀችውን አገር መልሶ ማቋቋምና ዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዓት መመሥረትም ላይ ነበር። ሆኖም ከስደት መልስ በኋላ ኢትዮጵያን ለማስተዳደርና ለመምራት የሚያስችል በቂ ዓቅም ስላልነበራቸው እንግሊዞች ከእርሳቸው ጋራ ያደረጓቸውን ስምምነቶች መሠረት በማድረግና የነበራቸውን የበላይነት በመጠቀም በመንግሥት ሥራና በተለያዩ የአስተዳደር መስኮች ተሰማርተው ነበር። በተለይ ዘመናዊ ጦርና የፖሊስ ሠራዊት የማቋቋሙን ተግባር እንግሊዞች ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥረውት ነበር። በመሆኑም አጼ ኃይለ ሥላሴ ከጣልያኖች ወረራ በፊት ተጀምሮ የነበረውን የቋሚ ጦር መመሥረት እንቅስቃሴ በተጠናከረ መንገድ ገፍተውበት የተማከለና ከዱሮው እጅግ የተለየ ጦርና የፖሊስ ኃይል ለማቋቋም ችለው ነበር። እንግሊዞች አጼ ኃይለ ሥላሴ የተማከለ አስተዳደር ለማቋቋም ባደረጉት ጥረትም ረድተዋቸው መጀመሪያ ለንጉሠ ነገሥቱ ተጠሪ የሆኑ ሠላሳ አራት የአስተዳደር አሐዶችን ቆይቶም አሥራ ሁለት ጠቅላይ ግዛቶችን አቋቁመው ነበር። የተለያዩ የአስተዳደር ዘርፎችም አደራጅተው አስተዳደሩን ዘመናዊ ለማድረግም በእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች ይገለገሉበት የነበረውን የትምህርት ሥርዓት ተጠቅመው ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችን ከፍተው ነበር።

5. የአጼ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ፈተናዎች

አጼ ኃይለ ሥላሴ ከጣልያን ወረራ በኋላ መጀመሪያ ላይ ብርቱ ፈተና ያጋጠማቸው ከአርበኞች በኩል ነበር። ኢጣልያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት አጼ ኃይለ ሥላሴ አገር ጥለው ሄደው ሳለ በአገር ውስጥ ፀረ-ኢጣልያ የሽምቅ ውግያ ያኪያሂዱ የነበሩ በርካታ ወገኖች ነበሩ። ጣልያኖች ኢትዮጵያን በሙሉ ተቆጣጥረናል ባሉበት ወቅት ቁጥጥራቸው ልል በነበረበት የገጠር አካባቢ የሽምቅ ውግያው በርትቶ ቀስ በቀስ ሽምቅ ውግያው ወደ መላው አገሪቱ ተሰራጨ። እንግሊዞች ጣልያኖችን ሊያጠቁ ሲመጡም በሽምቅ ውግያው ተሰማርተው የነበሩት አርበኞች ከጎናቸው ተሰልፈው ተዋጉ። በመሆኑም ንጉሡ ከስደት ተመልሰው ሥልጣን ሲይዙ «*የሸሸ ንጉሥ መልሶ አይነግሥም፣ ያፈረሰ ቄስ መልሶ አይቀድስም*» እንዲሉ ከአርበኞች ዘንድ ብዙ ተቀባይነት አላገኙም ነበር። በባንዳነት ይከሰሱ የነበሩትን የድል አጥቢያ አርበኞች ሲሾሙና ሲሸልሙም ለአገራቸው የተሟሟቱትን አርበኞች ይበልጥ ቅር አሰኟቸው። አንዳንድ አርበኞችም ካደረጉት ተጋድሎ ጋራ ፍጹም የማይመጣጠን ሹመትና ሥልጣን ሲሰጣቸው በንጉሡ ላይ የነበራቸው ቅሬታና ተቃውሞ በረታ። ለምሳሌ ጀግናው በላይ ዘለቀ በወምስት ዓመቱ የጣልያን ወረራ ጣልያኖችን ያንቀጠቀጠ ስመ ጥር አርበኛ ከመሆኑም ባሻገር አጼ ኃይለ ሥላሴ ከስደት ሲመለሱ አጅቧቸው የዓባይን ወንዝ አሻግሯቸው ነበር። ሆኖም ለጀግንነቱ የተሰጠው ሹመት ደጃዝማችነትና የብቸና አውራጃ ገዥነት ብቻ ነበር። በላይ በሹመቱ እንደተከፋ የገመቱት ንጉሡ ያምፃል የሚል ሥጋት አድሮባቸው የራስነት ማዕርግ ተሰጥቶት ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ እንዲዘዋወር ቢያዙም በላይ ሹመቱን ሳይቀበለው በንጉሠ ነገሥቱና በጠቅላይ ግዛቱ አስተዳድር ላይ ዐመፀ። ዐመፁን ለመመከትም ከመኻል አገር ጦር ተልኮ በላይ ለሦስት ወራት ያህል ከተዋጋ በኋላ ተማርኮ ለእስር ወደ አዲስ አበባ ተወሰደ። በእስር ላይ እያለም ከራስ ኃይሉ ልጅ ከማሞ ኃይሉ ጋራ በመሆን መፈንቅለ መንግሥት ለማኪያሄድ አሲሯል ተብሎ ሁለቱም በስቅላት ተቀጡ።[64] ይህ የንጉሡ ድርጊት ብዙ አርበኞችንና ዐልፎም በአስተዳደሩ ደስተኛ ያልነበረውን የጎጃም ሕዝብ አሳዝኗል።

[64] Henze 2000, op. cit., p. 240.

ንጉሡ ከስደት እንደተመለሱ ያጋጠማቸው ሌላው ፈተና በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የተቀሰቀሰው የወያኔ ዐመፅ ነበር። ይህ በ1934 ዓ.ም. በዋጀራት አካባቢ የተጣለውን የገንዘብ ቅጣት አንከፍልም በማለት የተጀመረው ፀረ-መንግሥት ዐመፅ[65] ወደ ሌሎች የትግራይ አካባቢዎች ተዛምቶ ገና በመቋቋም ላይ የነበረውን የአጼ ኃይለ ሥላሴን የተማከለ አገዛዝ አስደነገጠ። መጀመሪያ ላይ በወያኔዎች የተነሡት ጥያቄዎች ያጠነጠኑት በአካባቢ በሚደርሱ የአስተዳደር በደሎችና ጭቆናዎች ላይ ነበር። ከነዚህ በዐማፅያኑ ከተነሡትና ለወያኔ እንቅስቃሴ መነሻ ከሆኑት የአጼ ኃይለ ሥላሴ ሥርዓት የአስተዳደር በደሎች መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፤

ሀ/ አጼ ኃይለ ሥላሴ ከስደት ከተመለሱ በኋላ የተሾሙት የአውራጃ፣ የወረዳና የምክትል ወረዳ ገዥዎች ብዛት ያለው ታጣቂ አስከትለው በየገጠሩ እየተዘዋወሩ አንድ ገበሬ ቤት ከአሥር እስከ ኻያ ባለሚሎች እየተመሩ እንዲቀለቡ መደረጉ፣

ለ/ በየገበሬው ቤት የተመሩት ሹማምንት በገበሬው ከመቀለባቸውም በላይ ለእጅ መታጠቢያ ዐምስት ብር ለመሶብ ማንሻ ደግሞ ተጨማሪ ዐምስት ብር ማስከፈላቸው፣

ሐ/ ገንዘብ መክፈል አልችልም ያለ ገበሬም በገመድ እየታሰረ እንዲሰቃይ መደረጉ፣

መ/ ገበሬውን ከሚስቱና ከልጆቹ ፊት እያሰቃዩ የሞራል ውድቀት ማድረሳቸው፣

ሠ/ ሹማምንቱ ደስ የሚሏቸውን የገበሬ ሚስትና ሴት ልጆች መድፈራቸው፣

ረ/ ሹማምንቱ የገበሬውን የእርሻና የግጦሽ መሬት እየነጠቁ ማረሳቸው፤[66]

እነዚህና ሌሎች በደሎች የደረሰባቸው ገበሬዎች በድብቅ መመካከር ጀመሩ። በተለይ ዋጀራቶች የባህላዊ ልምዳቸውን መሠረት አድርገው ሕዝባዊ ስብሰባዎችን እየጠሩ በሹማምንቱ ላይ ማመፅ እንዳለባቸው ተስማሙ። ይህን ስምምነታቸውንም ለእንደርታ ሕዝብ አሳውቀው ሕዝቡም ዓረና[67] ብሎ ከነእርሱጋ መስማማቱን ገለጸላቸው። ከዚያም መላው የራያ፣ የምሥራቅ ትግራይና የከፊል ተምቤን ሕዝብ በዐመፁ ተስማምቶ በአጼ ኃይለ ሥላሴ የተሾሙትን ባለሥልጣናት በሙሉ አስወገደ። ቀጥሎም የወያኔው ኃይል ኩይላ ላይ የነበረውን በእንግሊዞች የተደራጀውንና በሻለቃ /ኋላ ላይ ጄኔራል/ ኢሳያስ ገብረ ሥላሴ የሚመራውን ጦር አጥቅቶ አቸነፈ። እንዳ እየሱስ ላይ ሰፍሮ የነበረውንና በሻለቃ /ኋላ ላይ ሜጀር ጄኔራል/ ተድላ መኮንን እና በደጃዝማች ገብረ ሕይወት መሸሻ የሚመራውን ኃይል አጥቅቶም የትግራይን ዋና ከተማ መቀሌን ተቆጣጠረ። ከዚያም ወደ አላጄ አምርቶ የመከላከል ውግያዎችን ለማኪያሄድ ተዘጋጀ። አጼ ኃይለ ሥላሴም በእንግሊዞች የሠለጠነውን አዲሱን ጦራቸውን አሰልፈው የእንግሊዝ መኮንኖችንም በመሪነትና በተዋጊነት አሳትፈው ወያኔዎችን ተዋጉ፤ ዐመፁንም ተቆጣጠሩ። *«ስለሆነም ዐመፁን ለማዳፈን የተቻለው እንግሊዞች ጣልቃ በመግባታቸውና እያንዳንዳቸው አርባ ፓውንድ የሚመዝኑ 116 ቦምቦች ከአውሮፕላን በመጣል ሕዝቡን ከደበደቡ በኋላ ነበር። በዚህ አሳዛኝ መቀሌና ኑዋሪዎቿ ሳይቀሩ ተደብድበዋል።»*[68]

---

[65] ዝኒ ከማሁ፣ በላይ ግደይ፣ ገጽ 229

[66] አስፋው በላይ፣ *ዝክረ አባ ደብልቅ በላይ ወልድዬ/ፈታውራሪ/*፣ 1999 ዓ.ም.፣ ገጽ 152-153

[67] አቶ አስፋው በላይ፣ እንደተረጎሙት፣ *«ተባብረናል፤ ተስማምተናል፤»* ማለት ነው።

[68] ክፍሉ ታደሰ፣ 1991፣ *ያ ትውልድ፣ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ታሪክ፣ ክፍል 1፣ ከአጀማመሩ እስከ 1967 ዓ.ም. ድረስ፣ The Generation* ከተባለው መጽሐፉ የተተረጎመ፣ ኢንዲፔንደንት አሳታሚዎች፣ ገጽ 16

የወያኔ ዐመፅ ከከሸፈ በኋላ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የወሰደው የበቀል እርምጃ ከዱሮው ብሶ እያንዳንዱ ቤተሰብ ለዘመተው ጦር አበል አሥር ማርተሬዛ ብር እንዲከፍል ተገደደ፤ ትጥቁንም ተነጠቀ። ይባስ ብሎም የራያ መሬት ተነጥቆ ለባለ ሥልጣኖች በቀላድነት ተከፋፈለ።[69] የወያኔው እንቅስቃሴ ሊቀመንበር የነበሩት ብላታ ኃይለ ማርያምና በአላጄና በሌሎች ውግያዎች የዐማፅያኑ የጦር አዛዥ የነበሩት ባሻይ ጉግሳ እንዲሁም ሌሎች ታዋቂ አርበኞችም ለግዞትና ለእስር ተዳረጉ። አጼ ኃይለ ሥላሴ የወሰዱት የቅጣት እርምጃ በትግራይ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ የሞራል ውድቀት፣ የንብረት መጥፋትና የሕዝብ ዕልቂት አስከተለ። የአጼ ኃይለ ሥላሴ ብልሹ አስተዳደርና እሱን ተከትሎ የሕዝቡን ጥያቄ ከማስተናገድ ይልቅ ተበዳዩን ጥፋተኛ አድርገው ያደረሱት ጥፋት ጊዜውን ጠብቆ ለሌላ ዐመፅ በር መክፈቱንና ብዙ መዘዝ ማስከተሉን ኋላ ላይ በስፋት እመለከተዋለሁ።

አጼ ኃይለ ሥላሴ በሺሕ ዘጠኝ መቶ ሠላሳዎቹና በሺሕ ዘጠኝ መቶ አርባዎቹ የተማከለ አገዛዛቸውን ለማጠናከር ጣልያኖች የገነቧቸውን መሠረተ ልማቶች በተለይ መንገዶችን፣ እንግሊዞችና አሜሪካኖች የሰጧቸውን ዘመናዊ ወታደራዊ እርዳታና ሥልጠና፣ እንዲሁም ዘመኑ ያፈራቸውን የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ቀድሞ ከአንዱ የአገራችን ጫፍ ወደ ሌላው የአገራችን ጫፍ ለመሄድ ወራት የሚፈጀውን ጉዞ በጥቂት ቀናት ቢያስፈልግም በሰዓታት እንዲፈጸም አስተዋፅኦ አድርገዋል። ይህን የተሻሻለ መዋቅር ተጠቅመውም በጠቅላይ ግዛቶች የተሸነሸኑ የአካባቢ አስተዳደሮችና በጣም የተማከለ የአገዛዝ ሥርዓት በመመሥረታቸው «*የተማከለ መንግሥት የማቋቋሙን ጉዳይ አጼ ቴዎድሮስ ዐለሙት፤ አጼ ዮሐንስ በዝርዝር ገለጹት፤ አጼ ምኒልክ አጠናከሩት፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ ከፍጻሜ አደረሱት*[70]» ተብሏል። ሆኖም በኻያኛው ክፍለ ዘመን የሚቋቋም መንግሥት ዴሞክራሲያዊ ሆኖ ሕዝቡን ሳያሳትፍ የተማከለና ዘመናዊ መሆኑ ብቻ በቂ ባለመሆኑ አጼ ኃይለ ሥላሴ የተከተሉት የአገዛዝ ዘይቤ ከጊዜው ጋራ የሚራመድ አልነበረም። አጼ ኃይለ ሥላሴ ለይስሙላ ሥልጣን ለማከፋፈል ሲባል የሕገ መንግሥት መሻሻያዎች ቢያደርጉም፣ የሕግ መምሪያና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቶችን ቢያቋቁሙም፣ ምንም በማያወላዳ ሁኔታ ሥልጣንን በገዛ እጃቸው አከማችተው ነበር።

የአጼ ኃይለ ሥላሴ ፈላጭ ቆራጭነት ያስከፋው አዲሱን ትውልድና ተራውን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ሥልጣኔን ያስጠብቅልኛል ብለው ያቋቋሙትን የጦር ኃይልና እላቸውን ብቻ ለመጠበቅ የተቋቋመውን የክቡር ዘብንም ጭምር ነበር። በመሆኑም የማይነኩና የማይደፈሩ ይመስሉ የነበሩት ንጉሠ ነገሥት በታኅሣሥ 1953 ዓ.ም. በክብር ዘቦቻቸው የሚመራ መፈንቅለ መንግሥት ተካሂደባቸው። በጄኔራል መንግሥቱ ንዋይና በወንድማቸው ግርማሜ ንዋይ የተመራውና ሌሎችን የፖሊስና የደኅንነት መኮንኖች ያሳተፈው መፈንቅለ መንግሥት ባይሳካም ሙከራው ሥርዓቱ መለወጥ እንዳለበት የሚያመለክት ነበር። መፈንቅለ መንግሥቱ ለመክሸፉ ዋናው ምክንያት የጦር ሠራዊቱን በሙሉና በሥርዓቱ ወሳኝ ሚና የነበራቸውን ተቋማት ማለትም የጦር ሠራዊቱን፣ ቤተክህነትንና ዲፕሎማሲያዊ ማኅበረሰቡን ያለመሳተፉ ነበር። ተራው ዜጋም ዝግጁ ስላልነበር ለመፈንቅለ መንግሥቱ ቁርጠኛ ድጋፍ አልሰጠም ነበር። በመሆኑም የፖሊስ ሠራዊት ዋና አዛዥ የነበሩት ጄኔራል ጽጌ ዲቡ፣ የደኅንነት ኃላፊ የነበሩት ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁና አውራጃ አስተዳዳሪ የነበሩት ግርማሜ ንዋይ በግርግሩ በተፈጠረው የተኩስ ልውውጥ ሕይወታቸውን ሲያጡ ዋነኛው የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪና የክብር ዘቡ አዛዥ የነበሩት መንግሥቱ ንዋይ ተማርከው በስቅላት ተቀጥተዋል።

---

[69] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 17

[70] Teshale Tibebu. 1995. *The Making of Modern Ethiopia: 1896-1974.* The Red Sea Press Inc., p. 31.

በወቅቱ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ላይ የተደቀነባቸው ሌላው ፈተና በሶማልያና በደጋፊዎቿ የዓረብ አገሮች አማካይነት የተቀሰቀሰው ጦርነት ነበር። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት አጼ ኃይለ ሥላሴ በፓሪሱ የሰላም ኮንፈረንስ ደቡብ ሶማልያ ወደ ኢትዮጵያ መጠቃለል አለባት የሚል አቋም ቢይዙም ሳይሳካላቸው ቀርቶ ሶማልያ በ1952 ዓ.ም. ነጻነቷን ተቀዳጅታ በጂቡቲ[1] በኬንያና በኢትዮጵያ የተበታተኑትን ሶማልያውያን አሰባስባ ደቡብ ሶማልያንና ሶማሊላንድን አዋሕዳ አንዲት ታላቅ ሶማልያን ለመፍጠር ተነሣች።

ኢብራሂም ኤጋልና ሼርማርኬ የሚመሯት የአዲሲቷ ሶማልያ መንግሥት ታላቅዋን ሶማልያ የመመሥረት ሕልማቸውን ለማሳካት አስቀድመው ያተኮሩት በምሥራቅ ኢትዮጵያ በኦጋዴን እሚኖሩት የሶማሌ ተወላጆች ላይ ነበር። በመሆኑም የሶማልያን የወጣቶች ሊግ *(Youth League)* በመጠቀም የመስፋፋትና የአንድነት መፈክራቸውን አጠናክረው ሲያስተጋቡ ቆይተው በ1956 ዓ.ም. ኦጋዴንን ከኢትዮጵያ ለመውሰድ ከባድ ጦርነት ገጠሙ። ሆኖም ጦርነቱ በኢትዮጵያ የበላይነት ተጠናቆ ኦጋዴንን ከኢትዮጵያ የመገንጠሉ ሙከራ ሊከሽፍ ቻለ። በዚያን ጊዜ ሶማልያን ይህን ጀብዱ እንድትፈጽም ይገፋፏት የነበሩት በቀይ ባሕርና በዓባይ ወንዝ ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ፍላጎት የነበራቸው ግብጾች እንደነበሩ ታሪክ ይዘግባል። *«የኤርትራውያን እንቅስቃሴ በካይሮ እየተደራጀ በነበረበት ወቅት ግብጻውያን በአፍሪካ ቀንድ ሌላ የተጠናከረ የእስላማዊ ዓረብ ይዘታ ለመፍጠር ፈለጉ። ይህን እውን ለማድረግ የጣሩትም የኢትዮጵያ ግዛት የሆነውን ኦጋዴንንና በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት የምትገኘውን የሐረርን ከተማ እናስመልሳለን ያሉትን ሶማሌዎች በማጠናከር ነበር። በመጀመሪያዎቹ የሶማልያ የነጻነት ዓመታት ግብጻውያን በሶማልያ የነበራቸው ተጽዕኖ ከፍተኛ ነበር።»*[71] ከካይሮ ይሰራጭ የነበረው የግብጽ የሬድዮ ፕሮግራምም ከኤርትራ ነጻነት ባሻገር ስለታላቋ ሶማልያ መፈጠር ይቀሰቅስ ነበር።[72] ግብጾችና ሌሎች ዓረቦች ኢትዮጵያን አዳክመው ቀይ ባሕርን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቆጣጠር ከነበራቸው ፍላጎት የተነሣ ለሶማልያ ከፍተኛ ድጋፍ ቢያበረክቱም በኦጋዴን ጦርነት ወቅት በኢትዮጵያና በሶማልያ መካከል የነበረው የኃይል ሚዛን ተመጣጣኝ ስላልነበር ሶማልያ ተሸንፋ ኦጋዴንን የመውሰድ ዕቅድዋን ለማዘግየት ተገደደች።

ዓረቦች በተለይም ግብጾች በምሥራቅ ኢትዮጵያ የተደረገው የኦጋዴን ጦርነት ቢከሽፍባቸውም ሌሎች የመገንጠል እንቅስቃሴዎችን ከመደገፍ ወደ ኋላ አላሉም። የኤርትራን የመገንጠል እንቅስቃሴ በመደገፍ ወታደራዊና ዲፕሎማሲያዊ እርዳታ ያበረከቱ ነበር። አቶ ወልደ አብ ወልደ ማርያም እ.አ.አ. ከ1953 ዓ.ም. ጀምሮ መቀመጫቸውን ካይሮ ላይ በማድረግ በሬድዮ ካይሮ አማካይነት ፀረ-ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳ ያሰራጩ ነበር። የኤርትራ ነጻ አውጪ /ጀብሃ/ የተቋቋመውም በናስርና በዓረብ ብሔርተኝነት ጉያ ውስጥ እንደነበር[73] ቀድሜ ገልጪዋለሁ። በሌላ በኩል በሺሕ ዘጠኝ መቶ ኀምሳዎቹ መጨረሻና በሺሕ ዘጠኝ መቶ ስድሳዎቹ መጀመሪያ ላይ በእነዋቆ ጉቱ የሚመራ የኦሮሞ የነጻነት እንቅስቃሴም በደቡብ ኦሮሚያ ባሌ ውስጥ ተቋቁሞ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ሥርዓት የአስተዳደር በደል የተማረሩ ዐማፅያንን አሰባስቦ ነበር። ኦሮሞዎች ከአጼ ምኒልክ ጀምሮ በጭሰኛና በነፍጠኛ ሥርዓት ሥር ወድቀው በተለይ አጼ ምኒልክ ሊቆጣጠሯቸው ያደረጉትን ዘመቻ ሲመክቱ ከባድ ጭፍጨፋ ደርሶባቸው ነበር። በዚህ ዘመቻ ይበልጥ የተጎዱት የደቡብ ኢትዮጵያ ኦሮሞዎች በተለይም የአጼ ምኒልክን ዘመቻ ለአራት ዓመታት ያህል የመከቱት የአሩሲ ኦሮሞዎች ነበሩ። መጨረሻ ላይ ግን በ1879 ዓ.ም. የአጼ ምኒልክ

[1] Haggai, E. 1994, op.cit., p.134.
[2] ibid., p.138.
[3] ibid., p.130.

አጎት በሆኑት በራስ ዳርጌ የተመራው ግዙፍ ጦር አዙሌ[74] ላይ አቸነፋቸው። እነዚህ በአጼ ምኒልክና በኦሮሞዎች መካከል የተደረጉ ውግያዎች የተውት ጠባሳ ሳያበቃ ኦሮሞዎች በአጼ ኃይል ሥላሴ ጊዜም የተሻለ አስተዳደር አላገኙም። ሰፊና ለም የሆነው የባሌ የእርሻና የግጦሽ መሬት በመጤዎች ቁጥጥር ሥር መዋሉና እነዚህ ለዘመናት ከንጉሡ ቁጥጥር ውጭ የነበሩ አካባቢዎች ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ሹማምንት እንዲገብሩና የጉልበት አገልግሎት እንዲሰጡ መደረጉ በኦሮሞ ተወላጆች ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታ አሳድሮ ነበር።

ሁኔታዎች በቋፍ እያሉ በ1952 ዓ.ም. ነጻ የወጣችው ሶማልያ ሐረርጌ፣ አርሲ፣ ባሌና ደቡብ ሲዳሞ ከኢትዮጵያ ተገንጥለው ነጻ እንዲወጡ ዐቅዳ «*የተባበሩት የምዕራብ ሶማልያ ነጻ አውጪ ግንባር*» የሚባል እንቅስቃሴ ሞቃድሾ ላይ አደራጀች። በ1955 ዓ.ም. በግንባሩ ከታቀፉት ኃይሎች መካከል «*የኦጋዴን ነጻ አውጪ ግንባር*» የሚባለው ህልውናውን እውን አደረገ። በርካታ በአጼ ኃይለ ሥላሴ የተከፉ ኢትዮጵያውያን ኦሮሞዎችና ሶማሌዎችም በሞቃድሾ መጠግያ አገኙ። ከነዚህ መካከልም ዋቆ ጉቱ የተባሉት በሶማልያ የገንዘብ፣ የመሣሪያና የሥልጠና ድጋፍ ካገኙ በኋላ በ1957 ዓ.ም. ፀረ የኢትዮጵያ መንግሥት የትጥቅ ትግል ጀመሩ። በዋቆ ጉቱ የሚመራው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት ወቅት ከ12 እስከ 15 ሺሕ ተዋጊዎችን አሰልፎ ነበር። እንቅስቃሴው ከነጭ ለባሽና ከብሔራዊ ጦር ቁጥጥር ውጭ በሆነበት ወቅትም መንግሥት የአየር ኃይሉን አሰማርቶ በከብቶችና በተመረጡ መንደሮች ላይ ድብደባውን አጧጥፎ፤ ጦሩንም ወደ አካባቢው አሰማርቶ ነበር። ይህ እንቅስቃሴ ከዓረቦችጋ የነበረው ግንኙነት ግልጽ ባይሆንም በጠቅላይ ሚኒስትር ኢብራሂም ኢጋል የሚመራው የሶማልያ መንግሥት የመሣሪያ፣ የቁሳቁስና የሥልጠና እርዳታ ያደርግለት እንደነበር ይታወቃል።[75] ወደ ኋላ ላይ የእንቅስቃሴው መዳከም አንዱ ምክንያትም ይህ ከሶማልያ መንግሥት ይገኝ የነበረው ድጋፍ መቋረጡ እንደነበር ተዘግቧል። በመጨረሻም የእንቅስቃሴው መሪ የነበሩት ዋቆ ጉቱ ከኢትዮጵያ መንግሥትጋ ተደራድረው እጃቸውን ሰጡ። በባሌ ተቀስቅሶ የነበረውን ዐመፅ በማዳከም ረገድ የባሌ ጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪ ሆነው ተሹመው የነበሩት የኦሮሞ ተወላጅ ጄኔራል ጃገማ ኬሎ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

በወቅቱ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከተለያዩ ወገኖችና የጎብረተሰብ ክፍሎች ተቃውሞ ቢገጥመውም ጥያቄዎችን በአግባቡ ለመመለስና ራሱን ለማሻሻል ዝግጁ አልነበረም። ቀደም ሲል ከተገለጹት መገንጠልን ከሚያቀነቅኑ የትጥቅ ትግል እንቅስቃሴዎችና ከነጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በተጨማሪ የተለያዩ በቅጡ ያልተደራጁ የመፈንቅለ መንግሥትና የዐመፅ ሙከራዎችም ነበሩ። ከነዚህ መካል የነደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት፤ የሜጫና ቱለማ ማኅበር መሪዎችና አባላት የነበሩት የእነ ጄኔራል ታደሰ ብሩ[76] እና የእነ መቶ አለቃ ማሞ መዘምር፤ ሙከራዎች ተጠቃሽ ናቸው። ከዚህ ሌላ ጎጃም ውስጥ በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ ክፍለ አገራዊ የገበሬዎች ዐመፅም ተቀስቅሶ ከሽፏል። የጎጃም ሕዝብ የጣልያኖችን ወረራ በመመከት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ቢያደርግም፤ ንጉሡ ከስደት ከተመለሱ በኋላ በዓይነ ቁራኛ እያዩት የአካባቢውን ተወላጆች አስተዳዳሪ ላለማድረግ ከሌላ ጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪዎች እያመጡ ይሾሙ ነበር። የጎጃም ሕዝብ ዋነኛ ቅሬታ ግን የሹመቱ ሳይሆን ከዐቅሙ በላይ የሚጣልበት ግብርና ለዓመታት የተከማቸውን ውዝፍ ግብር እንዲከፍል መጠየቁና ብልሹ አስተዳደር መንሰራፋቱ ነበር። በመሆኑም፤ አብዛኛው የጎጃም ሕዝብ ዐምፆ ፖሊስ ጣብያዎችን፣ የአስተዳደርና የግብር

[74] Bahru Zewde, op.cit. p.43.
[75] Henze 2000, op.cit., pp. 263-264.
[76] Bahru Zewde, op.cit., pp. 211-261.

ሰብሳቢ ማዕከላትን ተቆጣጥሮ ነበር። ዐመፁ ከ1960 ዓ.ም. እስከ 1962 ዓ.ም. ቀጥሎ ሥርዓቱን በማስደንገጡ ከመኻል አገር እግረኛ ታጣቂዎች ብቻ ሳይሆኑ የአየር ኃይልም ተልኮ ሕዝቡን ደበደበ። በ1961 ዓ.ም. ሞጣ አካባቢ የገበሬ መኖሪያ ቤቶች ሲቃጠሉ እኔ ራሴም ተመልክቻለሁ።[77] ዐመፁ ያሠጋው የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በመጨረሻ ለዓመታት የተከማቸ ውዝፍ ግብር የመሰብሰብ ትእዛዙን በመሠረዙ ዐመፁ ሊቆም ቻለ።

ተደራጅተው ይኪያሄዱ ከነበሩት የትጥቅ ትግልና የገበሬ ዐመፅ እንቅስቃሴዎች ሌላ ከ1950ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ በከተማም የሲቪል እንቅስቃሴዎችም ተጠናክረው ነበር። የእነዚህ እንቅስቃሴዎች ተሳታፊዎች የሚያነሷቸው አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች ያጠነጠኑት በመብትና በኑሮ መሻሻል ዙሪያ ሲሆን ከነዚህ እንቅስቃሴዎች መኻል በ1958 ዓ.ም. እና በ1959 ዓ.ም. የተደረገውን የአየር መንገድ ሠራተኞች ዐድማ፣ በ1959 ዓ.ም. እና በ1960 ዓ.ም. የተኪያሄዱትን የአውቶቡስ ሹፌሮችና የማተሚያ ቤት ሠራተኞች ዐድማ፣ እንዲሁም በ1965 ዓ.ም. የተኪያሄደውን የባንክ ሠራተኞች ዐድማ መጥቀስ ይቻላል።[78]

የአጼ ኃይለ ሥላሴን አገዛዝ በመቃወም ገኖ የወጣው ሌላው የጎበረተሰብ ክፍል ተማሪው ነበር። ከ1953 ዓ.ም. መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ ጎበረተሰቡ በተለይ ደግሞ የተማረው ክፍል አገሪቱ በአስቸጋሪ ሁኔታ ላይ እንዳለች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ተገንዝቦ ነበር። በመሆኑም የኑሮ ችግሮችን የተመለከቱ ጥያቄዎችን ያነሣ የነበረው ብቸኛው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በኮሌጅ ደረጃ ከተደራጀ በኋላ አንዳንድ የአካዴሚክ ነጻነት ጥያቄዎችን ሲያነሣ፤ ከተወሰነ ጊዜ በኋላም ተማሪዎችም ከበድ ያሉ የፖለቲካ ነጻነት ጥያቄዎችን ማንሣት ጀመሩ። ለአብነት፤ በገጠር የነበረውን ድኽነትና ኢ-ፍትሐዊ የመሬት ይዞታ ሥርዓት በመቃወም የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ተማሪዎች እ.አ.አ. በ1965 ዓ.ም. «መሬት ለአራሹ»[79] የሚል መፈክር እንግበው ፓርላማ ድረስ ሄደው ያደረጉት ሰላማዊ ሰልፍ ተጠቃሽ ነው። ሥርዓቱም ይህ የተማሪዎች ሰልፍና ጥያቄ ስላስደነገጠው ልክ በዓመቱ እ.አ.አ. በ1966 ዓ.ም የመሬት ይዞታ ማሻሻያ ሚኒስቴር ቢያቋቁምም የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መሬትን በማከፋፈል ረገድ ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወስድ ቀረ።

ተማሪዎች እ.አ.አ. እስከ 1967 ዓ.ም. ድረስ ያራምዱት የነበረው እንቅስቃሴ ዓላማ በሥርዓቱ ላይ ተጽዕኖን በማሳደር የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ ማስገደድ ስለነበር እንቅስቃሴው ሁሉ በሥርዓቱ ማዕቀፍ ሆኖ ሊደረጉ በሚችሉ ለውጦች ላይ ያተኮረ ነበር። ከ1967 ዓ.ም. በኋላ ግን ተማሪዎች በተሻለ መንገድ ተደራጅተው ላቅ ያሉ መፈክሮችን ማንገብና ጥልቅ የሆኑ ጥያቄዎችን ማንሣት ጀመሩ። በፖለቲካ ሥርዓቱ ግዕቀፍ መፍትሔ ከመሻት ይልቅ የፖለቲካ ሥርዓቱን ለመቀየር ተነሥተው[80] «ታገል» ወይም «Struggle» በሚል ርእስ የተማሪዎች ማኅበር መጽሔት ማተም ጀመሩ። እንዲሁም ሁሉንም የዩኒቨርሲቲ ኮሌጆች የሚያካትት «የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር» (Union of University Students of Addis Ababa - USUAA) የሚል ማኅበር አቋቋሙ። እ.አ.አ. በ1968 ዓ.ም. የዩንቨርሲቲው ተማሪዎች ስድስት ኪሎ በሚገኘው የመኮንን አዳራሽ የተከፈተውን የፋሽን ትርኢት የአሜሪካን ባህላዊ ኢምፔርያሊዝም ያንጸባርቃል በማለት

---

[77] የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ ቢንግ ቴይለር ከሚባል አሜሪካዊ የሰላም ጓድ አስተማሪዬ ጋራ በገና በዓል ዕረፍት ወደ ደብረ ማርቆስና ሞጣ ስንሄድ ሞጣ አካባቢ በርካታ ቤቶች ሲቃጠሉ አይተን ቤቶቹ ለምን እንደተቃጠሉ ስንጠይቅ ዐመፅ የቀሰቀሱ ገበሬዎች ቤቶች እንደሆኑ ተነግሮን ነበር።

[78] ዝኒ ከማሁ፣ ዶ ትውልደ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 31

[79] Balsvik, R.R. 2007. *The Quest for Expression: State and the University in Ethiopia Under Three Regimes, 1952-2005*, Addis Ababa University Press, pp. 22-23.

[80] ibid., p. 27.

ተቃወሙት። በሚቀጥለው ዓመት ማለትም በ1961 ዓ.ም. የተማሪዎቹ እንቅስቃሴ ሌላ ፈር ይዞ ሥርዓቱን መቃወሙ፣ ሰላማዊ ሰልፎችን ማኪያሄዱንና ትምህርት ማቋረጡን አጧፈፉ። እንቅስቃሴው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ወጥቶ፣ በአዲስ አበባና በሌሎች ትላልቅ ከተሞች ወደሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተዛመተ። ከ1956 ዓ.ም. ጀምሮ፣ «ብሔራዊ አገልግሎት» ይሰጡ የነበሩ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም ይህ እንቅስቃሴ ወደ ጠቅላይ ግዛቶች እንዲስፋፋ አስተዋፅኦ አደረጉ።

በ1961 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ፖለቲካ ሂደት ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳደረው «*የብሔር ጥያቄ በኢትዮጵያ*» የሚለው የዋለልኝ መኮንን ጽሑፍ በታገል መጽሔት ታትሞ ወጥቶ መነጋገሪያ ሆነ። የተማሪው እንቅስቃሴ ጣሪያው ላይ በመድረሱ የሚነሡት ጥያቄዎች ከተማሪው ማዕቀፍ ውጭ መስተናገድ እንዳለባቸውም ግልጽ ሆነ። ከዚህ በኋላ ተማሪዎች በአገሪቱ የሚከሰቱ ወቅታዊ ጉዳዮችና መሠረታዊ የፖለቲካ ጥያቄዎችን እያነሡ ከሥርዓቱ ጋራ መጋጨት ጀመሩ። ከነዚህ ተማሪዎችን በስፋት ካንቀሳቀሷቸው ጉዳዮች አንዱ በ1965 ዓ.ም. በወሎና በትግራይ የተከሰተው ረሀብና ድርቅ ነበር። ተማሪዎች በድርቁ ለተጎዱት ረሀብተኞች የተቻላቸውን ያህል እርዳታ ሲያደርጉ በተጓዳኝ የረሀቡ መነሻ ከመሠረቱ ታይቶ መፍትሔ እንዲያገኝ ጥያቄ አቀረቡ። እንዲሁም በትምህርትና በሌሎች ዘርፎች የታዩትን የፖሊሲ ችግሮች በመቃወም ሰልፍ ወጡ።

የተማሪዎች እንቅስቃሴ በአገር ቤት ብቻ ሳይሆን በውጭ አገርም በተለይ በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ ይኖሩ በነበሩ ተማሪዎችም ዘንድ ይኪያሄድ ነበር። ምንም እንኳን ከአገራችን ነባራዊ ሁኔታ ቢርቁም ከኢትዮጵያ ውጭ የነበሩት ተማሪዎችም ከሥርዓቱ ዐፈና ገለል በማለታቸው ጊዜያቸውን በበለጠ ለፖለቲካዊ ጥናትና ምርምር ሊጠቀሙበት ይችሉ ነበር። በተናጠል ከመታገል መደራጀትን መርጠውም በየአካባቢያቸው የተማሪ ማኅበራት ማቋቋም ጀመሩ። በዚህም መሠረት «*የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅብር በሰሜን አሜሪካ*» እና «*የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በአውሮፓ*» የተባሉ ታዋቂ ማኅበራት ተመሠረቱ። እነዚህ ማኅበራት የየራሳቸውን ልሳናት አቋቁመው የሰሜን አሜሪካው «*ቻሌንጅ*» እና የአውሮፓው «*ታጠቅ*» መጽሔቶች በውጭና በአገር ውስጥ የነበረውን ተማሪ ንቃተ ኅሊና አዳብረዋል።

በሺሕ ዘጠኝ መቶ ሰሳዎቹ በሥርዓቱ የተከሰቱትን ችግሮች ለመቃወም ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች ተጧጡፈው ነበር። የገበሬዎች ዐመፅ፣ የኤርትራ የትጥቅ ትግል፣ የሲቪል ማኅበራት ዐድማና ሰልፍ፣ የተማሪዎች መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴዎች፣ ተገጣጥመው መሠረታዊ መፍትሔ የሚሹ ሆኑ። ሥርዓቱም በበርካታ የሕዝብ ጥያቄዎች ቢወጠርም ለጥያቄዎቹ መፍትሔ ለመስጠት ዝግጁ አልነበረም። በሌላ በኩል ደግሞ ለተከሰቱት ችግሮች መሠረታዊ መፍትሔ ለመስጠትና ሥርዓቱን ለመለወጥ በርካታ ወገኖች ጥረት ማድረግ ጀመሩ። ወቅቱም አገራችን መንታ መንገድ ላይ የቆመችበት ሆነ።

6. የፖለቲካው መጧጧፍና የአዱው ሥርዓት መጨረሻ ቀናት

6.1 አዲስ የትግል አቅጣጫ

የተማሪዎች እንቅስቃሴ ጣራው ላይ ሲድረስ አንዳንድ ሩቅ አሳቢ ተማሪዎችና ምሁራን እንቅስቃሴው ከተማሪው አመራር ወጥቶ ሌላ ፈር መያዝ እንዳለበት ተገንዝበው ተማሪው ሊኖረው የሚችለው ሚና በሲቪል ማኅበረሰቡ ማዕቀፍ የሚታይ እንጂ ከዚያ የዘለለ ሊሆን እንደማይችል በጥብቅ ያሳስቡ ነበር። ተማሪው የፖለቲካ ፓርቲ ሚና እጫወታለሁ ካለ

በሕዝቡ አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ገምተውም ከእንግዲህ ሥርዓቱን በላቀ ደረጃ ለመፋለም በቅጡ መደራጀት ያስፈልጋል ይሉ ነበር። ሥርዓቱም በሕጋዊ መንግድ መደራጀትንና በይፋ ፓርቲ መሥርቶ መንቀሳቀስን አይፈቅድ ነበርና በጎቡእ መደራጀት ተጀምሮ በመላው አገሪቱ በርካታ ጎቡእ የጥናት ሕዋሶችና የተወሰኑ የፖለቲካ ቡድኖች ተፈጠሩ።

እነዚህ የጥናት ሕዋሶችና ቡድኖች ንቃተ ኅሊናቸውን ለማዳበር በጥናት ተጠምደው የፖለቲካ ጉዳዮችን በተለይ ከማርክሲያዊ-ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለም አኳያ መመልከት ጀምሩ። የማርክስ፣ የኤንግልስ፣ የሌኒን፣ የስታሊን፣ የማኦ ዜ ዱንግ፣ የቼ ጉቬራ፣ የካስትሮ፣ የፋኖን፣ ወዘተ... የግራ ዘመም መጻሕፍት ቀን ከሌት እየተነበቡ አንዳንዶቹም በአንዳንድ የአገሪቱ መሠረታዊ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ በማተኮር ስለብሔር ጥያቄ፣ ስለኤርትራ ጥያቄ፣ ስለመሬት ይዞታ፣ ስለፊውዳሉ ሥርዓት ባሕርያት፣ ስለኢምፔሪያሊዝም፣ ስለአግራጭ የትግል ስልቶች፣ ወዘተ... ይወያዩ ነበር። አንዳንድ የጥናት ሕዋሶችና የፖለቲካ ቡድኖችም ስለትጥቅ ትግልና ስለወታደራዊ ጉዳዮች ከመወያየት ዐልፈው ራሳቸውን ለትጥቅ ትግል ማዘጋጀት ጀመሩ። ይህ ሁሉ ይደረግ የነበረው የአጼ ኃይለ ሥላሴ ሥርዓት ከመገርሰሱ ቀደም ብሎና በደርግ የመጀመሪያ የሥልጣን ዓመታት ነበር። ምንም እንኳን በጎቡእ የተደራጁት የተለያዩት የጥናት ሕዋሶችና ቡድኖች የርዕዮተ ዓለም፣ የፖለቲካና የትግል ስልት ልዩነቶችን ቢያንጸባርቁም ሁሉም ፈጣንና ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣትና በአገራችን የነበረውን ጨቋኝ ሥርዓት ለማስወገድ ፍላጎት ነበራቸው።

እነዚህ የጎብረተሰቡ ብሶት የወለዳቸው እንቅስቃሴዎች በአንድ በኩል ሥር ነቅል ለውጥ ለማምጣት ሲጣጣሩ በሌላ በኩል ደግሞ ገና ያላደገ ጎብረተሰብ ውጤት በመሆናቸው በጎብረተሰቡ ይከሰቱ የነበሩት አሉታዊ አመለካከቶች ተጽዕኗቸውን አሳድረውባቸው ነበር። ድብቅነት፣ ተንኮለኝነት፣ ምቀኝነት፣ ማን አኽሎኝነት፣ የሚቃወምን በጠላትነት መፈረጅ፣ የተለየ ሐሳብ ያለመቀበል፣ ተቻችሎ አለመኖር፣ ወዘተ... የፖለቲካ ቡድኖቹና የጥናት ሕዋሶቹ ወደ ፖለቲካ ድርጅት ሲሸጋገሩም አልተለይዋቸውም ነበር።

6.2 የፖለቲካ ድርጅቶች መመሥረት

ከሺሕ ዘጠኝ መቶ ሠላሳዎቹ ቀደም ብሎ በኤርትራና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ትጥቅ እንግበው ከሥርዓተጋ መፋለም የጀመሩ ግንባሮች ነበሩ። እነዚህ ግንባሮች ከማዕከሉ ርቀው ይንቀሳቀሱ የነበሩ ቢሆንም በሺሕ ዘጠኝ መቶ ሠላሳዎቹ ለተጧጧፈው የፖለቲካ እንቅስቃሴ አስተዋፅኦ ማድረጋቸው አልቀረም። ሥርዓቱን በማናጋት ረገድ ትልቅ እምርታ የታየው ግን የፖለቲካ ማዕከሉ በሆነው የአገሪቱ ዋና ከተማ አዲስ አበባ በተኪያሄደው ከፍተኛ እንቅስቃሴ ነበር። ሁኔታዎች በፍጥነት ተለዋውጠው አንዳንድ አገር ዐቀፍና ብሔር ተኮር ቅድመ ፓርቲ ድርጅቶችና ግንባሮች በዋናነት በተማሪውና በምሁሩ መቋቋም ጀመሩ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያገኘኋቸው መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የፖለቲካ ድርጅት በማቋቋም ረገድ አንጋፋ የነበረው በ1960 ዓ.ም. ጀርመን አገር ሃምቡርግ ከተማ[81] በእነ ኃይሌ ፊዳ የተመሠረተው «*የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ*» /መኢሶን/ ነበር። አንዳንዶቹ መኢሶን በ1960 ዓ.ም. መመሥረቱን ቢጠራጠሩም፣ መረጃውን ትክክል ነው ብለን ከተቀበልነው መኢሶን ከኤርትራና ከሶማልያ ድርጅቶች ቀጥሎ የተቋቋመ አንጋፋ ፓርቲ መሆኑ ነው። እንደተባለው ከሆነ መኢሶን የተመሠረተው የኢትዮጵያ አብዮት ከመፈንዳቱ ከስድስት ዓመታት በፊት ቢሆንም በኢትዮጵያ የነበረው የፖለቲካ ተጽዕኖ

[81] ተስፋዬ መኮንን፣ 1985 ዓ.ም፣ *ይድረስ ለባለ ታሪኩ*፣ ብራና ኤሌክትሮ አሳታሚ፣ ገጽ 191

ዝቅተኛ ሆኖ ቆይቶ ፓርቲው በአገራችን ህልውናውን ያረጋገጠው «የሰፊው ሕዝብ ድምጽ» የሚል በራሪ ጽሑፍ በ1966 ዓ.ም. መጨረሻና በ1967 ዓ.ም. መጀመሪያ ገደማ ማሰራጨት ሲጀምር ነበር።

ሌላው በ1964 ዓ.ም. በጀርመን አገር በርሊን ከተማ[82] የተቋቋመው አገር ዐቀፍ ፓርቲ ደግሞ «የኢትዮጵያ ሕዝቦች አርነት ድርጅት» /ኢሕአድ/ ነበር። የዚህ ፓርቲ መሥራቾች በተማሪው እንቅስቃሴ ዕውቅ የነበሩት እነ ብርሃነ መስቀል ረዳ፣ እያሱ ዓለማየሁ፣ ዘርኡ ክሕሸንና በውጭ አገር ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱት እነ ዶክተር ተስፋይ ደበሳይ፣ ነበሩ። ይህ ድርጅት የተመሠረተው በውጭ አገር ቢሆንም አገር ውስጥ ከነበሩት እንደነ «አብዮት» ከመሳሰሉት ቅድመ ፓርቲ ድርጅቶች ጋራ አብሮ ለመሥራት ፍቃደኛ ሆኖ በመጨረሻም ተዋሕዷል። ከዚህ ሌላም የ1966 ዓ.ም. አብዮት ከመፈንዳቱ ከሁለት ዓመታት በፊት የትጥቅ ትግል ለመጀመር በምድረ ኤርትራ «ከሀዝባዊ ሓይልታት ሓርነት ኤርትራ» ወይም «ሻዕብያ» ተጨማሪ ሥልጠና ወስዷል። በመጨረሻም ድርጅቱን ከተወሐዱት ጋራ «የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ/ኢሕአፓ» ተብሎ ተሰይሞ «ዴሞክራሲያ» የሚባለውን ልሳኑን ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ በአገር ውስጥ ያሰራጭ ነበር።

ከፍ ብለው ከተጠቀሱት አገር ዐቀፍ ድርጅቶች ሌላ የትጥቅ ትግል ለማኪያሄድ በዝግጅት ላይ የነበረው «የኦሮሞ ነጻ አውጪ ግንባር/አነግ» በይፋ የተቋቋመው በ1966 ዓ.ም. ቢሆንም፣ ከዚያ ቀደም ሲል «በሚጫና ቱለማ» የኦሮሞ መረዳጃ ማኅበር ውስጥ ጥንስስ የፖለቲካ እንቅስቃሴውን ጀምሮ ነበር። የዚህ ድርጅት ቀደምት መሥራቾች ተብለው ከሚታወቁት መኻል እነ ባሮ ቱምሳ፣ ዘገየ አስፋውና ሌሎች ዕውቅ የኦነግ መሪዎች እስከ 1969 ዓ.ም. ድረስ አገር ውስጥ ይንቀሳቀሱ ነበር። እንዲያውም ባሮ ቱምሳና ዘገየ አስፋው «የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል/ኢጭአት»ን ወክለው በ«ኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ጎብረት/ኢማሌድጎ» እስከ 1969 ዓ.ም. ተሳትፈው ነበር። ዓላማቸው ለትጥቅ ትግሉ የከተማውን ክንፍ ለማደራጀት ይሁን ወይም በሰላማዊ ትግል መቀጠል ግልጽ ባይሆንም፣ ደርግ እስኪያስራቸው ድረስ በኢማሌድጎ አመራር ውስጥ ቆይተዋል።

ሌላው ብሔር ተኮር የፖለቲካ ድርጅት ደግሞ «ማሕበር ገስገሰቲ ብሔረ ትግራይ /ማገብት/ በአማርኛ፣ «የትግራይ ተራማጆች ማኅበር» የሚባለው ሲሆን፣ ይህ ድርጅት በይፋ የተቋቋመው መስከረም 1967 ዓ.ም. ላይ ነው። የዚህ ድርጅት መሥራቾች ቀደም ሲል በተለያዩ የጥናት ሕዋሶች ተደራጅተው ሲንቀሳቀሱ ቢቆዩም ወደ ፖለቲካ ድርጅትነት የተሻገሩት ግን ደርግ ሥልጣን በያዘ ማግስት ነበር። አብዛኞቹ የድርጅቱ መሥራቾች በዚሁ ዓመት መስከረም ወር ላይ ይኪያሄድ በነበረው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ፀረ-ደርግ እንቅስቃሴ ተሳታፊ ነበሩ።

ብሔር ተኮር ከሆኑት የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ማገብትን ቀድሞ የተቋቋመ በ1962 ዓ.ም. በአብዛኛው በትግራይ ተወላጅ ተማሪዎችና መምህራን የተቋቋመው «ማሕበር ፖለቲካ» ነው። የዚህ ድርጅት ሊቀመንበርም መምህር ዮሐንስ ተክለ ሃይማኖት ነበር። ድርጅቱ ትግራይ ውስጥ የትጥቅ ትግል ለማኪያሄድ ዝግጅት እያደረገ እስከ 1967 ዓ.ም. ድረስ በተጋድሎ ሓርነት ኤርትራ ውስጥ ተጠልሎ ይንቀሳቀስ ነበር።

[82] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 104

6.3 የዘውዳዊው ሥርዓት መገርሰስ

1966 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር በሥርዓቱ ላይ ያመፀበትና ዘውዳዊ አገዛዝን የገረሰሰበት ዓመት በመሆኑ በኢትዮጵያ ታሪክ ልዩ ቦታ አለው። የ1966 ዓ.ም. አብዮት በድንገት የተከሰተ ሳይሆን ከፍ ብሎ የተጠቀሰው የተከማቸ የጎብረተሰብ ብሶት ጣሪያ ላይ ደርሶ የፈነዳበት ወቅት ነበር። ገዥው መደብ ከሕዝቡ የተነሡትን ጥያቄዎች መመለስ እቅቶት አንዱን ሲቋጥር ሌላውን ሲፈታ ጭራሽ የተቸገረበት በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝቡ ቁጣ ከመረን ዐልፎ የገዥውን መደብ ህልውና የሚያስጠብቁ ተቋማት ውስጥ ጭምር የተዛመተበት ነበር።

በዚሁ ዓመት ጥር ወር ላይ በየአካባቢው ከተዛመቱት ክስተቶች ዋናው የሠራዊቱ ዐመፅ ሲሆን የዐመፁ ፋና ወጊ በነገሌ ቦረና የነበረው አራተኛው ክፍለ ጦር ነበር። ክፍለ ጦሩ በተደጋጋሚ ላቀረባቸው የሻገተ ምግብና የደፈረሰ ውሃ አቅርቦት ጥያቄዎች መልስ ባለማግኘቱ ብሶቱን እንዲያጠኑ የተላኩትን ከፍተኛ መኮንኖች በቁጥጥር ሥር አውሎ ከሠራዊቱ ጋራ እንዲመገቡ አደረገ። ከዚህ ባሻገር ወታደሮቹ እየደረሰባቸው የነበረውን በደል ለመላው ሠራዊት አሳውቀው በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ሰፍሮ በነበረው ሁለተኛ ክፍለ ጦር እጅግ የበረታ ተቃውሞ ተነሣ። ሁለተኛው ክፍለ ጦር በአሥመራ የነበረውን የሬድዮ ጣብያ በመቆጣጠር በዚሁ ሬድዮ ጣብያ አማካይነት በርካታ ጥያቄዎችን አቀረበ። ካቀረባቸው ጥያቄዎች መኻል የደመወዝ ጭማሪና የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተ ወልድ ካቢኔ ከሥልጣን መውረድ ከፍተኛ ቦታ የያዙ ነበሩ። ንጉሡም የሠራዊቱን ጥያቄዎች ሊያዳፍኑ ባለመቻላቸው ወድያውኑ የደመወዝ ጭማሪ አድርገው የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተ ወልድን ካቢኔ አውርደው በጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንን የሚመራ ካቢኔ አቋቋሙ። የሠራዊቱን ብሶት ለማጣራት የተሰየመው ኮሚቴም ሥራውን ቀጥሎ በወታደሩ የተቀሰቀሰው ዐመፅ ጋብ አለ።

ሆኖም የወታደሮቹ እንቅስቃሴ ጋብ ቢልም፤ ትምህርት ቤቶች ከተከፈቱ ጀምሮ ሲወራ የነበረው የድኻውን ልጅ በአራተኛ ክፍል ብቻ የሚገድብ «ሴክተር ሪቭዩው» ይሩ በመሆኑ ይህን በመንግሥት የተነደፈ የትምህርት ፖሊሲ በመቃወም መምህራን ዐድማ ጠሩ። የመምህራኑን ዐድማ በመደገፍም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሰልፍ ወጡ። መንግሥት የተለያዩ ማስተባበያዎችን ቢሰጥም፤ ሴክተር ሪቭዩው የኢትዮጵያን ሕዝብ በድንቁርና ለማኖር የተተለመ መሰሪ ፖሊሲ ነው በሚል ከወላጆች፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠመው።

በተጨማሪም ጎብረተሰቡ ሌሎች የተለያዩ ጥያቄዎችን ማቅረብ ጀመረ። በ1965 ዓ.ም. በተኪያሄደው የዓረብ-እስራኤል ጦርነት ምክንያት የአገር ውስጥ የነዳጅ ዋጋ በጎምሳ ከመቶ ጨምሮ ስለነበር የታክሲ ነጂዎች በነዳጅ ላይ የተደረገውን የዋጋ ጭማሪ ተቃውመው ዐድማ መቱ። በርካታ ገበሬዎችም ከገጠር እየመጡ በፓርላማው አካባቢና በየጎዳናው ተሰብስበው ስለሚደርስባቸው የመሬት መፈናቀልና የአስተዳደር በደል ቢጮኹም መንግሥት ሊያዳምጣቸው አልቻለም። ይህ ሁሉ ተደማምሮ በወርኀ የካቲት ከፍተኛ የሰልፍና የዐመፅ ናዳ ተከስቶ መንግሥትን እጅግ አስደነገጠው።

መጋቢት ወር ላይ ኑሮ የከበዳቸው የፋብሪካ ሠራተኞች ደመወዛቸው እንዲጨመር፣ ነጻ ማኅበራት እንዲያቋቁሙና የአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ እንዲሻሻል ጥያቄ አቅርበው ጥያቄዎቻቸው ካልተመለሱ የሥራ ማቆም ዐድማ እንደሚያደርጉ ዛቱ። ከጊዜ በኋላም የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር አባላትም አጠቃላይ የሥራ ማቆም ዐድማ እንዲጠራ

ጠይቀው ለአራት ቀናት የተደረገው የሥራ ማቆም ዐድማ የአገሪቱን ኢንዱስትሪ ከማንበርከኩም ባሻገር በነዳጅ ዋጋው ጭማሪ የተጎዳውን ኢኮኖሚ አዳከመው።

ሙስሊሙ የጎብረተሰብ ክፍልም የሚደርስበት የሃይማኖት ጭቆና እንዲወገድለት ጥያቄ ሲያቀርብ ቆይቶ መፍትሔ ባለማግኘቱ ሚያዝያ 1966 ዓ.ም. ላይ ከፍተኛ ሰላማዊ ሰልፍ ተጠርቶ በክርስትያን ወገኖችና በተማሪዎች ጭምር ተደግፎ፤ «*እሰላም እሰላም ምን ታየበት፣ ከሰው በታች የሆነበት*» ብሎ እየዘመረ፣ «*እኛ ሙስሊሞች ከክርስቲያን ወንድሞቻችን በምን እናንሳለን?*» የሚለውን መፈክር አንግቦ፣ የሃይማኖት እኩልነቱ እንዲከበርለትና በዓሎቹ ሕጋዊ ዕውቅና እንዲያገኙ ጠየቀ። ይህ የሙስሊሞች የመብት ጥያቄና ሰልፍ በየካቲት ወር ከፍተኛ ደረጃ ለደረሰው የሕዝቡ ዐመፅ ተጨማሪ ኃይል ሰጠው።

ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት ንጉሡ የሕዝቡን ዐመፅ ለማቀዝቀዝ ከየካቲት 1966 ዓ.ም. ጀምሮ የተለያዩ እርምጃዎችን ወስደው እጅግ የዘገየውን የካቢኔ ሹም ሽር እንዳደረጉ በደከመ ድምጻቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሳውቀው፤ በተጨማሪም ሕገ መንግሥቱ እንዲሻሻል ከተለያዩ የጎብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጣ የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን ቢያቋቁሙም፤ ሕዝቡ፣ በተለይ የተማረው የጎብረተሰብ ክፍል፣ ከእርሳቸው የጠየቀው መጠነኛ ማሻሻያ ሳይሆን ከሥልጣን ወርደው በሕዝብ የሚመረጥ መንግሥት እንዲቋቋም ነበርና ያሰሙት ንግግር ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ።

ንጉሡ የተነሣባቸውን ተቃውሞ ለማስታገስ የመረጡት ሌላ መንግድ ሠራዊቱ ውስጥ መከፋፈልን ፈጥረው ደጋፊዎቻቸውን ማጠናከር ነበር። ለዚህ ይረዳቸው ዘንድም በሚያዝያ ወር 1966 ዓ.ም. በጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንን ዘመድ በኮሎኔል ዓለም ዘውድ ተሰማ የሚመራ «*ብሔራዊ የደኅንነት ኮሚሽን*» አቋቁመው፤ በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ ጥቃት ለማኪያሄድ ቢሞክሩም ከሕዝቡ ዐልፎ የጦሩ ልሂቅ ክፍልም ልቡ ሸፍቶ ነበርና ሳይሳካላቸው ቀረ። የጦሩ አርሚ አቭዬሽን፣ መሐንዲስ ክፍል፣ የአየር ኃይልና ሌሎች የሠራዊቱ ክፍሎች በድብቅና ዐልፎ ዐልፎም በይፋ የሕዝቡን እንቅስቃሴ እንደሚደግፉ ይገልጹ ነበር። ይህም በሠራዊቱ ውስጥ አለመግባባትንና መከፋፈልን በመፍጠሩ ሕዝቡ ነጻነት አግኝቶ እንዲደራጅ ፋታ ሰጠው። የፖለቲካ ሊቃውንት እንደሚሉትም ለዓመታት ሊሳካ ያልቻለው ፍጻሜም በአጭር አብዮት ተፈጸመ። ወቅቱም ብዙዎቹ ቀድም ሲል የጠቀስኳቸው ቅድመ ፓርቲ ድርጅቶች ሊቋቋሙና ሊጠናከሩ የቻሉበት ነበር።

ሕዝባዊ ወገኖች ሥርዓቱን ለመቃወም ራሳቸውን ለማደራጀት ቢጥሩም ይህን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማከናወን ባለመቻላቸው የወታደሩ ክፍል ተሰባስቦ «ደርግ» በሚል አንድ ኮሚቴ አቋቁሞ ራሱን «*የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስና የብሔራዊ ጦር*[83] *አስተባባሪ ኮሚቴ*» ብሎ ሰየመ። ከሰኔ ወር በኋላ የፖለቲካ እንቅስቃሴውን የተቆጣጠረው ይኸው ወታደራዊ ኮሚቴ ለንጉሡ ያለውን ታማኝነት እየገለጸ ቀንደኛ ባለሟሎቻቸውን አንድ በአንድ በቁጥጥር ሥር አዋለ። ደርግ በወሰዳቸው እርምጃዎች ምክንያት ክረምት ላይ የንጉሡ ሥርዓት የሚደገፍበት ምሰሶ አጥቶ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም. ላይ ንጉሡ ከሥልጣናቸው ተወግደው «*ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር*» ታወጀ። ሆኖም ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ ለሕክምና ወደ ውጭ ከሄዱበት ሲመለሱ ንጉሣዊ ሥርዓቱ እንደሚቀጥል በዚህ አዋጅ ይፋ ሆኖ ነበር።

---

[83] Bahru Zewde, op.cit., p.233.

ምንም እንኳን በወቅቱ በርካታ አመለካከቶች ለምሳሌ የሕገ መንግሥታዊ ንጉሣዊ ሥርዓትን፣ ሪፐብሊካኒዝምና ኮምዩኒዝም ቢሰራጩም ጊዜው የአብዮት ነበርና ከሥር ነቀል ለውጥ ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበረም። በተማሪው ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት የነበረውና ወደ ሕዝቡም እየዘለቀ የነበረው ርዕዮተ ዓለም ማርክስያዊ ሌኒናዊነት ቢሆንም በወቅቱ ፍልስፍናውን በጥልቀት የተገነዘቡ ምሁራን መኖራቸው አጠራጣሪ ነው። የታሪክ ምሁሩ ባሕሩ ዘውዴ እንደሚሉት፤ *«ማርክሲዝም ሌኒኒዝም የተያዘው በእምነት ደረጃ እንጂ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ለመተንተን የሚረዳ የአስተሳሰብ ሥርዓት ተደርጎ አልነበረም። ንድፈ ሐሳቡቹ በመፈክሮች ተተክተው ይወሰዱ ነበር። ሥር ነቀል ለውጥ ፈላጊ መስሎ መታየት ራሱ ማንነት የሚረጋገጥበት ተግባር ሆኖ ነበር። በሌላ አነጋገር ይበልጥ ግራ መስሎ መታየት የተሻለ ሆኖ መገኘት ሆኖ ይወሰድ ነበር።*[84]» ከዚህ የተነሣም ሁሉንም ነገር የአገርንና የሕዝብን ጥቅም መሠረት በማድረግ ከማየት ይልቅ የማርክስያዊ ሌኒናዊ መጻሕፍትን በማገላበጥ ግልብ በሆነ አስተሳሰብ መተርጎም ተጀምሮ ነበር። ይህ የሆነው ወጣቱ ከነበረው ከፍተኛ የለውጥ ፍላጎት የተነሣ ቢሆንም፤ መነሻውና መድረሻው በውል ባልታወቀበት ሁኔታ ርዕዮተ ዓለምን መዞ መንቀሳቀሱ ኋላ ላይ በአገራችን ለተከሰቱት ችግሮች አንዱ መንሥኤ ሆኗል።

የንጉሡ ከሥልጣን መውረድ ያለቀለትና የሚጠበቅ ስለነበር ብዙዎችን ባያስገርምም ወጣቱን በተለይ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ያሳሰበው ንጉሡ ወርደው በሌላ አምባገነን ወታደራዊ መንግሥት መተካታቸው ነበር። ይህን የወታደሮችን ሥልጣን መቆጣጠር ሲቃወሙ የነበሩ ተማሪዎች መስከረም መጀመሪያ ላይ በአራት ኪሎ ግቢ ቢደርግ በተጠራው ስብሰባ ተገኝተው ስለደርግ ወደፊት አቅጣጫ ገለጻ ተሰጥቷቸው ከደርግ ጋራ ፍጹም መግባባት አቃታቸው። ደርጎች በወቅቱ ከተማሪው የቀረበላቸውን ሥልጣን ለሕዝብ የማስረከቡን ጥያቄ ፈጽመው እንዳልተቀበሉትና አመጣጣቸው ተማሪውን ለመስበክ እንጂ ለመመካከር እንዳልሆነም ከዚያ ቀን ጀምሮ ግልጽ ሆኖ ተራማጅ ነኝ የሚለው ተማሪና የደርግ ፍቺ ተረጋገጠ።

[84] ibid., p.226.